የኢትዮጵያ ሕግ

መጽሔት

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት
JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

ቮልዩም 14 ቁጥር 1

መጋቢት ፣ 1981 ዓ.ም.

Vol. 14 No. 1

March, 1989

ባለመብት ሕግ ፋኩልቲ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 1981 ዓ.ም.
Faculty of Law, Addis Ababa University, 1989

አዲስ አበባ Addis Ababa

ሕትመት በሕግ ፋኩልቲ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 1981 ዓ.ም.
Published by Faculty of Law, Addis Ababa University, 1989

ንግድ ማተሚያ ቤት
Commercial P. P.

የዝግጅት ቦርድ አባላት

ወንድማየሁ ምሕረቱ ፣ ሊቀመንበር
የፍትሕ ሚኒስትር

ቢልልኝ ማንደፍሮ
ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

አሰፋ ሊበን
ፕሬዚዳንት ፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ግርማ ሥላሴ ኦርአያ
ፕሬዚደንት ፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ታደሰ በየነ
ዲሬክተር ፡ ኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም

ዳንኤል ኃይሌ
ዲን ፣ ሕግ ፋኩልቲ

ሰላሙ በቀለ ፣ ጸሐፊ
ዋና አዘጋጅ

የዝግጅት ቡድን

ሰላሙ በቀለ
ዋና አዘጋጅ

ዘ. ኃሌሲክ ፣ የመጣጥፍ አዘጋጅ

ኢብራሂም እድሪስ ፣ ሥራ አስኪ.
ያጅ አዘጋጅ

መንበረጸሐይ ታደሰ ፣ የፍርድ ውሳኔ
ትችትና ወቅታዊ ጉዳዮች አዘጋጅ

ምህረት አደራዬ ፣ ጸሐፊ

ለሥራ ግንኙነት በሚከተለው አድራሻ ተጠቀሙ ፣ የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት
የመ.ሣ.ቁ. 1176 ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፡ አዲስ አበባ ፡ ኢትዮጵያ ።
ቴሌፎን 111733/110844 ውስጥ መስመር 108
ቴሌክስ/ቴሌግራም ፣ AAUNIV
21205

ረዳት አዘጋጆች

ሙሉቀን ተሾመ

ታከለ ተዘራ

ሙሐሪ ረዲኢ

ጋዩሉልሁል ሙሉጌታ

ሰይፈሥላሴ ለማ

ዘካርያስ ጋዩሉ

በላቸው እንቆጵኔ

የሰያስ ታደሰ

ደሰኪልኝ መሰጎ

ማውጫ

መጣጥፎች ፡—

ዳግማዊ ኦጼ ቴዎድሮስና በ1842 ዓ. ም.
በእንግሊዝና በኢትዮጵያ መካከል በተደረገው
ውል የተቋቋመው ግዛት ለቀቅ ልዩ
የዳኝነት ሥልጣን ።
ታምሩ ወንድምአገኘሁ ፡ 1

የአጼ ቴዎድሮስ ደብዳቤዎች ። 25

የወዳጅነትና ፣ የንግድ ውል በእንግሊዝ ንግሥትና
በሐበሻ ንጉሥ መካከል ። 27

ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ የሕግ አወጣጥ
ሥርዐት (በሁለት ክፍል) ።
ሺፈራው ወልደ ሚካኤል 30

የፍርድ ውሳኔዎች ፡—

ይግባኝ ባይ የአየለች ወልደገብርኤል
ሞግዚት ፣ መልስ ሰጭ ጥሩነሽ ተሰማ ፤
(የፍትሐ ብሔር ይግባኝ መ.ቁ. 394/72/ ።) 47

ይግባኝ ባይ ታደሰ ጉርሙ ፡ መልስ ሰጭ ጥሩወርቅ
ኢያሱ ፤
(የፍትሐ ብሔር ይግባኝ መ.ቁ. 1111/74/ ።) 56

ትችት ፡ —

ከጋብቻ ውጪ ወይም ከጋብቻ ውጭ ከሚገኝ የግብረ
ሥጋ ግንኙነት ኑሮ ውጪ የሚወለድ ልጅን አባትነት
ስለማወቅ ።
መስፍን ገብረሕይወት 63

ወቅታዊ ጉዳይ :—

የጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር የመጨረሻ ውሳኔዎችን መስማት ፣
ከተከራካሪ ወገኖች ለአንደኛው የተሰጠ ሌላ የይግባኝ መብት ነውን ?
ዮሴፍ ገብረእግዚአብሔር 72

ዳግማዊ ቶጼ ቴዎድሮስና በ1842 ዓ.ም. በእንግሊዝና በኢትዮጵያ መካከል በተደረገው ውል የተቋቋመው ግዛት ለቀቅ ልዩ የዳኝነት ሥልጣን

ታምሩ ወንድምአገኘሁ *

መግቢያ

ዳግማዊ ቶጼ ቴዎድሮስ ስማቸው በውደሳ ገኖ የተነሳውን ያህል በጥላቻም ከተወሱ መሪዎች መካከል አንዱ ሳይሆኑ አይቀሩም ። በእርግጥም ሊወደሱበት ከሚገባቸው ሥራዎች አንዱ በራስ ዓሊ ላይ በተጎናጸፉት ድል ኦማካይነት ከሥልጣኑ መንግሥቱ ጋር የተረከቡትን ለእንግሊዝ ቆንስል ልዩ የዳኝነት ሥልጣን የሚሰጠውን ውል አልቀበልም ማለታቸው ነው ** ። በቀላል አገላለጽ ከግዛት ውጭ ልዩ የዳኝነት ሥልጣን የሚያጎናጽፈው የውል መብት ባዕዳን ከራሳቸው ግዛት ውጭ እንኳ ሲገኙ በራሳቸው ብሔራዊ ሕግጋት ጥበቃ ሥር እንዲኖሩ ዋስትና የሚሰጥ ሥርዓት ነበር ።

ይህ ይሆንበት የነበረው ምክንያቱ ከዘመን ዘመን እየተለያየ የመጣ ነው ፤ በመጀመሪያ መሰረቱ የሃይማኖት ልዩነት ሲሆን ፤ ከጊዜ በኋላ ግን እንደ ንግድ የመሳሰሉትን ሌሎች ጥቅሞችን መጠበቂያ ሰበቦች ማካተት ጀመረ ። በጽንሰ ሃሳቡ አራማጆች አባባል ይህ የተለየ ጥበቃ ያስፈለገው ኋላ ቀርና ዝቅተኛ የሆነ የዕድገት ደረጃ ያላቸው ተቀባይ አገሮች የውጭ ዜጎችን አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ለመጠበቅ ሥልጣኔ የሚጠይቀውን ሥርዓት የሚያሟላ የሕግ መድረኮች ስለሌላቸው ነው ። [1]

ግዛት ለቀቅ ልዩ የዳኝነት ሥልጣን በዚህ መልኩ በአጠቃላይ ባንድ በኩል የሰለጠነ ተብሎ የሚጠራ መንግሥትና በሌላ በኩል ደግሞ ኋላቀር የሆነ መንግሥትን የሚያቅፍ ስምምነት ሆነ ። ነገር ግን በዚህ ዓይነት ውል ውስጥ ኋላቀር የሆነው ተዋዋዩ መንግሥትን ያለ ምንም ጥቅም ከነጻዊ የላቀ መብቱ ላይ ቀንሶ መስጠት ይጠበቅበት ስለነበረ ምንግዜም ቢሆን ተጎጂ እንጂ ተጠቃሚ አልነበረም ።

ይባስ ነገር ደግሞ ይህን ዓይነት ስምምነት ከአንድ መንግሥት ጋር ሲደረግ የውሉ ተዋዋይ ያልሆኑ ሌሎች ነገሮች የውሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችል ነበር ። ይህ የሚሆነው ቀድሞ በነበሩ ወይም አዲስ በተፈረሙ ውሎች ውስጥ የሚገኘውን “ ይበልጥ ተጠቃሚ አገር ” የሚለውን አንቀጽ ሥራ ላይ በማዋል ነበር ። [2] ይህ ዓይነቱ አሠራር በግልጽ እንደሚታየው የውል ተቀባዩን መንግሥት ራሱን በራሱ በነጻ ማስተዳደሩን በብዙ መንገድ የሚገድብ ነበር ። ይህን በተለያዩ ሁኔታዎች ስናየው ባዕዳኑን ሕብረተሰብ ከሚኖሩበት ወይም ከሚሰሩበት መንግሥት የሥልጣን ክልል ውጭ ማድረግ ነበር ። በተጨማሪም ስምምነቱ ቆንሲሉን ወይም የዲፕሎማቲክ ልዑክ የሆነውን የውጭ አገር ሰው የተቀባዩን መንግሥት የዳኝነት ሥልጣን እንዲነጥቅ ብቻ ሳይሆን የራሱንም አገር የሕግ ሥር

** ከዚህ መጣጥፍ ቀጥሎ የሚገኙትን የቴዎድሮስን ደብዳቤዎችና የ1842 ዓ.ም የወዳጅነትና የንግድ ውል እንደ ማስረጃ ሰነድ ስለሚጠቀሙ ተመልከት (አዘጋጅ) ።

ዐት ቢያንስ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ሉዐላዊና ነጻ በሆነ አገር ውስጥ ሥራ ላይ እን ዲያውል አስችሎታል ።

የንግድ የሥራ ዘርፉ በብዛት የሚንቀሳቀሰው በውጭ አገር ተወላጆች ስለ ነበረ ይህ ዓይነቱ ስምምነት ይህን የሥራ ዘርፍ ከተቀባዩ መንግሥት ቁጥጥር ውጭ እንዲሆን የማድረግም ተጨማሪ ውጤት አለው ። ይህም በአጭሩ ተቀባ ዩን መንግሥት ለባሰ ጉዳት የዳረገና ብዙ ጊዜም ወደቅኝ ግዛትነት ወይም በሞ ግዚትነት ወደ መተዳደሩ ደረጃ ዝቅ እንዲል ሁኔታዎችን ያመቻቸ የጥቃት በር ከፋች ነበር ። [3]

የዚህ ዓይነቱን አሠራር መሠረ ባህሪይ ያልተረዱት ሁሉም ለሰለባው የተ ጋለጡ መንግሥታት መሪዎች አልነበሩም ፤ ከ1847 — 1860 ዓ.ም. የነገሡት ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የዚህ ዓይነቱን ውል እኩይ ነት አስቀድመው ከተገነዘቡትና ፊት ለፊት ለመቋቋም ከቆረጡት መሪዎች አንዱ ነበሩ ። በኢትዮጵያ ነጻነት ላይ ይህን የመሰለ ማዕቀብ ለመጣል የተደረ ገው ሙከራ በዓይነቱ ቀዳሚና የመጀመሪያው ነው ። ቴዎድሮስ ያሳዩት ሃሳበ ጽኑነት የእንግሊዝ ሥልጣነ መንግስት በኢትዮጵያ እንዲንሰራፋ ከመቀበል ይልቅ የራስን ሕይወት በገዛ እጅ ማጥፋትን የተሻለ ምርጫ አድርጉ እስከማቅ ረብ የዘለቀ ነበር ።

የ1842 ዓ.ም. ውል መነሻ

ይህ አነስተኛ ጽሑፍ የውሉንም ሆነ የአጼ ቴዎድሮስን ታሪክ ለማቅረብ አይሞክርም ። በዚህ ጽሑፍ ለማድረግ የታቀደው በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መካ ከል በ1842 ዓ.ም. በተደረገው ውል ውስጥ ስላለው የቆንሲል ልዩ የዳኝነት ሥል ጣን ዋና ዋና ነጥቦችን ለመጠቋቆምና በንጉሠ ነገሥቱ ከተሰነዘሩት ተቃውሞ ዎች መካከል ጥቂቶቹን ለማመልከት ነው ።

ሆኖም ግን ይህን ለማድረግ በመጀመሪያ የውሉን መነሻና ከሱም ጋር በቅ ርብ የተያያዙ ሰዎችን ታሪክ በጥቂቱም ቢሆን መዳሰስ ተገቢነት ይኖረዋል ።

በአንድ መልኩ የ1842 የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ውል ታሪክ የዋልተር ቺችል ፕላውዴን ታሪክ ነው ለማለት ይቻላል ። ዋልተር ፕላውዴን እንደ አው ሮፓውያን አቆጣጠር ነሐሴ 3፣1820 ተወለደ። በ19 ዓመቱ ወደ ሕንድ ሄደ ፤ እዛም በካልካታ የሚገኘው የካር ፤ ታጉርና ኩባንያው ድርጅት ሠራተኛ በመሆን ለአራት ዓመታት ከሠራ በኋላ ወደ እንግሊዝ አገር ለመመለስ ከሥራው ተሰናበተ ። በ1836 ገደማ ስዌዝ ከተማ ፣ ግብጽ አገር ፣ እንደደረሰ በብሪታንያ ጦር ውስጥ የቀድሞ የባህር ኃይል መኮንን የነበረውን ሚስተር ጆን ቤልን አገኘውና የነጭ ዓባይን ምንጭ ለማግኘት በሚደረገው ፍለጋ ከሚስተር ቤል ጋር ለመጓዝ ወዲያውኑ ወሰነ ። አምስት ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ ያደረገው ቆይታ በጊዜው ታዋቂነት የነበራቸው መሪዎች ዕውቀትና ከበሬታም አትርፎለት ነበር ።

ከነሱም መሐል ራስ ዓሊና ደጃች ውቤ ይገኙ ነበር ። እነዚህ ሁለት ኃያላን ጦረኞች የወቅቱ ከፍተኛ የሥልጣን ተፋላሚዎች ነበሩ ። የሚፋለሙትም አንዱ ሌላውን በመጣል የእንጋሽነቱን ሥልጣን ይዞ የፈለገውን ለስም ያህል በማንገስ በስሙ ጠቅልሎ አገር ለመግዛት ነበር ።

በዚያ ለሥልጣን በሚደረገው መራኮት ውስጥ ሁኔታዎች ያደሉት ለራስ ዓሊ ነበርና ፣ ፕላውዴን ወደ እንግሊዝ አገር ለመሄድ ሲነሳ እግረ መንገዱንም የራስ

ዓሊ መልዕክተኛ በመሆን ለማገልገል ተስማማ ። ከፕላውዴን ጋርም ልዩ መልዕክተኛ በመሆን አለቃ ደስታ ተልከው ነበር ። ነገር ግን በቀይ ባሕር ላይ ሲጓዙ ያጋጠማቸው የመርከብ አደጋ ከፉኛ አስመርሯቸው ነበርና ካይሮ ሲደርሱ ወደ ለንደን ጉዞውን ለመቀጠል ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ ።[4]

መልዕክቱ እስከዚህም ቁም ነገር ያልነበረው በመሆኑ ራስ ዓሊ በጽሑፍ ከማድረግ ይልቅ በቃል እንዲላክ ነበር የመረጡት ። ልዩ መልዕክተኛው ወደ እንግሊዝ አገር ጉዞውን ለመቀጠል ፈቃደኛ ባለመሆናቸውና ፤ ለንግሥቲቱ እንዲሰጡ የተላኩትን ጥቂት የስጦታ ዕቃዎች በአደጋው ምክንያት ውሀ ስለበላባቸው የቃል መልዕክቱን ብቻ ለታላቋ ብሪታንያ የማቅረብ ብቸኛ ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ያረፈው ፕላውዴን ላይ ነበር ።

በራስ ዓሊ በኩል የተልዕኮው ዓላማ ከመልካም ምኞት መግለጫነት የሚያልፍ አልነበረም ። ይህንኑ ከፕላውዴን ማስታወሻ ውስጥ ቀጥሎ ከተጠቀሰው ክፍል መረዳት ይቻላል ።[5]

> መልካም ምኞት መግለጫዎችን ከመለዋወጥና
> በዚሁ መንፈስ ለእንግሊዝ ተጓዦች ሁኔታዎችን
> የሚያመቻቹና ጥበቃም የሚሰጡ መሆናቸውን ከመግለጥ
> ባሻገር ራስ ዓሊ ዓላማ አላቸው ብሎ መገመት አይቻልም ።

ለፕላውዴን ግን ተልዕኮው የታወቀ ዓላማና ውጤት ነበረው ። ከሁሉ በፊት ተልዕኮው በብሪታንያ መንግሥት ወጪ እንግሊዝ አገር ደርሶ ለመመለስ አስችሎታል ። ሁለተኛም አጋጣሚው ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር የመገናኘት ዕድሉን ከፍ ስላደረገለት ብሪታንያ ኢትዮጵያን በተመለከተ መከተል ይገባታል ብሎ የሚያምንበትን ሀሳብ ለመሰንዘርና ለተቀባይነቱም የበኩሉን ግፊት ለማድረግ ሳያስችለው እንዳልቀረ ይገመታል ። በመጨረሻም ገኖ ብቅ ያለው ፕላውዴን የዓሊ መልእክተኛ ሳይሆን ፕላውዴን እንግሊዙ ነበር ። ታላቋ ብሪታንያም በጉዳዩ ላይ ሳትዘገይ ውሣኔ ሰጠች ፤ በ1840 ዓ.ም. ገደማ መቀመጫው ምጽዋ ላይ ሆኖ በሀበሻ የእንግሊዝ ቆንሲል እንዲሆን ፕላውዴንን ለመሾም ፓልመርስቶን ወሰነ ።

ቀጥሎም ተጨማሪ ምክር ተደርጎ የሥራውን ዝርዝርና መመሪያ ከተቀበለ በኋላ ለራስ ዓሊ እንዲያደርስ የተሰጠውን ደብዳቤና “ መሰረታዊ ለውጥ ሳይደረግበት ” እንዲፈራረሙ የተረቀቀውን ውል ይዞ በምጽዋ በኩል አድርጐ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት በጥር 1841 ዓ.ም. ጉዞውን ጀመረ ። እንግዲህ የፕላውዴን ተልዕኮ ሁለት ተግባሮችን ማከናወን ነበር ።

የመጀመሪያው በምጽዋ የእንግሊዝን የቆንሲል መሥሪያ ቤት ማቋቋምና መቀመጫው እዚያ ሆኖ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የብሪታንያ ቆንስል በመሆን ማገልገል ፣ ሁለተኛው ደግሞ በንጉሡ ወይም በንጉሡና በራስ ዓሊ ስም የተረቀቀውን ውል ራስ ዓሊ እንዲስማሙበትና ሁለቱም እንዲፈርሙበት ማድረግ ነበር ።[6] ይህ የፕላውዴን ጥንድ ተልዕኮ ውጤትንም ውድቀትንም የተላበሰ ነበር ። ራስ ዓሊን በሚመለከት ተልዕኮው የተሳካለት ሲሆን በአጼ ቴዎድሮስ በኩል ግን ያጋጠመው ተልዕኮውን ሙሉ በሙሉ የሚያከሽፍ ሁኔታ ነበር ።

የቆንስላው መቋቋምና የቆንሲሉ መሾም ከሁለቱ አገሮች የጋራ ስምምነት ያልመነጨ በመሆኑ የታላቋ ብሪታንያ ብቸኛ ሃሳብ መሆኑ ግልጽ ነው ። ሆኖም ቆንሲሉ ሥራውን እንዲያካሄድ የታሰበውን መሥሪያ ቤት በወቅቱ በቱርክ አስ

ተዳደር ሥር በምትገኘው በምጽዋ አድርጐ መሆኑ ይህን የእንግሊዝ ብቸኛ ውሣኔ ውጤት የሚያለሳልሰው ይሆናል ።

ምንም እንኳ ፕላውዴን የመጀመሪያው ቆንሲል ሆኖ ቢሾምም ለሀበሻ አገር ቆንስላ የማስፈለጉን ሃሳብ ለማፍለቅ የመጀመሪያው ሰው አልነበረም ። ቻርልስ ቤክ ቀደም ብሎ በ1838 ዓ.ም. ይህን ሃሳብ ማቅረቡን ገልጧል ። ስለዚህም ሲጽፍ "የነገሩ መነሻ የእርሻ ሠራተኞችን ከሀበሻ አገር ለማግኘት በ1838 ዓ.ም. የአቀረብኩት ሃሳብ እንጂ ከፖለቲካ ዓላማ የመነጨ አልነበረም" ብሏል ።[7] ፓልመርስቶን ምክንያቱን ከንግድ ጋር ያያይዘዋል ፤ ፕላውዴንም ቆንስላው በኢትዮጵያ ምድር ላይ መቋቋም አለበት በማለት አጠንክሮ ቢያሳስብም ፓርልመርስቶን "እኛ የምንፈልገው ንግድ ነው ፤ ለንግድ ደግሞ መሬት ነ ያስፈልገውም"[8] በማለት ሃሳቡን ውድቅ አድርጐታል ።

ነገር ግን ቆንስላውን ማቋቋም ያስፈለገበት ምክንያት ወይም ለቆንስሉ የተሰጡት ሥራዎች በቤክና በፓልመርስቶን እንደተባለው ፖለቲካ ነክ ያልሆኑ ወይም ቀላል ዓላማ ያላቸው ፈጽሞ አይመስሉም ። ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ የተከሰቱት ሁኔታዎች በግልጽ የሚያስረዱት ይህንኑ ነው ። በሸዋ ፣ በትግራይና በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ መሳፍንቶችን ድጋፍ ለማግኘት ሃይማኖትንና ፖለቲካን መሣሪያ በማድረግ በተለይም እንግሊዝና ፈረንሳይ ያጧጧፉት በነበረው ትግል የተንጸባረቀው በአውሮፓውያን መካከል በወቅቱ የተካሄደው ርኩቻ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረጉ ግልጥ ነው ።

ፈረንሳይ በአካባቢው ለመስፋፋት ያላትን አዝማሚያ ተገንዝቦ እንግሊዝ ከዚህ አደጋ ራሷን ለመከላከል እንድትችል እንግሊዛዊው ቪስካውንት ቫሌንሺያ (የቀድሞ ሰር ጆርጅ አንስሌይ) ሥጋቱን ገና በ1797 የገለጸው በሚከተለው አኳኋን ነበር ።[9]

"የእስልምና ግማሽ ጨረቃ ካሁን በኋላ ለክርስትና አደገኛነት የለውም ፤ ነገር ግን ከሱ ያላነሱ አደገኛነት ያላቸው በማንሰራራት ላይ ያለችው የፈረንሳይ ንስር በጥንታዊ ተቋሞች ላይ ጠቅላላ ውድመትን ለማስከተል በማስፈራራት ላይ ነው ፣ ግፈኛ ጌታቸውም እቅዱን ያወጣው በተለይ በምስራቃዊው የእንግሊዝ ግዛት ላይ መሆኑ ግልጽ ነው ። ግብጽም የተያዘችው ይህን ዓላማ ለማራመድ ሲባል ነው ፤ ይህም የአረብ ኃይሎችን ወዳጅነት ለማሳደግ የሚደረግ ጥረት ነው ። ሀበሻ ከነዚሁ ሁሉ የላቀ ጠቀሜታ ያላት ቢሆንም እንደ እድል ሆኖ ወደ ሀበሻ ዘልቆ ለመግባት የሚቻል መሆኑን ለፈረንሳይ እስካሁን አልተከሰተላትም ።"

ቪስካውንቱ ታላቋ ብሪታንያ በሀበሻ ምድር ቀድማ የደረሰች እንደመሆኗ በዚህ ዕድሏ ተጠቅማ ከአገሪቱ ጋር ግንኙነት እንድትመሠርትና "ፈረንሣይ ምንጊዜም ቢሆን እንዳትገባ እንድታደርግ ፤ ግን በዚህ አጋጣሚ ሳንጠቀም ችላ ብንል የድክመታችን ተጠቃሚዎች ፈረንሣዮች ይሆናሉ" ሲል አስገንዝቧል ።

በ1832 ዓ.ም. ብሪታንያ ኤደንን መያዝዋና የካቶሊክ ሚሲዮንም በሰሜናዊ ኢትዮጵያ መስግሰግ እንዲሁም በዘይላና በታጁራ ፈረንሣዮች በወቅቱ ያደርጉት የነበረው ከፍተኛ እንቅስቃሴ በሁለቱ አገሮች መካከል የሚካሄደውን ሽኩቻ ለማሻሻል የሚረዱ ምልክቶች አልነበሩም ።

ፕላውዴን ከሞተ በኋላ ኃላፊነቱን አልተወጣም ተብሎ ከውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤታቸው ባለሥልጣኖች ለተሰነዘረበት ወቀሳ የፕላውዴን ወንድም ከሰጠው ምሬት የተሞላበት መልስ የምንረዳው ይህንኑ ሁኔታ ነው ። እንደሱ

ሊባባልም [10] "የቆንሲሉ ኃላፊነቶች የውጭ ኃይሎችን ፤ በተለይ የፈረንሳይን ፤ ተንኮል በተጠንቀቅ መጠበቅና ነጸፋውን መመለስ ፤ በሀበሻና በግብጽ መሐል ሰላምን መጠበቅ ፤ ባርነት እንዲወገድ ማስደረግና በታላቋ ብሪታንያና በሀበሻ መሐል የንግድ ልውውጥን መመስረትና ማራመድ ናቸው ። "

ለማንኛውም የቆንሲል መላኩ ዓላማ ምንም ሆነ ምን ፕላውዴን እንደቀድሞው በተራ ተጓዥነቱ ሳይሆን የታወቀ ተልዕኮ ያለው የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ሆኖ በ1841 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ተመልሶ ጉንደር ገባ ።

ለውጭ ጉዳይ መ/ቤት ፕላውዴን ያቀረበው ሪፖርት እንደጠቆመው ለራስ ዓሊ ያመጣውን ስጦታዎች ለማበርከትም ሆነ ለብሪታንያ ቆንስላነቱ ተቀባይነት ለማግኘት ያጋጠመው ችግር አልነበረም ።

እንዲሁም የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ብቻውን ያረቀቀውን ውል ይዞት በተመለከተም ያጋጠመው ምንም ዓይነት ተቃውሞ አልነበረም ።

ከውሉ ጋር የተያያዘ አንድ ችግር ቢኖር የውሉን መንፈስና ይዘት ለመግለጥ እሳቸውን አግኝቶ ለመነጋገር ነለመቻሉ ነበር ። ፕላውዴን እንደገለጠው በዚህ ረገድ ጆን ቤል የሚባለው የአገሩ ሰው በጣም ረድቶታል ፤ ጆን ቤል ቀደም ብሎ ለራስ ዓሊ አድሮ ስለነበር በርሳቸው ዘንድ ከፍተኛ ክብርና ሞገስ ማግኘት ችሎ ነበር ።

በመጨረሻም ፕላውዴን ለስምንት ወራት ከራስ ዓሊ ጋር ዘመቻ ሲንከራተት ከቆየ በኋላ በጉጃም ክፍለ ሀገር እናውጋ በምትባል ሥፍራ ጥቅምት 24 ቀን 1842 ዓ.ም. የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤቱ እንዳዘዘው ንጉሡን ሳይሆን ፤ ራስ ዓሊን ውሉን ለማስፈረም ችሏል ።

በዚህም የተነሳ ራስ ዓሊ "የፈረሙት ውል ከፍተኛ ቁምነገር ያዘለ መሆኑን እንዲገነዘቡት ለማድረግ ይረዳ ዘንድ" የውሉ ማጽደቂያ ሰነድ ለራስ ዓሊ እንዲላክ ፕላውዴን ለውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ያቀረበውን ማሳሰቢያ መሥሪያ ቤቱ ተቀብሎት የተላከላቸውን የማጽደቂያ ሰነድ ራስ ዓሊ የካቲት 22 ቀን 1844 ዓ.ም. ተቀብለውታል ። [11]

ውሉ የተፈረመበትን ሁኔታ ፕላውዴን ስዕላዊ በሆነ አገላለጽ እንደሚከተለው አስቀምጦታል ። [12]

> . . . አንድ ቀን ጠዋት ወደ ዕልፍኝ ድንኳን ገባሁና ጸሐፊዎ ውሉን እንዲያነብላቸው አደረግሁ ።
> . . . . . ወዳጃቸው ከሆነ አንድ ሹም ጋር በድንኳኑ ውስጥ ስለ ታሰረ አንድ ፈረስ ይነጋገሩ ነበር ። ፈረሱ የታሰረው አጠገቤ ነበርና ደጋግሞ ሊረግጠኝ ምንም አልቀረውም ። ሁላችንም ፤ ራስም ጭምር የተቀመጥነው መሬት ላይ ነበር ። ቁምነገር የሌለው ጥያቄ አቅርበውልኝ እኔም ይልቁን የሚነበበውን ጉዳይ ልብ ብለው ይከታተሉ ብዬ ተማጸንኩ ። እሳቸውም ሀሳቤን ተቀብለው በሰፊው አዛጉ ። የኔ ማብራሪያና መግለጫ ታክሎበት ሰነዱን ዘለቅነው ፤ ከዛም ሰነዱ በያዘው ነገር ምንም ጉዳት እንዳላዩበት ራስ ተናገሩ ፤ እንዲያውም በተቃራኒው እጅግ በጣም ጥሩ ሆኖ እንዳገኙት ከገለጡ በኋላ ሀበሻ በነበረችበት ሁኔታ በአሥር ዓመት እንኳ አንድ እንግሊዛዊ ነጋዴ ሊመጣባት አይችልም

> ብለው መገመታቸውንና በዚህም የተነሳ ውሉ ፈጽሞ ጥቅም የለሽ ሆኖ እንደሚቀር እምነታቸውን ገለጡ ። ቀጥሎም በሁለቱ ውል ቅጂዎች በማህተማቸው ካተሙ በኋላ የራሳቸውን ድርሻ ለሚያቀርቡት አንድ ደብተራ ሰጥተው ደብረ ታቦር ወስዶ እንዲቆልፍበት አዘዙ ።

ስለሆነም ዓሊ ሥልጣን ላይ ብዙ የሚቆዩ አልሆኑም ። እንኳንስ የውሉን ሥራ ላይ መዋል ሊያዩ ቀርቶ ቆንስላውንና የውሉን ዋንኛ ነጥቦች በአደባባይ ለማወጅ እንኳ ፋታ አላገኙም ። ወታደሮቻቸው በአማቻቸው ና በኋላ ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በሆኑት በካሣ ጦር በተከታታይ በመሸነፋቸው ውድቀታቸው ውሎ ሳያድር ተፋጥኖ ደረሰ ።

ከአራት ዓመት በፊት " ዓሊ ንጉሡ አበሻ " የሚል ቅጥያ ጨምረው ውሉን የፈረሙት የራስ ዓሊ ሥልጣን በፍጥነት ማሽቆልቆልና የነገሮች መለዋወጥ ፕላውዴንን እጅግ ስላሳሰበው ከራስ ዓሊ ጋር የተደረገው ውል " ዋጋ ቢስ መሆኑ የማይቀር ነው " በማለት ሥጋቱን ለውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት እስከመግለጽ አድርሶት ነበር ።[13] ወዲያውኑ ራስ ዓሊ ከመድረኩ ሲገለሉ የሳቸውን ቦታ ለመያዝ ካሣና ውቤ ዋንኛ ተፎካካሪዎች ሆነው ብቅ አሉ ። ይህም ሽኩቻ ብዙ የቆየ አልነበረም ።

በካሣና በውቤ ወታደሮች መካከል በየካቲት ወር 1847 ዓ.ም. የተደረገው የደረስጌ ጦርነት የውቤ ዕድልና የዘመነ መሳፍንት ማክተሚያ ሆኗል ። በተከታታይ ውጊያዎች ድል አድራጊነቱን የተጎናጸፉት ካሣ ከሳቸው በፊት የነበሩ መሪዎች ይሰገበገቡለት የነበረው የሺሚ ሻሪነት የውሸት ሥልጣን ሊያረካቸው አልቻለም ። ሁኔታውን ለማስወገድ ቆርጠው የተነሱ በመሆናቸው በስም ብቻ በዙፋን ላይ በተቀመጠው ንጉሥና ሥልጣንን ጠቅልሎ በያዘው አምባ ገነን መካከል ያለውን መጋረጃ አስወግዶ ሁለቱንም በአንድ መሪ ሰውነት ማዋሀድ ነበረባቸው ።

ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተሰኝተው የካቲት 4 1847 ዓ.ም. ገደማ በደረስጌ ማርያም ቤተክርስቲያን ዘውድ ሲደፉ ያሳኩት በትክክል ይህንኑ ነበር ። ያ ወቅትም ያረጀው ዘመን የማክተሚያው መጀመሪያና የአዲሱ ደግሞ የመጀመሪያው ምዕራፍ ነበር ለማለት ይቻላል ።

ካሣ ቴዎድሮስ ተብለው በመንግሥት ሥልጣን ቁንጮ ላይ በመቀመጣቸውና ጦርነቱም ያስከተለውን ሁከት ምክንያት በማድረግ ፕላውዴን ከራስ ዓሊ ጋር ስለተፈራረመው ውልና እራሱም በኢትዮጵያ የብሪታንያ ቆንሲል ስለመሆኑ ለቴዎድሮስ ማስታወስ ወቅቱ መስሎ ታየው ።

በአዲሱ ጌታው ሥር ይበልጥ በተመቸው በጆን ቤል አማባቢነት ሰኔ 1847 ፕላውዴን ቴዎድሮስ ቤተመንግሥት ተገኘ ።

የ1842 ውል

በዚሁ ከመቀጠላችን በፊት ግን አግባብ ያለውን የውሉን ክፍል ባጭሩ መመልከት ጠቃሚነት ስለሚኖረው ወደዚያው እንመለሳለን ።

በ1842 ዓ.ም. እንግሊዝና ኢትዮጵያ የተፈራረሙት ውል በሁለቱ አገሮች መካከል የተደረገ የንግድና የወዳጅነት ውል ነበር ።[14]

ውሉ 19 አንቀጾች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያዎቹ 16 አንቀጾችና የመጨረሻው የውሉ አንቀጽ በሸዋና በእንግሊዝ መካከል ኅዳር 7 ቀን 1834 ዓ.ም. [15] በሸዋ ዋና ከተማ በአንኮበር በሸዋው ንጉሥ በሳህለ ሥላሴና በካፒቴን ሐሪስ መካከል ከተፈረመው ባለ 16 አንቀጽ ውል ጋር እጅግ የተመሳሰሉ ነበሩ ።

አንቀጾቹ በአብዛኛው የሚናገሩት በሁለቱ አገሮች መሐል ስለዲፕሎማሲያዊ ወኪሎች ልውውጥና የንግድ ግንኙነቶች ስለሚካሄዱበት ሁኔታዎች እንደዚሁም አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ምን ያህል ቀረጥ መጣል እንዳለበትና የአከፋፈሉን ሁኔታና ሥርዓት አወሳሰን ጉዳይ ነው ።

ነገር ግን በነዚህ አንቀጾች እንደተደነገገው የግንኙነቱ መሰረት ሁለቱን አገሮች እኩል ከመጥቀም ይልቅ ወደ እንግሊዝ ያዘነበለና የእንግሊዝን ጥቅምና የበላይነት በኢትዮጵያ ውስጥ ለማራመድ የሚያስችል ሁኔታ ሽፋንፋን ባለ መልኩ የተቀነባበረበት ነበር ።

ነገር ግን ይበልጥ ተዋራጅ የሚደርገው የውሉ ክፍል ጠንቀኛ በሆነው 17 [16] ቁጥር ሥር የተመለከተው የውሉ ቃል ነው ።

ውሉ የተጻፈው በእንግሊዝኛና በአማርኛ ቋንቋዎች ሲሆን ይህም በያንዳንዱ ገጽ ላይ ጎን በጎን ሰፍሮ ነበር ። ሆኖም በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል ግጭት ሲነሳ የየትኛው ቋንቋ የውል ቃል የበላይነት ማግኘት እንዳለበት ውሉ ፍንጭ የሌለውና አንቀጽም ያልያዘ ነበር ። ግጭት ግን በእርግጥም ነበር ። ግጭቱም የተከሰተው በዚሁ በአንቀጽ 17 ውስጥ ሆኖ የእንግሊዝን ቆንሲል የመዳኘት ሥልጣን በሚያዳክም ሁኔታ ነበር ።

የአንቀጹ የመጀመሪያና የመጨረሻ ክፍሎች ሁለቱም ቋንቋዎች በተዋጣ መልክ የተስማሙበት ነበሩ ። ሆኖም ልክ አውቆ የተሠራ ይመስል ስለ ቆንሲሉ ሁለተኛ የዳኝነት ሥልጣን የሚናገረው በአማርኛው ጽሑፍ አንቀጽ 17 አጋማሽ ላይ የሚገኘው ክፍል የእንግሊዝኛው ጽሑፍ ፍጹም ተቃራኒ ነበር ። በአማርኛው ጽሑፍ ውስጥ ይህ ክፍል እንዲህ ይላል ።

> . . . . . በማንም ነገር ጠብ ቢነሳ ሙግትም በእንግሊዝ ዜጎች ቢነሳ ወይ በእንግሊዝ ዜጎችና በሐበሻ ንጉሥ ዜጎች ማኸል ወይ በእንግሊዝ ዜጎችና በሌላ አገር ዜጎች መሐል ቢነሳ በንጉሥ ሀበሻ ግዛት <u>የሀበሻ ንጉሥ</u> * ቆንሲል ወይ ሌላ በዚያ የተሾመው ይሰማና ይዳኝ . . .

እንደ አማርኛው ጽሑፍ አንቀጽ 17 ከሆነ የሁለት ቆንስሎች መኖር የታሰበ ይመስላል ።

የመጀመሪያው የእንግሊዝ ቆንሲል ሲሆን በሀበሻ ምድር በብሪታንያ ዜጋ የተፈጸመን ማንኛውም ወንጀል እሚዳኝ ነው ፤ ሁለተኛው ደግሞ የሀበሻ ንጉሠ ነገሥት ቆንሲል ሲሆን በብሪታንያ ዜጎች መሐል ወይም በሀበሻ ዜጎችና በብሪታንያ ዜጎች መካከል ወይም በብሪታንያ ዜጎችና በማንኛውም ሌላ አገር ዜጎች መካከል የሚኖርን ክርክር ወይም ሙግት የሚሰማና የሚወስን ነው ።

---

* መስመር የተጨመረ

ሕጉ እንዳለ በሥራ ላይ ይዋል ቢባል የዳኝነት ሥልጣን ድልድሉ በወንጀልና በፍትሐ ብሔር ነገሮች መካከል ክፍፍል ለማድረግ ታቅዶ የተደረገ ይመስላል ። በዚህም ሁኔታ የብሪታንያ ቆንሲል የመዳኘት ሥልጣን የብሪታንያ ዜጐች ያሉበትን የወንጀል ጉዳዮችን ከመስማትና ከመወሰን ባሻገር ፈቀቅ የሚል አይሆንም ። በፍትሐ ብሔር ነገሮች ላይ ያለውን ሥልጣን በአማርኛው አንቀጽ የተገፈፈው ቆንሲል በእንግሊዝኛው አንቀጽ እንዲኖረው ከታሰበው ሥልጣኑ ጋር ተነጻጽሮ ሲታይ የኰሰሰና የደከመ ሆኖ ይገኛል ።

በዚህ መለያየት ተጠያቂ የሆነው ጀብደኛ ወይም መሠሪ ማን መሆኑ በይፋ አልታወቀም ። እንዲሁም የአተረጓጐም ስህተት ይሁን ፤ የአጻጻፍ ስህተት ወይም ራስ ዓሊን ለማግባባት ሆን ተብሎ የተደረገ አሳቻ ዘዴ ስለመሆን አለመሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ነገር የለም ። ውሉ ስለተፈረመበት ሁኔታ የሚተርከው የፕላውዴንም ጽሑፍ ቢሆን ይህን ችግር በተመለከተ እምብዛም የሚረዳ አይደለም ። ከዚህም በላይ ሁለቱ መንግሥታት ውሉን በተመለከተ ከዚያ ወዲህ በተለዋወጧቸው መልዕክቶቻቸው ላይ የአንቀጾቹን አለመጣጣም አስመልክተው ያነሱት ነገር የለም ።

ሆኖም ግን ልዩነቱ የትርጉም ስህተት ውጤት እንደነበረ ወይም በምንም ዓይነት ፕላውዴን ተቀብሎት የገባ እንዳልነበረ የሚከተሉት ነጥቦች ሊጠቁሙ ይችሉ ይሆናል ።

1\. — በመጀመሪያ ደረጃ ውሉ የተዘጋጀው በእንግሊዝኛ ሲሆን የፕላውዴን ሥልጣንም መሠረታዊ ለውጥ ሳያደርግበት በሀበሻ መሪዎች ውሉን ማስፈረም ነበር ። የአማርኛው አንቀጽ የውል ቃል የተጻፈው ሆን ተብሎ ከሆነ በእርግጥም እላይ ከተገለጸው ሥልጣን ውጭ የተደረገ ነው ።

2\. — የእንግሊዝ ዜጐች ተከራካሪ የሆኑበትን የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን ለመስማትና ለመወሰን ሥልጣን ያለው የሀበሻ ሰው የሀበሻ ንጉሥ ቢሾም የሚቻልና ተቀባይነትም ያለው ነገር ነው ።
ነገር ግን ይህን የመሰለን ሹም ቆንሲል ብሎ መሰየምና " ማንም ቢሆን ከሀበሻ ሹማምንቶች ሳይነጋገሩበት ሳይግባቡበት ሳያስችግሩት ሙግት ሲጀምር ወይ ሲሚገት ወይ ሲጨርስ " የሚል ኀይለ የለሽ ነጻነት በአንድ ዓለም አቀፍ ውል ውስጥ መስጠት እንግዳና ያልተለመደ ጉዳይ ነው ። ውሉ ንጉሡ የውጭ አገር ሰው ለዚህ ቦታ እንዲመድብ ወይም የእንግሊዝን ቆንሲል ለዚህ ሥራ በተጨማሪ እንዲሾመው ስለማያስገድድ የተለየ ሁኔታ ለመገመትም አስቸጋሪ ነው ።

3\. — ራስ አሊ ውሉን እንዲፈርሙ በጣም ከፍተኛ ጥረት ያደረገው ፕላውዴን ውሉን ወደ አማርኛ ያስተረጐመው በራሱ ጸሐፊ ነው ። ውሉን ለራስ አሊ ያስነበበውም በዚሁ በጸሐፊው አማካይነት ነበር ።

በዚህም የተነሳ ውሉን በእንግሊዝኛው በተጻፈበት ሁኔታ ለማቅረብም ሆነ ራስ ዓሊ እንዳለ እንዲቀበሉት ለማግባባት ወይም ለመለመን አጋጣሚው ለፕላውዴን አመቺና ተስማሚ ነበር ።

ሁኔታው እንዲህ የተመቻቸለት ሆኖ እያለ ፕላውዴን በራሱ ነጻ ውሣኔ ከመጀመሪያው የውሉን የአማርኛ አንቀጽ 17 ትርጉም ጸሐፊው እንዲያለዝበውና እንዲያደክመው ሥልጣን በመስጠት ወይም በማዘዝ መደራደሪያውን ያዳከማል ብሎ ማሰብ በጣም ያስቸግራል ።

4. — እንዲሁም የውሉ የአማርኛው አንቀጽ 17 አቀራረጽ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መሐል የተደረሰ መግባባት ውጤት ነው ለማለት ምንም ፍንጭ ወይም መረጃ የለም ። ከአማካሪዎቻቸው ስለ ውሉ ምክር መጠየቃቸው የሚያጠራጥረው ራስ ዓሊ ውሉን ከመጤፍ ስላልቆጠሩት ለመዋዋል የነበራቸው ፍላጎት እጅግ የቀዘቀዘ ነበር ።

በዚህም የተነሳ በውይይቱ ወቅት ትርኪ ምርኪ ነገሮችን እያነሱ ስላስቸገሩ በጸሐፊው የሚነበበውን የውል ቃል ልብ ብለው እንዲያዳምጡ በፕላውዴን መለመን ነበረባቸው ።
ለራስ አሊ ውሉ ከተነበበላቸው በኋላ ፦—
. . . . . . የኔ ማብራሪያና መግለጫ ታክሎበት ሰነዱን ዘለቅነው ከዛም ሰነዱ በያዘው ነገር ምንም ጉዳት እንዳላዩበት ራስ ተናገሩ ። ቀጥሎም ሁለቱን ቅጂዎች በማህተማቸው ካተሙ በኋላ የራሳቸውን ድርሻ ለሚያቀርቡት እንደ ደብተራ ሰጥተው ደብረ ታቦር ወስዶ እንዲቆልፍበት አዘዙ ።
ሲል ፕላውዴን ገልጧል ።

ፕላውዴን ለራስ ዓሊ የገለጠው ስለምን መሆኑን ወይም ገለጣው አንቀጽ 17ን መጨመር አለመጨመሩን ለማወቅ አስቸጋሪ ነው ። የራስ ዓሊን ግድየለሽ አእምሮ እያስጨንቅ እንጂ ራስ ዓሊ ማህተማቸውን ከውሉ ግርጌ ሲያኖሩ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል በተለይ አንቀጽ 17ን በተመለከተ የአእምሮ መገናኘት የነበረ መሆኑን ለማወቅም እንደዚሁ አስቸጋሪ ነው ።

ፕላውዴንን በተመለከተ ግን ማህተም ያረፈበትን የራሱን ድርሻ በጁ ጨብጦ ከራስ ዓሊ የውስጥ ድንኳን ሲወጣ ውሉን በመመሪያው መሰረት በማስፈረሙ ኃላፊነቱን በተሳካ መልክ ከመወጣት ስሜት ጋር መሆኑን መገመት ይቻላል ። የአንቀጽ 17 የውሉ የእንግሊዝኛው ጽሑፍ እንደሚከተለው ተቀምጧል ፦—

> የሐበሻ ንጉሥ ውል ይሠር ፡ በምንም ነገር በግዛት ሐበሻ የእንግሊዝ ዜጐች በማንም ነውር በተከሰሱ ጊዜ በእንግሊዝ ንግሥት ኩንስል ይዳኝ ወይ በሌላ ሹም የእንግሊዝ ንጉሥ በዚያ የሾመው ፥ በማንም ነገር ጠብ ቢነሳ ሙግትም በእንግሊዝ ዜጐች ቢነሳ ወይ በእንግሊዝ ዜጐችና በሐበሻ ንጉሥ ዜጐች ማኽል ወይ በእንግሊዝ ዜጐችና በሌላ አገር ዜጐች መሐል ቢነሳ ፡ በንጉሠ ሐበሻ ግዛት የእንግሊዝ ንግሥት *ኩንስል ወይ ሌላ በዚያ የሾመው ይሰማና ይዳኝ ማንም ማን ቢሆን ከሐበሻ ሹማምንቶች ሳይነጋገሩበት ሳይገቡበት ሳያስቸግሩት ሙግት ሲጀመር ወይ ሲሟገት ወይ ሲጨርስ

በዚህ አንቀጽ መሰረት የብሪታንያ ቆንሲል ወይም ለዚሁ ጉዳይ በብሪታንያ መንግሥት የተሾመ ሌላ የብሪታንያ ባለሥልጣን የሚከተሉትን ለመፈጸም ሥልጣን አለው ።

---

* አማርኛው — የሐበሻ ንጉሥ ይላል ።

1. — በሐበሻ ንጉሥ ግዛት በማናቸውም ክልል ውስጥ አንድ የብሪታንያ ዜጋ ነውር ሰርቶ በተከሰሰ ጊዜ ጉዳዩን መስማትና መወሰን ፤

2.. — በሐበሻ ንጉሥ ግዛት ውስጥ ማናቸውም ጠብ ወይም ሙግት ፣
ሀ/ በእንግሊዝ ዜጐች መካከል ቢነሳ ፤
ለ/ በእንግሊዝ ዜጐችና በሐበሻ ንጉሥ ዜጐች መካከል ቢነሳ ፤
ሐ/ በእንግሊዝ ዜጐችና በማንኛውም ሌላ የውጭ መንግሥት ዜጐች መሐል ቢነሳ መስማትና መወሰን ፤

በዚህ አንቀጽ ውስጥ አንድ ግድፈት አለ ። ይኸውም የብሪታንያ ዜጋ የወንጀል ፈጻሚ በመሆን ፋንታ የወንጀል ሰለባ ሲሆን አቤቱታውን የት እንደሚያቀርብ አንቀጹ ለይቶ አለመናገሩ ነው ። ሁኔታው ከውሉ ዓላማ አኳያ ሲታይ ግድፈቱ የመጣው ካለማስተዋል እንጂ በሐገሪቱ ለነበረው የዳኝነት ሥርዓት ከበሬታ ተብሎ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል ።

ለማንኛውም ቆንሲሉ የእንግሊዝ ዜጐች ተከራካሪ ሆነው በሚቀርቡበት " ጠብ ወይም ሙግት " ሁሉ የተሟላ የዳኝነት ሥልጣን በውሉ የተጐናጸፈ ስለሆነ የአንቀጹ የመጀመሪያው ክፍል ጠባብ አቀራረብ የቆንሲሉን የዳኝነት ሥልጣን ይገድበዋል ለማለት ፈጽሞ የማይቻል ነው ።

በአንቀጽ 17 ለተዘረዘሩ ጉዳዮች የመዳኘት ሥልጣን የተጐናጸፈው የእንግሊዝ ቆንሲል ወይም ሌላ ሹም ከዚሁ ጋር አያይዞ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባውን ሕግ የመወሰን ተጨማሪ ሥልጣን ያለው ይመስላል ። ይህን በተመለከተ ሕጉ ምንም እስካላለ ድረስ የቀረቡለትን ጉዳዮች ሁሉ በራሱ አገር ብሔራዊ ሕግ መሰረት የመወሰን ሥልጣን በዝምታ ሰጥቶታል ማለት ይቻላል ። ይህም በአጭሩ የነበረውን የሀገሬውን ባህል ወይም የሕግ ሥርዐት እንደሌለ መቁጠር ማለት ነው ። የዚህ ዓይነት አሠራር ለብሪታንያ ዜጐች በተለይም የወንጀል ድርጊትን በተመለከተ ለክስ እንዳይጋለጡ በማድረግ ያለው የመከላከል ውጤት ግልጽ ነው ። የአንድ ድርጊት መፈጸም ወይም አለመፈጸም ወንጀል የሚሆነው የሀበሻ ሕግ ወይም ባህል እንዲያ ስለሚያደርገው ሳይሆን የዚያ ዓይነት ተግባር በብሪታንያ የሕግ ሥርዓት ወንጀል ነው ተብሎ በመደንገጉ ብቻ ይሆናል ። የዚህም ግልጽ ውጤት ለቆንሲሉ የዳኝነት ሥልጣን መስጠት ብቻ ሳይሆን የእንግሊዝን ምግባረ ግዕዛት የተለየ ሁኔታ ባለበት አገር ውስጥ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ማድረግንም ይጨምራል ።

ባጭሩ አንድ የብሪታንያ ዜጋ በሀበሻ አገር እየኖረ እንግሊዛዊ በመሆኑ ብቻ በእንግሊዝ ምግባረ ግዕዛት (ሕግ) እንዲተዳደር ተፈቅዶለታል ማለት ነው ። ይህ በመሆኑም ከእንግሊዝ ሕግ ጋር የማይስማማውን ማናቸውንም የሀበሻ ምግባረ ግዕዛት የማክበርም ሆነ የመጠበቅ ግዴታ አይኖርበትም ማለት ነው ። ይህ ሁኔታ አንድን የብሪታንያ ዜጋ የሚያጋጥመውን የፍትሐ ብሔርም ሆነ የወንጀል ሙግት በሀበሻ ሕግ መሰረት እልባት እንዲያገኝ ወይም የሽምግልና ግልግልን በመሳሰሉ የዳበሩ ባህላዊ ዘዴዎች ተጠቅሞ ለመጨረስ የሚገፋፋው አይሆንም ።

ስለ እንግሊዝ ቆንሲል ወይም ሹም የመዳኘት ሥልጣን የሚናገሩት ቀሪዎቹ ሶስት ሁኔታዎች የሚመለከቱት የፍትሐ ብሔር ነገሮችን እንደሆነ በአንቀጹ በኋለኛው ክፍል " ጠብ ወይ ሙግት " በማለት ከተጠቀሱት ቃላት መገመት ይቻላል ። ከነዚህም ውስጥ የመጨረሻዎቹ ሁለቱ የብሪታንያ ዜጐች ያልሆኑ ሰዎችን

መብት ሊነኩ በሚችሉ ክርክሮች ላይ የመፍረድ መብት ለብሪታንያ ቆንሲል ይሰጣሉ ። በነዚህ ጉዳዮች ላይ የእንግሊዝ ቆንሲል የመዳኘት ሥልጣን የሚኖረው ከባለጉዳዮቹ አንዱ የብሪታንያ ዜጋ በመሆኑ ብቻ ነው ። በመሆኑም የሌሎች ባለ ጉዳዮች ዜግነት እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የቀረቡት በከሣሽነት ይሁን ወይም በተከሣሽነት ግምት ውስጥ የሚገባ አይሆንም ።

እንግዲህ ይህ ሁኔታ የእንግሊዝ ዜጋ ያልሆነውን ተሟጋች በአገሩ ሕግ መሠረት ለችግሩ እልባት በመፈለግ ፋንታ ክሱን ለመመሥረት ቆንሲሉ እሚኖርበት ድረስ መሄድ እንዳለበትም ይጠቁማል ። ይህም ብዙ የሀበሻ ባለጉዳዮችን ጉዞው ከሚያስከትለው ወጭ ለመዳን ወይም በባዕድ ዳኛ ፊት ቆሞ መከራከር ከሚፈጥረው ችግር ለማምለጥ በእንግሊዝ ዜጎች ላይ ክስ እንዳይመሰርቱ የመገፋፋት ዝንባሌ ሊኖረው እንደሚችል ይታመናል ።

ቆንሲሉ " ጠብ ወይም ሙግት " ቀርቦለት በሚያከራክርበት ወቅት የራሱን አገር ሕግ ተፈጻሚ እንዳያደርግ ውሉ አሁንም ቢሆን ሥልጣኑን የሚገድብ አንቀጽ አልያዘም ። የሀበሻም ሆኑ የእንግሊዝ ዜጎች ባልሆኑ ሰዎች ላይ ለእንግሊዝ ቆንሲል የመዳኘት ሥልጣን የሚሰጠው የውሉ አንቀጽ የሌላ 3ኛ መንግሥትን ጥቅም የሚነካ በመሆኑ ሁለቱም መንግሥታት ሊደራደሩ የማይችሉበት ነጥብ ነበር ።

ተፈጻሚነት ስለሚኖረው ሕግ የማይናገረው ውል ቆንሲሉ በሚሰጠው ፍርድ ላይ የይግባኝ መብት ስለመኖሩም የሚወስነው ነገር የለም ። ይግባኝ ቢፈቀድ እንኳ ይግባኝ ሰሚው ማን እንደሚሆንም አይገልጽም ። ቆንሲሉ በሥልጣኑ ሥር ያሉ ጉዳዮችን በሙሉ ሰምቶ እንዲወስን ፦—

> ማንም ማን ቢሆን ከሐበሻ ሹማምንቶች ሳይናገሩበት ሳይገቡበት ሳያስቸግሩት ሙግት ሲጀምር ወይ ሲያሚግት ወይ ሲጨርስ

በማለት ውሉ ስለሚደነግግ ፤ የቆንሲሉን ውሳኔ በይግባኝ የሚሰማ አካል ለመፍጠርም ሆነ ጨርሰውንም የይግባኝ መብት እንዲኖር የማድረግ ፍላጎት አልነበረም ለማለት የሚያስችሉ ምክንያቶች አሉ ። በተጨማሪም የአንቀጹ አቀራረብ የቆንሲሉን ሥልጣን ከመዳኘት ክልል አሳልፎ ወደ ፍርድ አፈጻጸም መድረክም ስለሚያሸጋግረው የሥልጣኑ ስፋት አንድና ሁለት የማይባል ነው ።

ቆንስሉ በውሉ አንቀጽ 18 የሚከተለው ተጨማሪ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

> የእንግሊዝ ዜጋ በሐበሻ ግዛት የሞተ እንደሆነ . . .
> የሞተውን ሰው ወረቀቱን ገንዘቡን ይቀበላል ፥ ብድር ቢኖርባቸው ወራሽ ቢኖራቸው ባለዳ ቢኖርባቸው ወስዶ እንዲሰጣቸው የሐበሻ ሹማምንት ሳያስቸግሯቸው ።

እዚህም ላይ በድጋሚ የሟቹ እንግሊዝ ወራሾች ወይም አበዳሪዎች ዜግነት እግምት ውስጥ አልገባም ። የእንግሊዝ ቆንሲል የሕጎች መጋጨትን ሊያስከትሉ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ምናልባትም የራሱን አገር ሕግ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችል ሥልጣን በድጋሚ ተሰጥቶታል ።

በመጨረሻም የዚህ የተዛባ የውል ሁኔታ ጥብቅ አፈጻጸም " የዘለዓለም ወዳጅነት በሁለቱ ነገሥታቶች ማኸል ያቆማል " ተብሎ በአንቀጽ 19 ላይ ተመልክቷል ። ውሉ ለምን ያህል ጊዜ ጸንቶ እንደሚቆይ ፤ ወይም በምን ሁኔታ ማፍረስ

እንደሚቻል በውሉ ላይ የተመለከተ ነገር የለም ። በዚህም የተነሳ ውሉን ቀሪ ለማድረግ ያለው መንገድ የሁለቱን መንግሥታት ስምምነት የሚጠይቅ ይሆናል ። ለዚህም በታላቋ ብሪታንያ በኩል ፈቃድ ላይ መተማመን ግዴታ ይሆናል ። በወቅቱ በነበረው ሁኔታ ደግሞ ያንን ከታላቋ ብሪታንያ መጠበቅ የማይመስል ነገር ነበር ።

ቴዎድሮስና የ1842 ዓ.ም. ውል

ፕላውዴን ይህን የመሰለ የውል ሁኔታ ራስ ዓሊን እንዲቀበሉ ያግባባቸው ያለ ብዙ ችግር ነው ።[17] በ1847 ዓ.ም. አጼ ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት ሲገኙ በ1842 ዓ.ም. የተፈረመውን ውል እንደገና ለመደራደርም ሆነ በሥልጣን የተቀመጡት ንጉሥ እንዲቀበሉት የመጠየቅ ሀሳብ አልነበረውም ። የውሉ ጉዳይ ያለቀ የደቀቀ ስለነበር ቴዎድሮስ ውሉን የመቀበልና የማክበር ግዴታ አለባቸው በማለት ፕላውዴን ያምን ነበር ።

ይህንንም ፕላወደን ለወጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ሰኔ 18 : 1847 ዓ.ም. ከጻፈው ደብዳቤ መረዳት ይቻላል ። አግባብ ያለው የዚያ ደብዳቤ ክፍል እንደሚከተለው ይነበባል ።[18]

> በመሄጃዬ ቀን ዋዜማ ምሽት የመጣሁበትን ዓላማ ለማወቅ ንጉሡ መልእክት ላኩብኝ ፤ እኔም በመንግሥቴ ተልኬ ወይም መንግሥትን ወክዬ አለመምጣቴን ገልጬ ወደ ሀገሬ ስለምሄድ የቆንሲል መሥሪያ ቤት ስለማቋቋምና ባጠቃላይም በሀገሮቻችን መካከል የወዳጅነት ግንኙነት ለመፍጠር ንጉሥ ያላቸውን ሀሳብ ማወቅና ለመንግሥቴም ማሳወቅ እንዳለብኝ አስረድቼ ፡ ከራሴ ዓሊ ጋር ስለተደረገውም ስምምነት ጠቆም አደረግሁ ።

ፕላውዴን በልበ ሙሉነት ለተናገረው ቃል ንጉሡ የሰጡት ምላሽ ሳያስደነግጠው እንዳልቀረ መገመት ይቻላል ።

> “ ራስ አሊ ምን እንደሆኑ ” አሉ ቴዎድሮስ “ የማውቀው ነገር የለም . . . በቀደሙት የሀበሻ ነገሥታት ጊዜም የቆንሲል መሥሪያ ቤቶች ስለመኖራቸው የሰማሁት ነገር የለም ፤ ስለዚህ ይህ ጉዳይ እንዲመከርበት ለአማካሪዎቼና ለሹማምንቶች መቅረብ ያለበት ነው ። ”[19]

እንግዲህ ቴዎድሮስ ስለውሉ ያላቸውን አቋም ባጭሩና በጠራ መልክ የገለጡት በዚህ ሁኔታ ነበር ። መልሳቸውም አዎንታዊና አሉታዊ ነጥቦችን አጣምሮ የያዘ ነው ። በማያውቁትና ተዋዋይ ሆነው ባልፈረሙት ውል አልገደድም ማለታቸው አሉታዊ መከራከሪያቸውን የሚያንጸባርቅ ነው ። በወቅቱ በነበሩት ሁኔታዎች አንጻር በርግጥም አጼ ቴዎድሮስ ውሉን ሳያውቁ መቻላቸው ሊሆን የሚችል ነገር ነው ።[20]

የውሉን መኖር አውቀው ቢሆን እንኳ ኖሮ “ ራስ ዓሊ በፈጸሙት ድርጊት ” መገደድ ስለማይገባቸው ውሉን ለማክበር ዝግጁ አልነበሩም ።

ዓሊን በጦር ኃይል አስወግደው ሥልጣነ መንግሥቱን የተረከቡት ቴዎድሮስ ከሥልጣን የተባረሩት የራስ አሊ ወራሴ መንግሥት ወይም ሕጋዊ ተተኪ እንደ

ሆኑ ተቆጥረው ራስ ዓሊ የገቡትን የውል ግዴታ በሕግም ቢሆን የማክበር ኃላፊነት ጨርሶ ስለሌለባቸው ውሉን አልቀበልም ማለታቸው የተገባና ትክክል ነበር ። ይህ ውል በውርስ ሊተላለፍ አይችልም የሚለው አቋም ቀሪ ቢሆን እንኳ " በቀደሙት የሀበሻ ነገሥታት ጊዜም የቆንሲል መሥሪያ ቤቶች ስለመኖራቸው" ቴዎድሮስ የሚያውቁት ነገር ስለሌለ ውሉን ለመቀበል ፈቃደኛም ዝግጁም አልሆኑም ። ባጭሩ የቆንሲል መሥሪያ ቤት የማቋቋሙን ጥያቄ ቴዎድሮስ ያልተቀበሉት በሀበሻ ታሪክ ውስጥ ያልተመዘገበ " አዲስ " ክስተት ሆኖ ስላገኙት ነው ።

ራስ ዓሊ ባደረጉት ውል አልገደድም በማለትና ከዚያም በፊት በሀበሻ ታሪክ ውስጥ ያልተመዘገበ እንግዳ መሥሪያ ቤት እንዲቋቋም አልፈቅድም ሲሉ ቴዎድሮስ የሰጡት መልስ ፕላውዴንን ዙሪያውን ገደል ስላደረገበት ሀሳቡን ለማጠናከር መፈናፈኛ ሊያገኝ አልቻለም ። ቴዎድሮስ ካነሷቸው ነጥቦች መካከል አንዳንዶቹ ተከታታይ ሁኔታዎችን ጭምር አስቀድመው የሚነኩ ስለነበሩ እንግሊዞች ከዚያ ወዲህ እንኳ የሰነዘሯቸውን ነቀፌታዎች የሚያከሽፉ ነበሩ ። ለምሳሌ መስከረም 25 ቀን 1858 ዓ.ም. አርል ረስል ለኰሎኔል ሰታቶን በጻፈው ደብዳቤ ላይ የሚከተለው ይገኛል[21] ።

> ንጉሡ በ1842 የተፈረመውን ውል አላከብርም ማለት ብቻ ሳይሆን የውሉን መኖር ለመቀበል አሻፈረኝ ብለዋል ። ንጉሡ የውሉን መኖሩ የመቀበል የቅን ልቡና ግዴታ እንዳለባቸውና የማይስማሙበት አንቀጽ ቢኖር ግን የማሻሻያ ሀሳብ ለማቅረብ እንደሚችሉ ለቆንሲል ፕላውዴን በ1850 የእንግሊዝ መንግሥት ገልጦለት ነበር ።

ፕላውዴን ከዚህ ሁለት ዓመት ቀደም ብሎ የንጉሡን መልስ ጠቅሶ ባስተላለፈው ሪፖርት ላይ የገለጠው ሲታይ ከላይ የተሰነዘረውን አስተያየት የሚደግፍ ፍንጭ አይገኝም ። ስለ ውሉ የቴዎድሮስ ተቃውሞ ግልጽና የታወቀ ነበር ። እንዲህ በማለትም እንደመስተዋት አጥርተው አስቀምጠውታል ።

> በታሪካችን ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ነገር ስለሌለ የቆንሲል መሥሪያ ቤት እንዲቋቋም አልፈቅድም ።

የዚህ ግልጥ አቋም መልእክት በጥራት የገባው ፕላውዴን " ቴዎድሮስ ለቆንሲሉ የመዳኘት መብት የሚሰጠው አንቀጽ ሥልጣኔን የሚነካ ነው የሚል ሥጋት አሳድሮባቸዋል " በማለት ሰኔ 18 ፤ 1847 ዓ.ም. ለውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ባስተላለፈው ሪፖርት ላይ ገልጦታል ።

አጼ ቴዎድሮስ ውሉን እንዲቀበሉት ለማግባባት ከ1847 ዓ.ም. ጀምሮ ያልተሞከረ ድርጊት የለም ። ጆን ቤልና በወቅቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ የነበሩት አቡነ ሰላማም[22] በአማላጅነት ተልከዋል ። በንጉሡና በፕላውዴን መካከልም በተካሄደው ቀጥታ ውይይት አማካይነት ንጉሡን ለማግባባት ተሞክሯል ። ሌላው ቀርቶ ቴዎድሮስ ውሉን ቢቀበሉ ተጨማሪ ግዛት እንደሚሰጣቸው ተገልጦላቸዋል ።

ስለዚህም ፕላውዴን እንዲህ ይላል ።

> ውሉን ለመቀበል ከፈቀዱ የባህሩ ጠረፍና ምጽዋ ሊሰጣቸው እንደሚችል ለመጠቆም ደፍሬአለሁ ።

ይህ ሁሉ የተደረገው በእንግሊዝ ተረቅቆ የቀረበውን የ1842 ዓ.ም. ውል ያለምንም ለውጥ አጼ ቴዎድሮስ እንዲቀበሉት ለማግባባት ነው ።

ይሁን እንጂ የቴዎድሮስ አቋም በጽኑ ዓላማ ላይ የተመሠረተ ነበር ። ከታላቋ ብሪታንያ ጋር ለመወዳጀት ፈቃደኛም ዝግጁም ነበሩ ። በዚህም የተነሳ ወደ አውሮፓ ኃያላን መንግሥታት አምባሳደሮቻቸውን ለመላክ ሀሳብ አቅርበው ነበር ። ሆኖም ከዚሁ ጋር ያቀረቡት አንድ ዋና ሁኔታ " ከነዚህ መንግሥታት ጋር መወዳጀት የሚገባን በእኩልነት ደረጃ ነው "[23] የሚል ነበር ።

ሥልጣን እንደጨበጡ ከወሰድዋቸው እርምጃዎች አኳያ ነገሩ ሲታይ ያነሱት የዕኩልነት ጥያቄ ከዋልተር ፕላውዴን ሳይቀር ድጋፍ አስገኝቶላቸዋል። ። ዋልተር ፕላውዴን ለውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ሲጽፍ እንዲህ ብሏል[24]።

> ነፍሰ ገዳዮችን ለሚች ወገኖች አሳልፎ የመስጠትን የጭካኔ አሠራር አስወግደው የሞትም ሆነ የመሰየፍ ቅጣት በአደባባይ እንዲፈጸምባቸው አጥፊዎች ለመንግሥት ሹሞች እንዲሰጡ አድርገዋል ።
>
> በየአውራጃው የሚገኙ ወታደሮች ሁሉ የመዳኘትና የመቅጣት ሥልጣንን ሳይጨምር ከፍተኛ ማዕረግ በሰጧቸው ታማኝ ተከታዮቻቸው ሥር እንዲሆን አድርገዋል ።
>
> በዚህም በንጉሣቸው ሳይሆን በዘራቸው የሚኩራሩትን የፊውዳል ባላባቶች አስወግደው ጀኔራሎችን ተክተዋል ። ንግድን በተመለከተ በየቦታው ይደረግ የነበረውን አሰልቺ ክፍያ አስወግደው በግዛታቸው ውስጥ በሶስት ሥፍራ ብቻ ግብር እንዲከፈል ወስነዋል ። እነዚህ ጥረቶች ሁሉ ባንድ ጊዜ ያለህጸጽ ተፈጻሚ ይሆናሉ ማለት ያስቸግራል . . . ሰይፍንና ጦርን ወደ ማረሻና ማጭድ እለውጣለሁ ፤ አራሹ በሬም ከተመሰገነ ሰንጋ ፈረስ የበለጠ ዋጋ እንዲያወጣ አደርጋለሁ ብለዋል ።

በሌላ በማንም ሳይሆን በራሱ በእንግሊዝ ቆንሲል የተሰጠው ይህ ምስክርነት እንግሊዝ በሀበሻ ምድር ዜጐቿን ለመዳኘት እንድትችል ያቀረበችውን ጥያቄ የሚያዳክም ነው ።

ምስክርነቱ በሀበሻ ለሚኖሩ ባዕዳን የተለየ ጥበቃ የማያስፈልጋቸው መሆኑን ስለሚጠቁም እንደዚያ ያለውን ስምምነት ጠቀሜታ ቢስ ያደርገዋል ። ይህም ባዕዳን በሙሉ እንግሊዞችንም ጨምሮ ሀበሻ ምድር ከገቡ በኋላ በወቅቱ በሀገሪቱ በነበረው ምግባረ ግዕዛት እንዲተዳደሩና እንዲዳኙ ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው ። እንደሚገመተው ቴዎድሮስ ለራሳቸው ጀኔራሎች እንኳ የነፈጉትን የዳኝነት ሥልጣን ለባዕድ ቆንሲል አሳልፈው ለመስጠት ፈጽሞ ዝግጁ አልነበሩም ።

የቆንሲሉን የዳኝነት ሥልጣን አለመቀበላቸው ከውጭ መንግሥታት ጋር መገናኘት ያለብን በእኩልነት ደረጃ ነው ብለው ከያዙት አቋም ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው ። ከእኩልነት ያነሰ ምንም ነገር እንደማይቀበሉ ደጋግመው አስገንዝበዋል ። ይህን በተመለከተ ፕላውዴን ለውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበር ።

> ሉዐላዊ መብታቸውን የሚቀናቀን መስሎ በሚታያቸው በማና ቸውም ነገር ላይ እንደሚገመቱው ሁሉ ቀናኢነታቸው እጅግ ከፍተኛ ነው ።

ይህም የፕላውዴን አስተያየት ቴዎድሮስ ባንድ አጋጣሚ ሥልጣንን በተመለከተ በመዘበት መልክ ከእግዜር ጋር አድርገናል ስላሉት ውል በተናገሩት ቃል የተደገፈ ነው ። [25]

> እግዚአብሔር መሬት ወርዶ እንዳይቀባኝ እኔም ሰማይ ወጥቼ እንዳልወጋው ተስማምተን ውል ገብቻለሁ ።

ለእንግሊዝ ቆንሲል የዳኝነት ሥልጣን እንዲሰጥ የቀረበው ጥያቄ ንጉሡ ሉዐላዊ መብታቸውን ለእግዚአብሔር ጭምር እንኳ ሳያጋሩ ለመያዝ ካላቸው ቊርጠኝነት ጋር የማይስማማ መሆኑ ፍጹም ግሃድ ነው ።

እንደዚሁም ይህ ስምምነት የማታ ማታ የሚያስከትለው ዞማና ከዚሁ ጋር በማስታከክ ሊፈጸሙ የሚችሉ ደባዎችና መሰሪ ድርጊቶች ከንጉሡ የተሰወሩ አልነበሩም ። ስለ ኢትዮጵያ ሰፊ ዕውቀት የነበረው መሆኑ የሚነገርለት ቻርላስ ቤክ በ1858 ዓ. ም. መጀመሪያ ላይ የንጉሡን እንቢታ ደግፎ እንደሚከተለው ጽፎአል[26]።

> ግብጽንና ቅድስት ሀገርን ጐብኝተው ከተመለሱ የራሳቸው ሀገር ዜጐችና ከባዕዳን ተጓዦችም ከሰሙት የአውሮፓ መንግሥታት ቆንሲሎች በነዚያ አገሮች ስለነበራቸው ከፍተኛ ሥልጣንና ይህም በአገሮቹ ውስጥ ችግር ስለማስከተሉ በሰፊው የሚያውቁ ስለሆነ በቱርክ ግዛት እንዳለው ዓይነት <u>በመንግሥት ውስጥ መንግሥት</u> እንዳይቋቋም ቊርጠኛ አቋም በመያዛቸው ማንም ሊፈርድባቸው አይገባም ።

የቤክን ዘገባ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በመስከረም 1856 በሀበሻ የፈረንሳይ ቆንሲል የነበረውን ኤም ሌዣንን ሲያስወጡ ከተናገሩትና በራሱ በቆንሲሉ እን ደበት ከተዘገበው መጥቀሱ ይበቃል ። [27]

> የአውሮፓ መንግሥታት የምሥራቅ አገሮችን መያዝ ሲፈልጉ የሚጠቀሙበትን ዘዴ አውቀዋለሁ ፤ መጀመሪያ ሚሲዮናውያንን ይልካሉ ፡ ሚሲዮናውያንን ለመደገፍ ቆንሲሎችን ያስከትላሉ ፤ ቆንሲሎችን ለመጠበቅ ደግሞ ለጥቀው ወታደሮች ይገባሉ ። እኔ በዚህ ዓይነት የምደለል የሂንዱስታን ራጃ (ንጉሥ) አይደለሁም ፤ ውዬ ሳላድር ከጦሩ ጋር ሙፋለምን እመርጣለሁ ፤

ይህ የሆነው በ1852 ዓ.ም. ከፕላውዴን ኢሳዛኝ ሞት በኋላ ሶስት ዓመት ቆይቶ ነው ። ፕላውዴን * የሞተው አጼ ቴዎድሮስን የሚያጠግብ የውል ሀሳብ ማመንጨት አቅቶት በምጽዋ በኩል አድርጐ ወደ እንግሊዝ አገር ለመቀጠል በመጓዝ ላይ እንዳለ ነበር ። ፕላውዴን በአምስት ዓመት ቆይታ ቆንሲልነቱን ቴዎድሮስ እንዲቀበሉት ማድረግ ቀርቶ በ1842 ዓ.ም. በተፈረመው ውል ላይ

* ፕላውዴን የተቀበረው በጐንደር ክፍለ ሀገር በግምጃ ቤት ማርያም ቤተክርስቲያን ሲሆን አጽሙም እስከ ዛሬ ድረስ በዚያው አርፎ ይገኛል ።

የተመለከቱትን የንግድና የዳኝነት መብቶች እንኳ ለሀገሩ ማስከበር ተስኖት ስለ ነበረ ጉዞውን የጀመረው ከመከፋት ጋር መሆኑን መጠራጠር አይቻልም ።

በአበሻና እንግሊዝ አዲስ ውል ድርድር

ፕላውዴንን የተኩው ካፒቴን ቻርለስ ዱንካን ካሜሮን ሲሆን "በሀበሻ አገር የግርማዊት ንግሥት ቆንሲል" ሆኖ መሾሙም ሰኔ 17 ፡ 1852 በለንደን ከተማ ይፋ ሆኗል ። አዲሱ ቆንሲል የካቲት 13 ፡ 1854 አርል ረስል ለቴዎድሮስ የጻፈውን የመተዋወቂያ ደብዳቤ ይዞ ወደ ምድረ ሀበሻ ጉዞውን ጀምሯል ። አቅራቢው የሚቺ የዋልተር ፕላውዴን ተተኪ መሆኑን ከሚናገር በቀር ስለአከራካሪው ውል ደብዳቤው የያዘው አንደም ነገር አልነበረም [28] ።

አዲሱ ቆንሲል ከርሱ በፊት የነበረው ቆንሲል ካሳረፈበት ሥፍራ ጀምሮ ሥራውን መቀጠል የነበረበት ቢሆንም እንግሊዞች ወደ በስተኋላ ኢትዮጵያን በተመለከተ ያሳዩት የፖሊሲ ማፈግፈግ በጉዳዩ ላይ ውይይቱን ባዲስ መንፈስና በሙሉ ልብ ለመቀስቀስ ካሜሩን ባደረገው ጥረት ውስጥ የተወሳሰቡ ሁኔታዎች ሳያጋጥሙት አልቀረም ። ወዲያውኑ በጥቅምት 1855 ዓ.ም. ጐጃም ላይ እንዳለ አንድ ያላሰበው ዕድል ካሜሮንን አጋጠመው ። ይኸውም ከአጼ ቴዎድሮስ የተላከ ደብዳቤ ሲሆን ፍሬ ሀሳቡም ባስቸኳይ ወደ ምጽዋ ወርዶ ንጉሡ ወደ እንግሊዝ አገር የሚልኳቸውን " መልእክተኞችና አምባሳደሮች ማሳለፍ ይችሉ ወይም አይችሉ " እንደሆነ አጣርቶ እንዲገለጥላቸው ካሜሮንን የሚያሳስብ ነበር ። ካሜሮንም ጊዜ ሳይፈጅ ወዲያውኑ ጥቅምት 19 ፡ 1855 ዓ.ም. ጐጃም ሆኖ በጻፈው ደብዳቤ መልሱን ሰጠ ። ከአሥራ ሶስት ዓመት በፊት ተፈርሞ ግዑዝ ወረቀት ሆኖ የቆየውን ውልም ጉዳይ ለመቀስቀስ ካሜሮን በዚያ አጋጣሚ ሊጠቀም ችሏል ።

ካሜሮን ያቀረበው አዲስ ሀሳብ ከቀድሞው ለየት ያለና ውሉ እንዲጸድቅ የሚጠይቅ ሳይሆን በ1842 ዓ.ም. የተደረገውን ውል ሀ ብሎ ለመደራደር የሚያሳስብ ነበር ።

አግባብ ያለው የዚያ ደብዳቤ ክፍል በሩ ባለ ሁኔታ እንደሚከተለው ተጠቅሷል[29] ።

> ለግርማዊነትዎ ስለአምባሲው ያለኝን ሀሳብ ከገለጥሁ በኋላ . . . . ላሳስብዎ የምፈልገው አንድ ነጥብ አለኝ ፤ ይውኸም ግርማዊነትዎ በእኔ እዚህ መገኘት አጋጣሚ በመጠቀም ለኛ ንግሥት የሚቀርብ አንድ የውል ረቂቅ እንዲዘጋጅ የሚስማሙ መሆንዎን ነው ። የግርማዊነትዎ መልካም ፈቃድ ቢሆን በረቂቁ ውል ላይ በጊዜያዊነት ብንፈራረምበት ስለሁኔታው እኔም ለመንግሥቴ አስቀድሜ ለመግለጥ የምችል ሲሆን በጊዜያዊነት የተፈረመው ውል ከአምባሳደርዎ ጋር ሊላክ የሚችል ነው ።
>
> በራስ ዓሊ አማካይነት ከቀድሞው ንጉሥ ጋር የተደረገው የውል ቅጂ በእጄ ስለሚገኝ የግርማዊነትዎ መልካም ፈቃድ ቢሆን ሰነዱ ለአዲሱ ውል መነሻ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ነው ። ሰነዱን አንዳንድ ለውጦች አክየበት ግርማዊነትዎ እንዲያየው ልኬዋለሁ ። ፈጥኘ ላሳስብ የምፈልገው ግን ከሚስተር ፕላውዴን ጋር ያልተግባባችሁባቸው ነጥቦች የሚከተሉት መሆናቸውን ነው ።

1. ቆንሲል እንዲኖር መስማማት ፤
2. ቆንሲሉ ተቀባይነት ካገኘ ከቀድሞው ንጉሥ ጋር በተደረገው ውል መሰረት የዳኝነት ሥልጣን ለቆንሲሉ ይሰጥ እንደሆን ፤

ስለመጀመሪያው ግርማዊነትዎን ለመጠየቅ የምፈልገው ባጠቃላይ በወዳጅነትና በእስታራቂነት ያገለገለው በተለይም ለግብጾች ወረራ ለተጋለጡት ያልታደሉ የሀበሻ ነገዶች ተላ ከለላ የነበረው የፕላውዴን እዚህ መኖር ጠቀሜታ አልነበረውም ወይ በማለት ነው ? በተጨማሪስ ግርማዊነትዎ ብቸኛ የአገሪቱ መሪ እንዲሆኑ ፍላጐቱን በቃልና በተግባር ሳይገልጥ ቀርቷል ? በመጨረሻም የሀበሻን ጥቅም ክብርና ነጻነት የሚጻረር አዝማሚያ ያሳየበት ወቅት ነበር ?

የእንግሊዝ የቴክኒክ ሰዎችን ለማስመጣት ግርማዊነትዎ ፍላጐት እንዳለው ሰምቻለሁ ፤ ሆኖም እነዚህ ሰዎች ደህንነታቸውን የሚጠብቅ ሹም በልዩ መልዕክተኛም ይሁን በቆንሲል ደረጃ ከሌለ እዚሁ መኖር አይችሉም ።

ቆንሲሉ የራሱን ሰንደቅ ዓላማ የሚያውለበልብ ስለመሆኑ ይህ ፈጽሞ ችግር የሚፈጥር አይደለም ። ሕዝብዎ ባልሆነ አቅጣጫ ሊረዳው ይችላል ማለትን ስለ ሰማሁ መንግሥቴም ቢሆን የሚፈልገው አይሆንም ።

የቆንሲሉን የዳኝነት ሥልጣን በተመለከተ ነገሩ ያለው በእኛ እጅ ሳይሆን በእርስዎ እጅ ነው ። እንግሊዝ የምትፈልገው ሌላ ሳይሆን ዜጐቿ ፍትህና ያልተዛባ አስተዳደር እንዲያገኙ ብቻ ነው ።

ከግርማዊነትዎ ለመንግሥታችን የመንግሥትዎ አቋም ነው ብዬ የማምን በትን ቢገልጡ ፤ ይኸውም የተለየ የዳኝነት ሥልጣን ለመስጠት የማይቻልና ሕጉ ቀና በሆነበት በሀበሻ አገርም ይህን ማድረግ የማያስፈልግ መሆኑን ቢያስረዱ ለአሁኑ ይህ የሚበቃ ይመስለኛል ።

የጥቂት ሰዓቶች ንግግር ችግሩን ከሁለቱ ባንዱ መንገድ ለመፍታት የሚያስ ችል ይመስለኛል ።

ከዚህ በኋላ ጥያቄው ንጉሡ በ1842 ዓ.ም. በእንግሊዝና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገውን ውል መቀበል አለመቀበል ሳይሆን ከታላቋ ብሪታንያ ጋር አዲስ ውል ለመዋዋል ፈቃደኛ መሆን አለመሆናቸው ነበር ። ለአዲሱ ድርድርም በቅድመ ሁኔታነት የቀረበ ነገር አልነበረም ። አዲስ ውል ለመደራደርም በቀድሞው ውል እንደሚገደዱ ለማመልከት የተጠቀሰ አንቀጽም አልነበረም ። እንዲያውም የቀረበው ሀሳብ “ የግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ ቢሆን ” የቀድሞው ውል ማሻሻያ ታክሎበት ለአዲሱ ውል በመነሻነት እንዲረዳ የሚያሳስብ ነበር ።

በዚህም የተነሳ ቆንሲሉ ያቀረበው የውል ሃሳብ እንግሊዝና ኢትዮጵያ በ1842 ከተፈራረሙት ውል ጋር ያልተያያዘ ራሱን የቻለ አዲስ ሀሳብ ነበር ። ካሜሮን አዲስ የውል ሃሳብ ማቅረቡ ውስጥ ውስጡን የቀድሞው ውል በንጉሡ ላይ ምንም የሕግ ግዴታ የማይጥል መሆኑንም መቀበሉን ያመለክታል ። ይህም ቆንሲሉ የሚወክለውን መንግሥት የቀድሞው የውል አቋም ያላላ ብቻ ሳይሆን ለቴዎድሮስም ከፍተኛ ድል ያጐናጸፈ ሁኔታ ነበር ። ሆኖም የክስተቶች ሂደት አዲሱ ጥረት ወደ ሰመረ ውጤት እንዲዘልቅ የሚረዳ አልሆኑም ።

እንግሊዝና ፈረንሳይ በክሪሚያ ጦርነት ክርስቲያን በሆነችው ሩሲያ ላይ አብረው እስላም የሆነችውን ቱርክን መርዳታቸው ቴዎድሮስ ከቱርክ ጋር ለነበ ራቸው አለመግባባት እነዚህ ሁለት ክርስቲያናት ኃያላን የአውሮፓ መንግሥ ታት ከጐኔ ይቆማሉ የሚል እምነታቸውን ጥያቄ ላይ ጥሎት ነበር ። ከዚያም ወዲህ በተከታታይ የተከሰቱ ሁኔታዎች ቴዎድሮስ በነዚህ መንግሥታት ላይ እም ነት እንዲያሳድሩ የሚረዱ አልነበሩም ። እንዲያውም ከ1856 በኋላ የእንግሊዝ ፖሊሲ ለኢትዮጵያ ኪሣራ ግብጽንና ቱርክን ለመጥቀም መዝመሙን የሚጠ ቁሙ ብዙ ምልክቶች ነበሩ ።

ይህም የዋለለ የእንግሊዝ የውጭ ፖሊሲ ከኢትዮጵያ ጋር የውል ግንኙነት ጨርሶ መመሥረት ለምን እንዳስፈለገ የእንግሊዝ ሹማምንቶች ሳይቀሩ ጥያቄ እንዲያነሱ አድርጓቸው ነበር ።

ሁኔታዎች በመዋለል ላይ በነበሩት በዚያ ያልታደለ ወቅት ነበር ቴዎድ ሮስ በካሜሮን በኩል ደብዳቤአቸውን ለእንግሊዝ ንግሥት የላኩት[30] ። ቆን ሲሉ የንጉሡን ደብዳቤ በኤደን ለንግሥቲቱ ልኮ በ1855 መጀመሪያ ላይ በሰሜን ኢትዮጵያና በግብጽ ግዛት ተዘዋውሮ ጉብኝት ለማድረግ ረጅም ጉዞውን ጀመረ ። ከጉዞው ሲመለስም ወደ ጐበኘው የኢትዮጵያ ጠረፍ አካባቢ የግብጽ ጦር የመ ገሰገሱ ጭምጭምታ በሰፊው በመናፈስ ላይ ነበር ።

ሆኖም ከተላከ ዘጠኝ ወሮች ያህል ቢያልፉትም ቴዎድሮስ በቆንሲል ካሜ ሮን በኩል ለንግሥቲቱ ለላኩት መልዕክት የመጣ መልስ አልነበረም ። ለቴዎ ድሮስም ሆነ ለካሜሮን አይታወቅ እንጂ እንግሊዝ ደብዳቤውን ችላ ለማለትና እንዲያውም መልስ ላለመስጠት ወስና ነበር[31] ።

በሐምሌ 1855 ዓ.ም. አካባቢ ካሜሮን ከጉብኝቱ ሲመለስ የመጠራጠሩና ክብራቸውም የመነካቱ ጉዳይ ለንጉሡ ከፉኛ ተሰምቷቸው ነበር ። በስድብ ላይ ቁስል (በትር) እንደማከል ያህል ካሜሮን ከውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በተላከ ለት መመሪያ መነሻነት ወደ ምጽዋ ለመውረድ ይችል ዘንድ ንጉሡ እንዲያሰና ብቱት ጥያቄውን ውጥረት በተሞላበት በዚያ ወቅት አቀረበ ። በዚያ ወቅት ነበር ቴዎድሮስ በሚቀጥሉት ዓይነት ጥያቄዎች ካሜሮንን ያጣደፉት[32] ።

— ከሣሙኤል[33] ጋር በገለስ* ላይ ከተለያያችሁ በኋላ የት ነበርክ ?

— ከሱዳን ዳርቻ አውራጃዎች ፤

— ለምን ?

— ስለ ጥጥ ንግድ እንዲሁም ሌሎችን ጉዳዮችን ለማየት ፤

— እዚያ ማን ሂድ አለህ ?

— የእንግሊዝ መንግሥት ፤

— ከእንግሊዝ መንግሥት ለደብዳቤዩ መልስ አመጣህልኝ ?

— አላመጣሁም ፤

— ለምን አላመጣህም ?

---

* የዛሬው ከረን አካባቢ

— ምክንያቱም ከእንግሊዝ መንግሥት ያንን በተመለከተ የተላከልኝ ነገር ባለመኖሩ ፤

— አሁን ታዲያ ምን ልትሆን ወደኔ መጣህ ?

— ወደ ምጽዋ ለመመለስ ፈቃድ ልጠይቅ ፤

— ለምን ?

— በመንግሥቴ ስለታዘዝኩኝ ፤

— እና ያንተ ንግሥት ጠላቶቼን ቱርኮችን ሂደህ እንድትጎበኝና ወደ ምጽዋ እንድትመለስ ትእዛዝ ይሰጡሃል ለኔ ደብዳቤ ግን የጨዋ መልስ መላክ አይችሉም ። መልስ እስካገኝ ከዚህ አትሄድም ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ንጉሡ ሀገሪቱን አንድ ለማድረግ እና የአስተዳደር ማሻ ሻያዎችን ለማስገባት የሚያደርጉት ጥረት ከግዛታቸው በአብዛኛው ክፍል ሁከትና ጦርነት ቀስቅሶ ነበር ። እነዚህ ሁሉ ባንድነት ተነባብረው ንጉሡን ሰላበሳ ጨዋቸው የኋላ ኋላ ወደ ክፉ ውጤት ያመሩ አንዳንድ ርምጃዎችን ለመውሰድ በቅተዋል ። በዚህ ረገድ ንጉሡ የወሰዱት አደገኛ ርምጃ ካሜሮንን ጨምሮ የውጭ አገር ዜጎች በሙሉ በታጋችነት እንዲያዙ ያስተላለፉት ትእዛዝ ነበር ። ቆንሲል ካሜሮን ከግብጽ ጋር ተመሳጥሯል ፤ ለንጉሡም ደብዳቤ ከንግሥቲቱ መልስ ሳያመጣ ቀርቷል በሚሉ ወንጀሎች ተይዞ ታህሣሥ 25 ቀን 1856 ዓ.ም. በእግረሙቅ ታስሯል ።

ከዚያ በኋላ አሳሳቢው ጥያቄ እንደገና ተለውጦ አዲስ ውል መዋዋል ሳይ ሆን ታጋቾችን ማስለቀቅ ሆኗል ።

በራሷ ጥፋት የተፈጠረውን ያንን ችግር ለማስወገድ ታላቋ ብሪታንያ ብዙ ጥረቶችን አድርጋለች ። ላለፈ ጥፋት ንስሐ እንደመግባት ያህል ንግሥቲቱ ለቴዎድሮስ ሁለት ደብዳቤዎችን ጽፈዋል ። ታጋቾችን የሚያስለቅቅ ውል ለመዋዋል በሆርሙዝ ራስም የሚመራ ሁለት አባላት የሚገኙበት የመልዕክተኞች ቡድን ተልኳል ። ቴዎድሮስ ታጋቾችን ለመልቀቅ ቢስማሙ አዲስ ውል ከቴዎድሮስ ጋር ለመዋዋል ታላቋ ብሪታንያ ፈቃደኛ መሆኗን ገልጣለች ። ነገር ግን እንግሊዝ ያሳየችው የአቋም ማላላት ዘግይቶ በመምጣቱ ይሆን ፤ ወይም እስከሚፈልጉት ድረስ አለመሄድ የአጼ ቴዎድሮስን የጠነከረ አቋም ሊያስለውጥ አልቻለም ።

በዚህም የተነሳ ራሳምና ጓደኞቹ ሳይቀሩ እንዲያስፈቱ የተላኩትን እሥረኞች ዕድል መቋደስ እጣ ፋንታቸው ሆነ ። የሚያስገርመው ቴዎድሮስ ባንድ አጋጣሚ ታጋቾች ካሜሮንም ጭምር ለፈጸሙት ወንጀል ተከስሰው በፍትሐ ነገሥቱ ቃል መሰረት ፍርድ ይሰጥባቸዋል በማለት መግለጣቸው ነው ። [34] እንግዲህ የእንግሊዝን ዜጎች ከሀበሻ ሕግና የዳኝነት ሥርዓት ውጭ እንዲደረግ ታስቦ የተረቀቀው ውል ከሀበሻ ሕግ በላይ ነው የተባለውን ቆንሲል እንኳ ማዳን ሳይችል ቀርቷል*። በመሆኑም ካሜሮን ወደ ሀገሩ ያዘገመው በቆንሲልነቱ የሚገባውን ክብር ማግኘት ቀርቶ በ1842 ዓ.ም. በተደረገው ውል ላይ የተመለከቱትን የንግድና የዳኝነት ሥልጣን ለሀገሩ ማስከበር ተስኖት ስለነበር የአርሱም ተልዕኮ ከፕላውዴን ባልተሻለ ሁኔታ የተቀጣ አልነበረም ።

* የውሉን አንቀጽ 3 ይመለከቷል ።

እንደእውነቱ ከሆነ ታላቋ ብሪታንያ ታጋቾችን በማስመልከት ለቴዎድሮስ ባስተላለፈችው መልዕክት ላይ በ1842 ዓ.ም. የተደረገውን ውል አንቀጾች ተጠቃሽ አላደረገችም ። ቆንሲሉንና ፤ የእንግሊዝን ዜጎች በታጋችነት መያዝ የውሉን አንቀጽ በግልጽ መጣስ ስለመሆኑ እንግሊዞች ለቴዎድሮስ ለመግለጥ አልሞከሩም ። ታጋቾቹን ለማስለቀቅ በመጨረሻም የወሰዱትን ርምጃ ተገቢነት ለማሳየት ውሉን በድጋፍነት አልጠቀሱም ። ንግሥቲቱ ለቴዎድሮስ የላኩዋቸው ሁለት ደብዳቤዎችም ስለውሉ በግልጽ የሚያነሱት ነገር የለም ። በማማለድ መንፈስ የተጻፈው የንግሥቲቱ የመጀመሪያ ደብዳቤ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ወዳጅነት ሲሉ ታጋቾቹን እንዲለቁ የሚማጸን ነው ።

አግባብ ያለው የደብዳቤው ክፍልም እንዲህ ይላል ። [35] ግርማዊነትዎ በሐቅ የኛ ወዳጅ ስለመሆንዎ እና በመካከላችንም ያለው ወዳጅነትና መተሰብለዘለቄታው ጸንቶ እንዲቆይ የሚሹ መሆንዎን አገልጋዮችንን ካሜሮንን . . ከቤተ መንግሥትዎ እንዲሰናበት ከማድረግ የተሻለ ማስረጃ ሊሰጡ አይችሉም ።

መስከረም 24 ፡ 1859 ዓ.ም. የንግሥቲቱ ሁለተኛውና የመጨረሻ ደብዳቤ ሲጻፍ የነገሮች ሂደት ወደ ባሰ አዘቅት አሽቆልቁሎ ነበር ።

በዚህም የተነሳ ቴዎድሮስ ታጋቾችን ለመፍታት የገቡትን ቃል ሁሉ ችላ ብለው የውጭ አገር ዜጐች በሙሉ ራሳምና ጓደኞቹ ጭምር ተይዘው እንዲታሰሩ አዘዙ ። ንግሥቲቱ በበኩላቸው ለጥያቄአቸው ሕጋዊና ሥነ ምግባራዊ ምክንያቶችን ጠቅሰው እሥረኞቹ እንዲለቀቁ አሳስበዋል ። ማግባባትና ከበሬታን የተላበሰ ወቀሳን አጣምሮ የያዘው የዚያ ደብዳቤ ቃል በከፊል ሲታይ እንደሚከተለው ነው ። [36]

> ነገሥታት የገቡትን ቃል በጥንቃቄ መጠበቅ ያለባቸው መሆኑን ግርማዊነትዎ ልብ ሊያደርገው ይገባል ፤ እንደራሳም ያሉ አምባሳደሮች ሰውነትና የተከታዮቻቸውም ጭምር ሰልጥነናል በሚሉ አገሮች ሁሉ የማይደፈር ነው ፤ በነገሥታት መካከል ያለዎትን የክብር ሥፍራ ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆንዎን ለዓለም እንዲያሳዩ ለግርማዊነትዎ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን ።

የፖለቲካ ሰዎች ችላ ያሉት ውል በጦር መኮንኖችም ቢሆን ነፍስ ሊዘራ አልቻለም ። ናፒር " ይድረስ ለቴዎድሮስ ንጉሠ ሀባሻ " በማለት አስቀድሞ በጻፈው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤውም ሆነ " ለሀበሻ ገዢዎች ፤ ለአድባራት አለቆች ፤ ለሃይማኖት መሪዎችና ለሀበሻ ሕዝብ " [37] በማለት ባስነገረው አዋጅ ስለ ውሉ የጠቀሰው አንድም ነገር የለም ።

የታጋቶቹ ጉዳይ ሚያዝያ 2 ቀን 1860 ዓ.ም. በቴዎድሮስ ወታደሮችና በጀኔራል ናፒር መሪነት በዘመተው ወራሪ የእንግሊዝ ጦር መካከል በተደረገው ዝነኛው የመቅደላ ጦርነት* እልባት አግኝቷል ። የናፒር ዘመቻ የክስተቶችን ሂደት ተከትሎ ሊመጣ የሚችል ጉዳይ በመሆኑ ቴዎድሮስ ያልጠበቁት እንግዳ ነገር ሊሆንባቸው የማይችል ነው ።

---

* ፊልድ ማርሻል ሮበርት ናፒር ስለክብሩ በሎንደን ኩዊንስ ጌት የመታሰቢያ ሐውልት ቆሞለታል ። ከግርጌውም " የመቅደላው ሎርድ ናፒር " ተብሎ ተጽፎበታል ።

በወቅቱ የቴዎድሮስ ኃይልም ሆነ የውጊያ ብቃት የሚገኘው እጅግ በተዳ
ከመ ሁኔታ ነበር ። የነበራቸው ኃይል በቁጥርም ሆነ በጥራት ከቦምቤይ ተነስቶ ረጅ
ሙን መንገድ ተጉዞ ለውጊያ ታጥቆ ከዘመተው ወራሪ ጦር ጋር ሲነጻጸር ቁጥር
ሊገባ ፈጽሞ የማይችል ነው ። በነገሮች መጫን በዚህ ዓይነት ውጥረት ላይ ይገኙ
የነበሩት ቴዎድሮስ ያላቸው ምርጫ ከናፒር ሠራዊት ጋር በጦር ሜዳ መገናኘት
ወይም ከናፒር ጋር ተገናኝቶ ጦርነቱን ማስቀረት ብቻ ነበር ። ከነዚህም የመጀመ
ሪያውን ምርጫቸው በማድረግ ተጽእኖ ባልተለየው ሰላማዊ መንገድ ቀስ በቀስ
አገርንና ራስን አሳልፎ ከመስጠት ይልቅ "በቀጥታ ከጦሩ ጋር መፋለምን" የሚ
መርጡ መሆናቸውን በተግባር አሳይተዋል [38] ።

እንደሚገመተው በጦርነቱ ድል የተነሱት ቴዎድሮስ ናቸው ። ሆኖም ድል
የተመቱ ቢሆንም ድል አድራጊዎች በታላቅ ቀናኢነት የሚመለከቱትን ፍላጎታ
ቸውን ጠላቶቻቸው እንዲቀበሉ የማስገደድ መብት ተግባራዊ ለማድረግ እንግ
ሊዞች ይችሉ ዘንድ ቴዎድሮስ በሕይወት አልተያዙላቸውም ።

ነገሩን መለስ ብለን ብንቃኘው እንግሊዞች የኢትዮጵያን ክብርና ሉዐላዊነት
የሚነካ የውል ሁኔታ በተጽእኖ ከማስፈረም የሚመለሱ አልነበሩም ። ነገር ግን
ቴዎድሮስ ለወራሪው በተሸናፊነት እጅ ከመስጠት ይልቅ ሞትን ስለመረጡ ሚያ
ዝያ 5 ቀን 1860 ዓ.ም. ወደ ማታ በገዛ እጃቸው ሕይወታቸውን አሳልፈዋል ።

<u>መደምደሚያ</u>

ሆኖም ቴዎድሮስ የጦርነቱ ብቸኛ ተጐጂ አልነበሩም ፤ ሞታቸውም በከንቱ
አልነበረም ። ቁርጠኛ አቋማቸው ታላቋ ብሪታንያ በ17943 በቅሎዎችና አጋሰ
ሶች በ2538 ፈረሶች በ1759 አህዮች በ8975 በሮች ፤ በ5735 ግመሎች በ44 ዝሆ
ኖች የሚረዱ 42 000 ሰዎችን እንድታሰልፍ አስገድዷታል። ለዚህም ዘጠኝ ሚሊ
ዮን ፓውንድ የወጣ ሲሆን ፤ ይህም ለጦርነቱ ከተመደበው በአምስት ሚሊዮን
ፓውንድ ከፍ ያለ ነው ። ይህም ሁሉ ኃይል የተሰለፈው ፤ ይህን ያህል ገንዘብም
የፈሰሰው ከ7000 ሰው የማይበልጠውን የቴዎድሮስ ጦር ለመግጠም ነበር [39] ።
በዚህም ትክክለኛ የሆነ ውል ለመዋዋል የሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች የጋራ ፈቃድና
ሙሉ ፍላጎት አስፈላጊ ስለመሆኑ ቴዎድሮስ በተጨባጭ እንግሊዞች እንዲያጤ
ኑት አድርገዋል ። እንደዚሁም ሀበሻ ብሪታንያን ጨምሮ ከአውሮፓ ኃያላን መን
ግሥታት ጋር በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዲኖራት
ያላቸውን ጽኑ ፍላጎት አጉልተው ለማሳየት ችለዋል ።

ባጭሩ ሞታቸው ጽኑ አቋማቸውንና እንቢተኛነታቸውን ባንድነት አጣ
ምሮ የሚያሳይ ነው ። መልዕክቱም ከእንግሊዞች የተሰወረ አልነበረም ።

ስለዚህ ጦርነቱ እንዳበቃ ናፒር ሲጽፍ የሚከተለውን ብሎ ነበር ።

> ከሀበሻ መሪዎች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር የእንግሊዝ መንግ
> ሥት በአፍሪካ ውስጥ ቆንሲል ላለማስቀመጥ ወስኗል [40] ።

ከዛም ሩቤንስን በትክክል እንደገለጠው " ቆንስሎቻቸው በምድር ሀበሻ
ሰንደቅ ዓላማቸውን ለማውለብለብ ሳይረጉት ጥረት የከፈሉትን ከፍተኛ መሰዋ
ዕትነት በማጤንና እንደዚህ ያለ ሁኔታ ለወደፊት እንዳይከሰት በማሰብ " እን
ግሊዞች በሀበሻና በጠረፎቿ የዘረጉዋቸውን የቆንሲል መረቦች ወዲያውኑ እንዳ
ነሱ እንገነዘባለን ። [41]

የቴዎድሮስ ነገር በዚሁ አክትሟል ። ከርሳቸው ሞት ጋርም የ1842 ዓ.ም. ውልና እንግሊዞች በኢትዮጵያ የነበራቸው ዕቅድ ገብአተ መሬት ተፈጽሟል ። በዚሁ እንግሊዞች ለሃያ ዓመታት ያህል ሲያራምዱት የነበረው የዲፕሎ ማሲያዊ እንቅስቃሴ በውድቀት ተደምድሟል ። ሆኖም ውድቀቱ እንግሊዞቹን ለዘለ ዓለም አስመርሮ ቆንስላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የዳኝነት ሥልጣን እንዲኖረው እንዳይፈልጉ የሚያደረግ አልነበረም ።

በዚህም የተነሳ ከ40 ዓመት በኋላ በ1900 ዓ.ም. በተፈረመው የክሎቢኪ ውሲኪ ውል አማካይነት ታላቋ ብሪታንያ ይህን ዓይነት መብት ብታስከብርም ፤ ይህን ማድረግ የቻለችው በፈረንሳይ[42] ጥላ ሥር ታካ በመግባትና በ1842 ዓ.ም. ውል ላይ ከተመለከተው እጅግ የደከመና የለዘበ የውል ሁኔታዎችን ተቀብላ ነው ።

የግርጌ ማስታወሻ ።

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ የጠቅላይ ፍ/ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ። ኤል ኤል ቢ የሕግ ፋኩልቲ አአዩ (ቀኃዩ) ፤ ኤል ኤል ኤም ማንቸስተር ዩኒቨርሲቲ ። በግልጽ ካልተመለከተ ጊዜው የተገለጸው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው ።

1. ሲ. ኤች አሌክሳንድሮዊች ፤ “ አን ኢንትሮዳክሽን ቱ ዘ ሂስትሪ ኦፍ ዘሎው ኦፍ ኔሽንስ ኢን ዘ ኢስት እንዲስ ” ኦክስፎርድ (1967) ገጽ 97—101 ።

. “ የክሎቢክዊስኪ ውል በመባል የሚታወቀው ” የ 1900 ዓ ም የፈረንሣይና የኢትዮጵያ ውል ዜጎችን የመዳኘት ሥልጣን ሰጥቶ የነበረው ኢትዮጵያ ለሚገኘው የፈረንሣይ ቆንሲል ብቻ ነው ። በ1920ዎቹ ግን ሀገሮቻቸው ከኢትዮጵያ ጋር የገቡትን “ ይበልጥ ተጠቃሚ አገር ” የሚለውን የውል ሐረግ መሠረት በማድረግ ከ10 የማያንሱ አገሮች የቆንሲል ፍርድ ቤቶችን አቋቁመው ነበር ።

3. ጂ ኤል ብሪየርሊ ዘ ሎው ኦፍ ኔሽንስ (ኦክስፎርድ — 6ኛ እትም እ. ኤ. አ. 1967) ገጽ 173—174።

4. ደብልዩ ሲ ፕላውዲን ትራቭል ኤን አቢሲኒያ ኤንድ ዘ ጋላ ካንትሪ (ለንደን እ. ኤ. አ. 1868) ገጽ 7

5. ፎርይን ኦፊስ (አፍኦ 401) 1 ገጽ 7—10 በሩቢንሰን እንደተጠቀሰው ዘ ሰርቫይቫል ኦፍ ኢትዮጵያን ኢንዲፔንደንስ ኖርዊች (እ. ኤ. አ. 1978) ገጽ 20 ።

6. ኤፍኦ 401(ገጽ 1 — 2 በሩቢንሰን እንደተጠቀሰው ገጽ 129 ።

7. ቻርለስ ቤክ ፤ ዘ ብሪትሽ ካፕቴቭ ኢን አቢሲንያ ። (ሎንግ ማንስ ለንደን እ. ኤ. አ. 1867) ገጽ 19።

8. በሩቢንሰን እንደተጠቀሰው ገጽ 121 ።

9. ጆርጅ አንሰሌይ ቮየጅስ ኤንድ ትራቭልስ — ቱ ኢንዲያ . . አቢሲንያ (ለንደን እ.ኤ.አ. 1809) ቮልዩም 3 ገጽ 263—264 ።

10. በቤክ እንደተጠቀሰው ገጽ 55—56 ።

11. ሩቢንሰን ገጽ 131 ።

12. ፕላውዴን ገጽ 420 — 421 ።

13. በሩቢንሰን እንደተጠቀሰው ገጽ 137 ።

14. የውሉን የእንግሊዝኛ ጽሑፍ ለማግኘት ከላይቭ ፓሪ ዘ ኮንሶሊዴትድ ትርቲ ሴሪስ ቦልዩም 103 ገጽ 299 — 303 ፤

15. ከዚያው ቮልዩም 92 ገጽ 272—276 ።

16. ጠንቀኛ መባሉ ምክንያቱም የውጫሌ ውል ተብሎ በሚታወቀውና የ1881 ዓ.ም. የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ውል አንቀጽ 17 ላይ የተፈጠረው አለመግባባት ነበር ለዝነኛው የአድዋ ጦርነት መንገድ ከፋች የነበረው ።

17. በእርግጥ በቀረበው ገጸ በረከት የተደሰቱ መሆናቸውን ለመግለጽ ራስ አሊ ለፕላውዲን ሁለት መንደሮች ሰጥተው ነበር ። ፕላውዴን ገጽ 396—399 ።

18. የሰኔ 17 1847 ዓ ም ዘገባ በቤክስ እንደተጠቀሰው ፤ ገጽ 48 ።

19. ከዚያው ።

20. ይህንንም ከፕላውዲን ትረካ መረዳት ይቻላል። “ በሁለቱ የውል ቅጂዎች በማህተማቸው ካተሙ በኋላ የራሳቸውን ድርሻ ለሚያቀርቡት አንድ ደብተራ ሰጥተው ደብረ ታቦር ወስዶ እንዲቀልፍበት አዘዘ ። የራስ ቤት በ1846 ዓ ም በደጃች ካሣ የተዘረፈና የተቃጠለ ስለሆነ ውሉ ስካሁን ሳይጠፋ አይቀርም ። ” ፕላውዲን ገጽ 421 ።

21. በቤክ የተጠቀሰ ገጽ 52 ።

22. “ አባ ሰላማ (ከእስክንድርያ የመጡት ጳጳስ) በኢትዮጵያ የነበረችውን የሮማ ቤት ክርስቲያንና ደጋፊዋን የፈረንሳይን መንግሥት ጥቅም አጥብቀው የሚጻረሩ ፤ ባንጻሩ ደግሞ የፕሮቴስታንት ወገን ጥብቅ ደጋፊ በመሆን የእንግሊዝን ጥቅም የሚያራምዱ ስለነበር ለዚሁ ወሮታ ድርጐ ተቆርጦላቸው ከፕላውዲንና እርሱም ከሞተ በኋላ ምጽዋ ከነበረው ወኪሉ ይቀበሉ እንደ ነበር ቻርለስ ቤክ ጽፎአል ። ገጽ 16—17 ።

23. የፕላውዴን የሰኔ 17 ፥ 1847 ዓ. ም. ዘገባ ፤ በቤክ እንደተጠቀሰው ገጽ 37 ።

24. ከዚያው ገጽ 35—38 ።

25. ከዚያው ገጽ 43 ።

26. ከዚያው ገጽ 54—55 ።

27. ከዚያው ገጽ 98 ።

28. ከዚያው ገጽ 67—68 ።

29. ቤክ የደብዳቤውን ቅጂ ከገጽ 312 — 316 አስፍሮታል ።

30. በ1855 ዓ ም ጥቅምት 19 ጐጃም ባይባባ ከተማ የተጻፈው ደብዳቤ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ግርማ ሥላሴ አስፋው በጻፉት <u>የኢትዮጵያ ንጉሥ ቴዎድሮስ ለንግሥት ቪክቶሪያና ለልዩ መልዕክተኛው በአማርኛ የጻፉአቸውን ደብዳቤዎች</u> ፣ መጽሐፍ ላይ ገጽ 3—3 ይገኛል ።

(ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ እ. ኤ. አ. 1979)

31. የንጉሡ ደብዳቤ በየካቲት 1855 ዓ ም ለውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ደርሶ በሶስተኛው ወሩ ለሕንድ ጉዳይ ጽ/ቤት ተልኮ ነበር ። እዚያም ለአንድ ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ ምንም አስተያየት ሳይታከል በት ግንቦት 3 ቀን 1856 ዓ ም ተመልሶ ለውጭ ጉዳይ መ/ቤት ተልኳል ። ግርማ ሥላሴና ሌሎች ገጽ ፤ 12

32. ቤክ ገጽ 93 — 94 ።

33. ሳሙኤል የተባለው ከካሜሮን ጋር እስከ ምጽዋ ድረስ አብሮ የሔደው ከንጉሡ ትርጁማኖች ውስጥ አንዱ ነበሩ ።

34. ከዚያው ገጽ 235 ። ከዚህ ትንሽ ቀደም ብሎ እሥረኞቹ በጊዜያዊነት ተለቀው ለራሳም ከተሰጡ በኋላ በራስም ድንኳን ውስጥ በተካሄደው ችሎት ላይ የተደረገውን ዋልድማየር እንዲህ ሲል ገልጦታል ።

ባለፈው ሳምንት እኛ የጋፋቶቹ ማለትም ፍላድና ወንድሞቻችን እንደዚሁም የተፈቱት እሥረኞች ጭምር በተገኘንበት በንጉሡ ትእዛዝ በራሳም ድንኳን ውስጥ ጉባኤ ነገር መሰል አድርገን ነበር ። ንጉሡ በካፒቴን ካሜሮን ፤ በባርዲል ፤ እና በሚሲዮናውያኑ በእነ ሽተርን እና ሮዘንታል ላይ የነበራቸው ክስ በጽሑፍ ቀርቦ ተሰምቷል ። ተከሳሾቹም ጥፋተኝነታቸውን በጉባኤው ፊት አምነው ተቀብለዋል ። በተለይ ሚስተር ሽተርን ሁሉንም ወክሎ “ ንጉሡን በድለናል ለዚህ የሚገባንን ቅጣት አግኝተናል እግዚአብሔር ለግርማዊነታቸው ረጅም ዕድሜ ፤ ለአገራቸው ብልጽግና ለጠላቶቻቸው ደግሞ ሽንፈትን እንዲሰጥ እንጸልያለን ። ” በማለት ተናግሯል ። በስብሰባው ላይ ቴዎድሮስ አልተገኙም ። በቤክ የተጠቀሰ ገጽ 210 — 211 ።

35. አለን ሞርሂድ <u>ዘ ብሉ ናይል</u> (1980 እ. ኤ. አ.) ገጽ 218 ።

36. ከዚያው ገጽ 232 ።

37. ከዚያው ገጽ 244—245 ።

38. ከሁለቱ ሠራዊቶቻቸው የሚሪ ግጭት በኋላ ጉዳዩን በሰላም ለመጨረስ ቴዎድሮስ እጃቸውን እንዲሰጡ ናፒር ጥያቄ ሲያቀርብላቸው እንዲህ ሲሉ ነበር የመለሱለት ፤

“ ታላቅና ጠንካራ ሰዎችን እንደ ሕጻናት በክንዱ ሲጫወትባቸው የነበረ ሰው በሌሎች እጅ ወድቆ እንዲጫወቱበት ፍጹም በጄ አይልም ። ” በሩቢንሰን የተጠቀሰ ገጽ 265

39. ሩቢንሰን ገጽ 257 ።

40. በሩቢንሰን የተጠቀሰ ገጽ 273 ።

41. ከዚያው

42. ከላይ የተጠቀሰውን ማስታወሻ ቁ. 1 ይመለከቷል ። የውሉን ጽሑፍ በሚመለከት ኤ. ጂንጉልድ ዱፕሪይ ደ ለ ኢንቬዚዮን አላሲቤሬሲዮን ደ ለ ኢቶዮፒ ቦልዩም 2 ፤ ፓሪስ 1955 (ገጽ 426—428 ይመለከቷል ።

የአጼ ቴዎድሮስ ደብዳቤዎች *

ዛቲ ጦማር ዘተፈነወት እምኀበ ንጉሠ ነገሥት
ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ ።
ትብጻሕ ኀበ ንግሥተ እንግሊዝ ብክቶርያ ።
እንዴት ነዎ ደኅና ነዎን ።
እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ ።
አቶ ቡላውዲንን የእርስዎ መላክተኛ ነው ብዬ ።
በፍቅር በወዳጅነት ተቀብዬው አለሁ ።
እስተ ዛሬ ድረስ ያለ መላኬ ባላርፍ ባይረጋልኝ ነው ።
አሁንም እርስዎም የክርስቶስ ልጅ ነዎ ።
እኔም የክርስቶስ ልጅ ነኝ ።
ስለክርስቶስ ፍቅር ወዳጅነት ፈልጌአለሁ ።
አሁንም ክርስቶስ ደሥ ቢአሠኘኝ ።
ሥንረጋ ደሥታየን ሁሉ ሺማግሌ ሰው ጨምሬ ።
ካቶ ቡላውዲን ጋር እልክ አለሁ አብሮ ደስ እንዲለን ።

(ማሃሉ ላይ ዘውድ የሜነ አንበሳ ፡ ዙሪያውን ከታች
" ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ " የሚል ከላይ የአረብኛ ጽሕፈት ያለበት ማኅተም አለ ፡ አዘጋጅ ።)

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ
ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ። ከአቶ ቦረኒ ።
እንዴት ሠነበትህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ ። የምሥራች በእግዚአብሔር ኃይል ቀናኝ ። ወዳጆቼን ቡላዲንን ዮሐንስን የገደሉን ሠዎች ፈጀኋቸው በእግዚአብሔር ኃይል ከሜት በቀር ከሠልፍ ያገኘሁትን ሁሉ ፈጀሁት አንድ አልተውሁም ። ወዲያው ተከታትዬ ተሻግሬ ሌባ ንጉሤን በእግዚአብሔር ኃይል ከነሠራዊቱ ፈጀሁት አኩስም ከሜዳው ላይ ። አንተንም ቶሎ ናልኝ ። ከዕንግሊዝ ንግሥት ከወዳጅ እግዚአብሔርን ያደረገልኝን የደሥታየን ወሬ የምልክ ሠው የምሠድ ነኝና ቶሎ ናልኝ ይዘህልኝ የምትሄድ ነህና ። የሊቀ መኳስ ዮሐንስን ። የአቶ ቡላዲንን ሠዎች እስታሁን ያቆየኋቸው ከኔ ሰው ካንተ ጋራ ይሄዱ ብየ ነው ።

(ማኅተም እላይ እንደተገለጸው አለ ፤ አዘጋጅ ።)

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ
ባንድነት በሶስትነት እግዚአብሔር መርጦ ያነገሰው ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ ይድረስ ። ከዕንግሊዝ ነገሥት ቢክቶሪያ ። እንዴት አሉ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ ። እስተ ዛሬ ድረስ አባቶች ነገሥታቱ ፈጣሪአችንን ቢበድሉት መንግሥታቸውን . . . እሚልፎ ሰጥቶባቸው ነበረ ዛሬ ግን እኔ ከተወለድሁ ፈጣሪየ ካመድ አንስቶ ኃይል ሰጥቶ ባባቶች መንግሥት አቆመኝ በእግዚአብሔር ኃይል . . . አስለቀቅኋቸው ቱርኮች ግን ያባቴን መሬት ልቀቁ ብላቸው እምቢ ብለውኝ

---

* እንዚህ ደብዳቤዎች ከዋናው መጣጥፍ ጋር እንዲወጡ ያረግ ነው ለተተቸው ሁኔታ መሠረታዊ ሰነድ ናቸው በሚል ነው ። (አዘጋጅ)

በእግዚአብሔር ኃይል ይኸው ልታገል ነኝ። እነአቶ ቡላዲን እነሊቀመኳስ ዮሐንስ የክርስቲያን ንጉሥ ታላቅ ሰው ክርስቲያን የሚወዱ አሉ እናስተዋውቅህአለን እያሉኝ እጅግ እወዳቸው ነበረ የርስዎን ወዳጅነት ያገኘሁ እየመሰለኝ ። ሞት አይቀርምና የጠሉኝ ሰዎች እኔን ይክፋው ሲሉ ገደሉአቸው እኔም በእግዚአ ብሔር ኃይል ደመኞችን ፩ ሳልተው ፈጀኋቸው የገዛ ዘመዶቼን ። በእግዚአብሔር ኃይል የርስዎን ዝምድና ሥፈልግ ። ቱርኮች ከባህር ላይ ሁነው መልክተኛየን አናሳልፍም ብለው ቸግሮኝ ሳለ ቆንስል ኬሜሮን መጣልኝ ወረቀትና የፍቅር በረከት ይዞ ። በእግዚአብሔር ኃይል እጅግ ደስ አለኝ ደህንነትዎንና ፍቅር ዎን ብስማ የሠደዱልኝንም የፍቅር በረከት ተቀበልሁ እግዚ አብሔር ይሥጥልኝ ። አሁንም መልክተኛየን ቆንስል ኬሜሮን ጋር የፍቅር በረከት ይዞ እንዳልሰደው ቱርኮች በባህር ላይ የማ ያስተላለፉልኝ ሆነ አሁንም እንዲህ ባለ ስፍራ እከሌ ይቀበለው ብለው ይላኩብኝ ። ምላሹን ቆንስል ኬሜሮን ይዞልኝ ይምጣ ። እናንተም ተገፉልኝ . . . ።

ተጻፈ በ፲ሺተ፫፻፶፰ ዘመን በሉቃስ ?

በወርኃ ጥቅምት በ፳ ቀን ጐጃም በይባባ ከተማ

(ማኅተም የለም ። አዘጋጅ ።)

የወዳጅነትና ፤ የንግድ ውል

በእንግሊዝ ንግሥትና በሐበሽ ንጉሥ መካከል

በንግድ እጅግ ሀብት እጅግ ገንዘብ የሚገኝ ከሆነ ስለዚያ አገሮች በወዳጅነት በፍቅር የታሰሩ ። የውል ማለቂያ የዘለዓለም ወዳጅነትና ንግድ በንግሥት እንግሊዝና በሐበሽ ንጉሥ መካከል በማድረግ ሁለቱ አገሮች እጅግ የሚጠቀሙ ስለሆኑ ካሁን ቀድሞ ስለተፈለገ በሁለቱ ነገሥታቶች ። የሁለቱ አገሮች ንግድ ውል እንደምን እንደምን የሚሆን እንዲጻፍ የሚገባ እንደሆን ስለዚህ የሚከተለውን ውል ሁሉ ተነግሮና ተደርጎ ባቶ ፑላውዱን ኩንስል ንግሥት እንግሊዝ በሐበሽ ይህን ውል ለማሰር ታዘው በንግሥት እንግሊዝና በሐበሽ ንጉሥ መሀል ። ውል ፊተኛ ብርቱ ልብ ለልብ የሚሆን የሚሰነብት ፍቅር በንጉሠ ሐበሻና ቀጥሎ በሚነግሥ በእንግሊዝ ንግሥት ፊት ጠሪያና ቀጥሎ በሚነግሥ ማኽል እንዲኖር ።

ሁለተኛ ።

የሁለቱ አገር ያሁን ቀደም ወዳጅነት እንዲጠና እንዲጨመር የሐበሽ ነገሥታትና ቀጥለው የሚነግሡ ከንግሥት እንግሊዝና ቀጥሎ ከሚነግሥ የተላከ ቢሆን ኩንስልም ቢሆን እንዲቀበሉ እንዲጠብቁ ወግም እያጥፉባቸው ያከብርዋቸው ።

ሶስተኛ ።

እንዲሀ ደግሞ ንግሥት እንግሊዝና ቀጥሎም የሚነግሥ ከሐበሻ ንጉሥ ቀጥሎም ከሚነግሥ የተላከ ቢሆን ሹምም ቢሆን ይቀበላሉ ይጠብቃሉ እንደዚህ ደግሞ ወግ እያጠፉባቸውም ያከብርዋቸዋል ።

አራተኛ ።

ንጉሠ ሐበሽ ውል ይሰር ሊሰጥ ለዜጎች ለእንግሊዝ ንግሥት ለቃቸውና ለንዷቸው ቸርነትን ሁሉ ማክበርን ሁሉ ነጻነትን ሁሉ ወይም በቀረጥ ወይም በግብር ወይም በሌላ ነገር ከዚህ በፊት ሰጥቶ እንግዲህም የሚሰጥ ቢሆን ።

አምስተኛ ።

የእንግሊዝ ዜጎች ወዲህ ወደሐበሻ የሚያገቡት ዕቃ ሲገባ ቀረጡ አምስት ከመቶ ይጣልና ይቀበል ንጉሠ ሐበሽና ቀጥሎ የሚነግሥ በሐበሽም ቢሆን ቢሸጥ ወዲያ ከሌላ አገር አልፎም ቢሸጥ ።

ስድስተኛ ።

ይህ አምስት በመቶ የተጣለው ገቢ ቀረጥ በጎንደር ገቢያ ዕቃ እንደሚሸጥ በወራቱ ይገምግምና ይሰጥ ይህን አምስት በመቶ የተጣለውን ግምግሙንም ቢሆን ዕቃውንም ቢሆን ነጋዴው እንደወደደ ይስጥ ።

ሰባተኛ

ይህን አምስት በመቶ የተባለን ቀረጥ በሚገባ ሰጥቶ የሚያገባው ነጋዴ ዕቃውን በስፍራው ሁሉ በግዛተ አበሽ በፈቀደው እንዲሸጥ ዕቃው ለመውጣቱ ትእዛዝ ሳይፈልግ ሳይከለከል ሳይቸገር ሌላ ገቢ ቀረጥ ሳይጣልበት ከገገፑ ላይ ሁለተኛ ቀረጥ እንዳይጣልበትና እምያገባው ነጋዴ ያን ዕቃ ከሌላው ስፍራ ከሌላ አገር በወደደው ይውሰድ ለመውሰዱ ትእዛዝ ሳይፈልግ ሳይከለከል ሳይቸገር ሳይበደል ሌላ ምንም ቀረጥ ሳይከፍል ።

ስምንተኛ ።

የእንግሊዝ ነጋዶች የሚሹትን ሁሉ ዕቃ በፈቀዳቸው እንዲገዙ በግዛተ ሐበሽ ያም ዕቃ የሐበሽም ቢሆን ወይም ከሌላ የመጣ ቢሆን እኒያ ነጋዶች በፈቀዳቸው ያን ዕቃ ወስደው ምንም ቀረጥ እንዳይከፍሉ ።

ዘጠነኛ ።

የሐበሽ ንጉሥ ዜጎች በንግሥት እንግሊዝ አገር በሌላ አገር የተወደዱ ዜጎች የሚያገኙትን ቸርነት ሁሉ የሐበሽ ንጉሥ ዜጎች ያገኛሉ ከሐበሽ የሚመጣ ዕቃ ከእንግሊዝ ንግሥት የሚገባ ዕቃ ከሌላ አገር የሚመጣው ዕቃ ከሚቀረጠው የበለጠ አይቀረጥም ።

አስረኛ ።

እኛ በኛ ንግድ በሐበሽ ዜጎች በሐበሽ አጠገም ያሉ አገሮች ሁሉና በእንግሊዝ ዜጎች ማኸል ይሁንና ይደረግ ።

አስረኃንደኛ ።

የሐበሽ ንጉሥና ተከትሎ የሚነግሠው የሌላውን የሩቁን አገር ነገዶች ያባብሉ ዕቃቸውን በሐበሻ ግዛት እንዲያመጡ በዚያ ንግድ እንዲያመጡ በዚያ ንግድ እንዲበዛ እንዲጨመር በሐበሻና በእንግሊዝ መካከል ።

አስራሁለተኛ ።

ባንድ አኩል ደግሞ እንግዲህ ይህን አይተው ንግሥት እንግሊዝና ተከትለው የሚነግሡ የእንግሊዝ ነጋዶች በሐበሽ የተፈለገውን ሁሉ ዕቃ እንዲያመጡ ያደርጋሉ ።

አስራዕስተኛ ።

ለነጋዶችና ለከብታቸው ጤና ማግኘት የሐበሽ ንጉሥና ተከትለው የሚነግሡ የእንግሊዝ ንግሥትና ተከትለው የሚነግሡ እንደጉልበታቸው ይጠብቃሉ መንገድ ያስመቻሉ ከባሕር እስከ ሐበሽ ድረስ ።

አስራራተኛ ።

የሁለት አገር ዜጎች መገናኛቸው እንዲገፉ እንዲጨመር የሐበሽ ንጉሥ ለርሳቸውና ተከትሎ ለሚነግሥ ውል ያደርጋሉ የእንግሊዝ እንግዶች ክፋትና መከልከል እንዳያገኛቸው በሐበሻም ግዛት ተቀምጠው ቢሆኑ ወይም ወደሌላ አገር ለማየት ሲያልፉ ቢሆኑ ሰውነታቸውና ከብታቸው በውል እንዲጠበቅ ።

አስራአምስተኛው ።

የኒህ እንግዶች ለመሸጥ ያላመጡት ዕቃቸው ምን ምን እንዳይቀረጥ በማናቸውም ምክንያት ሁኖ ገንዘባቸው እንዳይነካባቸው ።

አስራስድስተኛ ።

የሐበሽ ንጉሥ ዜጎች ምንምን ክልከላ ምን ምን መቸገር አያገኛቸውም በንግሥት እንግሊዝ ግዛት ሳሉ ከፈቀዳቸው ከሌላ አገር ቢያልፉ አይከለከሉም ።

አስራሰብዓተኛ ።

የሐበሽ ንጉሥ ውል ይሰር በምንም ነገር በግዛተ ሐበሽ የእንግሊዝ ዜጎች በማንም ነውር በተከሰሱ ጊዜ በእንግሊዝ ንግሥት ኵንስል ይዳኙ ወይ በሌላ ሹም የእንግሊዝ ንጉሥ በዚያ የሾመው በማንም ነገር ጠብ ቢነሻ ምጉትም በእንግሊዝ ዜጎች ቢነሻ ወይም በእንግሊዝ ዜጎችና በሐበሻ ንጉሥ ዜጎች ማኸል ወይም በእንግሊዝ ዜጎችና በሌላ አገር ዜጎች ማኸል ቢነሳ በንጉሡ ሐበሽ ግዛት የሐበሽ ንጉሥ ኵንሰል ወይ ሌላ በዚያ የተሾመው ይሰማና ይዳኝ ማንም ማን ቢሆን ከሐበሽ ሹማምንቶች ሳይናገሩበት ሳይገቡበት ሳያስቸግሩት ምጉት ሲጀምር ወይም ሲማጎት ወይ ሲጨርስ ።

አስራስምንተኛ ።

የእንግሊዝ ዜጋ በሐበሻ ግዛት የሞተ እንደሆን የእንግሊዝ ኵንሰል ወይም ወኪላቸው የሞተውን ሰው ወረቀቱን ገንዘቡን ይቀበላሉ ብድር ቢኖርባቸው ወራሽ ቢኖራቸው ባለዳ ቢኖርባቸው ወስዶ እንዲሰጣቸው የሐበሻ ሹማምንት ሳያስቸግርዋቸው ።

አስራዘጠነኛ ።

በመጨረሻው ውል ይደረግ ይህ ሁሉ በፊት የተናገርነው አለመፍረስ የዘለ ዓለም ወዳጅነት በሁለቱ ነገሥታቶች ማኸል ይቆማል ።

በዚህ ምስክር ይህ ውል ታተመ ካሁን ቀደም በተጠራ ባቶ ፕላውዱንና በሐበሽ ንጉሥ በጃቸው ።

በናውጋ በ፯ ሺሕ ከ፫፻ ዓመተ ዓለም በ፲፰ ወ፻፺ወ፭ ዓመተ ምህረት በዘመነ ማርቆስ በጥቅምት በ፳፬ኛ ቀን ተደረገ በእንግሊዝ ታሪክ በ፲፱ወ፻ወ፪ እምልደት ክርስቶስ በኖቬምበር በ፪ኛ ቀን የወዳጅነትና የንግድ ውል በታሪክ እንግሊዝ በኖቬምበር በሁለተኛው ቀን እንደ ሐበሽ ታሪክ በጥቅምት በ፳፬ተኛው ቀን የተደረገ በንግሥት እንግሊዝና በሐበሻ ንጉሥ መካከል ማስሬው በንግሥትም እንግሊዝ ማኅተም የታተመ ካቶ ፕላውድን ኮንሰል እንግሊዝ በሐበሽ የሐበሻ ንጉሥ ተቀብየአለሁ ብለዋል ። ለዚህም ምስክር የሐበሻ ንጉሥ ማኅተም ታትሟል ። ዛሬ በማርች በ፩ተኛው ቀን በዓመተ ምህረት ሺሕ ከ፱፻ከ፶፪ እንደ ሐበሻ ታሪክ በየካቲት በ፳፪ ቀን በዓመተ ምሕረት ሺሕ ከ፱፻ከ፵፬ ።

ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ የሕግ አወጣጥ ሥርዐት

ክፍል አንድ ።

የሕግ አወጣጥ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት

* በሺፈራው ወልደ ሚካኤል

ይህ ጽሑፍ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት በሥልጣን በቆየባቸው ጊዜያት በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረውን የሕግ አወጣጥ ሥርዐት ለማሳየት ይሞክራል ። በጊዜ ሲሰላ ጽሑፉ ከመስከረም 2 ፡ 1967 ዓ.ም. እስከ መስከረም 1980 ዓ.ም. ያለውን ወቅት የሚያካትት ይሆናል ።

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ የሕግ አወጣጥ የተለያዩ ደረጃዎች አሉት ፤ ማለትም ፡ የሕግ ማመንጨትን ፣ ማጠናቀርን ፡ ማጽደቅን ፡ መፈረምንና ፣ ማወጅ ያጠቃልላል ። ርዕሱን ከነዚህ ነጥቦች አኳያ ለመዳሰስ እንሞክራለን ።

የአብዛኛዎቹ ሀገሮች ሕገ መንግሥቶች በጽሑፍ የሠፈሩ ናቸው ፤ እነዚህም ሕግጋተ መንግሥት አብዛኛውን ጊዜ የሕግ አወጣጥን ማለትም ሕግ በማን እንደሚወጣ ፤ በአወጣጡም ሥርዐት ሊከተሉዋቸው ስለሚገቡ ቅደም ተከተሎች (በፓርላማ የሚወጣ ሲሆን ማለት ነው) ወይም ሊከተሏቸው (በዘውዳዊ አገዛዝ የሚወጣ ሲሆን) ስለሚገቡ ደንቦች ይደነግጋሉ ። በኢትዮጵያም ቢሆን ይህ ሁኔታ ከ1920ዎቹ ጀምሮ እስከ መስከረም 2 ፡ 1967 ዓ ም ድረስ የነበረ ሐቅ ነው ። ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት የኃይለ ሥላሴን ዘውዳዊ አገዛዝ አስለቅቆ ሥልጣን እንደጨበጠ መስከረም 2 ፡ 1967 ዓ ም በአዋጅ ቁ. 1/1967 መሠረት የ1948ቱን ሕገ መንግሥት እንዳይሠራ አደረገ ።[1] በተጨማሪም የሕግ መምሪያንና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቶችም (ፓርላማ) እንዲፈርሱ ሆነ ።[2] በዚሁም የተነሳ ከ1967 ዓ ም ወዲህ ላሉት ጊዜያት በኢትዮጵያ ላለው የሕግ አወጣጥ የ1948ቱ ሕገ መንግሥት ምንም ሕጋዊ ጠቀሜታ የለውም ።

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት ስለሕግ አወጣጥ ጉዳይ የሚያሳይ ቀጥተኛና ብቸኛ ሕግ እንዳላወጣ የታወቀ ቢሆንም ስለዚሁ ጉዳይ ፍንጭ የሚሰጡ ጥቂት ሕጎች እንዳሉ ይታመናል ። በጸሐፊው አስተያየት የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣን እንደገና ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁ. 110/1969 ለዚሁ ጉዳይ ዋነኛው ነው ። የአዋጁ አንቀጽ 5/6/ የደርግ ጉባኤ አዋጆችን እንደሚያወጣ ደንግጓል ።[3] ስለሆነም የበላይ ሕጎችን (አዋጆችን) የማውጣት ሥልጣን የደርጉ ጉባኤ መሆኑ የታመነ ነው ። ከዚሁ አዋጅ አንቀጽ 19[4] መገንዘብ እንደምንችለው ሚኒስትሮችና ኮሚሺነሮች ሕግ ማመንጨት ብቻ ሳይሆን ደንቦች የማውጣት ሥልጣንም እንደተሰጣቸው ነው ። ይህም የተለመደ አሠራር ነው ። ለምሳሌ የሠራተኛ ማኅበራት አዋጅ ቁ. 222/1974[5] ዓ.ም. የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን ደንቦች የማውጣት ሥልጣን አጐናጽፎታል ። የውሃ ሀብት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 21/1973[6] አንቀጽ 15ም ለውሃ ሀብት ኮሚሽኑ ደንብ የማውጣት ሥልጣን ሰጥቶታል ።

ሕግ የማመንጨቱ ሥልጣን ለአንዳንድ ሕዝባዊ ድርጅቶችም ቢሆን ተሰጥቶአል ። በዚሁ ጉዳይ የሠራተኛ ማህበራት አዋጅ ቁ. 222/1974 ዓ ም አንቀጽ5/12 እንደምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል ። ይኸው አንቀጽ እንደሚከተለው ይነበባል ።

5/ የሠራተኞች ማኅበር የወል ተግባርና ኃላፊነት አግባብ ባለው ሌላ ሕግ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሠራተኞች ማኅበር የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል ።

12/ የመንግሥት ሕጎች ፤ ደንቦች ፡ መመሪያዎችና ፡ መግለጫዎች በአባሉ እንዲታወቁ እንዲከበሩና በተገቢ ሁኔታ በተግባር ላይ እንዲውሉ ማድረግ ፤ ሠራተኞችን የሚመለከቱ አዳዲስ ሕጎችና ደንቦች እንዲወጡ የወጡትም እንዲሻሻሉ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን ጠብቆ ሐሳብ ማቅረብ (ሠረዝ የተጨመረ) ።

የመላው ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበርም ቢሆን ገበሬውን በሚመለከት በሚወጡ ሕጎች ላይ የተወሰነ ሚና እንዲኖረው ተደርጓል ። ይህም የገበሬ ማህበራትን ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቁ. 223/1974 [7] በአንቀጽ 30/3/ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል ። አንቀጽ 30/3/ በከፊል እንደሚከተለው ይነበባል ።

(3) ገበሬውን የሚመለከቱ ደንቦችና መመሪያዎች ሲወጡ ሃሳብ የማቅረብ . . . (ሠረዝ የተጨመረ) ።

ማእከላዊዎቹ የከተማ ነዋሪዎች ማህበራትም ቢሆኑ ሕግ የማመንጨትና አንዳንዶም ደንብ የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋል ። [8] ሕግ የማመንጨቱ ሥልጣን ቻርተር ለተሰጣቸውም ሆነ ላልተሰጣቸው ከተሞች የተሰጠ ሥልጣን ነው ። በዚሁ ነጥብ ጠቃሚዎቹ የሕግ አንቀጾች በአንቀጽ 39 ሥር ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ናቸው ። እንደሚከተለውም ይነበባሉ ።

1. ከተማው ቻርተር የተሰጠው ሲሆን ፤

ሀ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን በማስፈቀድ የቦታ ኪራይ ፤ የአገልግሎት ታክስ ፤ የቤት ግብርና ቀረጥ መደልደል ፤ መሰብሰብ ፤

ለ/ ስለከተማው አስተዳደርና ስለማኅበሩ ንብረት አጠባበቅ ስለከተማው ጸጥታና ስለሕዝቡ ጤንነት የሚኒስትሮች ምክር ቤትን በማስፈቀድ ደንብ ማውጣት ፤

ሐ/ የከተማውን ፕላን አዘጋጅቶ ለመንግሥት ማቅረብ ፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ማዋል ፤ የከተማውን ቦታ በፕላን መሠረት ማስተዳደር ፤

2. ከተማው ቻርተር ያልተሰጠው ሲሆን ፤

ሀ/ የቦታ ኪራይ ፡ የአገልግሎት ታክስ የቤት ግብርና ቀረጥ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ማቅረብ ሲፈቀድም መሰብሰብ ። (ሠረዝ የተጨመረ) ።

ለ/ የከተማውን ፕላን አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ማቅረብ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ማዋል የከተማውን ቦታ በፕላን መሠረት ማስተዳደር ።

የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራቱ ይህንን እላይ የተጠቀሰውን ሥልጣን የተሰጣቸው ሕዝባዊ ድርጅቶች በመሆናቸው ነው ወይስ የመንግሥት መስተዳድር አካላት በመሆናቸው የሚሉ ጉዳዮች አከራካሪ ለመሆናቸው የሚያጠያይቅ አይደለም። በጸሐፊው አስተያየት ግን ሁለተኛው መስመር ማለትም ሥልጣኑ የተሰጣቸው የመንግሥት መስተዳድር አካላት በመሆናቸው ነው የሚለው መስመር የበለጠ ተደጋፊነት ያለው ይመስላል ።

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሴቶች ማህበርና የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወጣቶች ማህበር ግን እላይ ለሕዝባዊ ድርጅቶች የተሰጡ ሥልጣናት የተሰጣቸው አይመስልም ።

ከዚህ በላይ የሕግ ማመንጨትንና፣የሕጎችና ደንቦችን አወጣጥ ተመልክተናል ። እስቲ ቀጥለን ደግሞ በማጠናቀሩ ፣ በማጽደቁ ፣ በመፈረሙና በማወጁ ሂደት የሚያጋጥሙ ሥነ ሥርዓቶችን እንመልከት ።

አብዛኛውን ጊዜ ሕጎች ጉዳዩ በሚመለከተው ሚኒስቴር ውስጥ ይረቀቃሉ። አንዳንድ ከሚኒስቴሮች ምክር ቤት ወይም ከርዕሰ—ብሔሩ ልዩ ትእዛዝ የሚመነጩ ሕጎች ግን የሚዘጋጁት በሚኒስቴሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ሥር በሚገኘው የሕግ ክፍል ውስጥ ነው ። በዚያም መጣ በዚህ ሕጉ ወደ ሚኒሲተሮች ምክር ቤት ይላካል ። የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ከሚኒስቴሮች ምክር ቤት ምክትል ሊቀመንበር ጋር በመስማማት የሕጉ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥር በሚገኘው የሕግ ኮሚቴ በዝርዝር እንዲጠና ያቀርበዋል ። በተግባር እንደምናየው ወደ ሕግ ኮሚቴው ሳይቀርቡ በቀጥታ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚቀርቡት ረቂቅ ሕጎች ከፍ ያለ የፖሊሲ ውሳኔ የሚጠይቁ ወይም በአስቸኳይ መታወጅ ያለባቸው ሆነው ሲገኙ ነው ። እንደነዚህ ዓይነቶቹን ረቂቅ አዋጆች ምክር ቤቱ በስፋት ከተወያየባቸው በኋላ ከፖሊሲ መመሪያዎች ጋር አጣምሮ ወደ ሕግ ኮሚቴው ይልካቸዋል ። በሌላ በኩል የፖሊሲ ውሳኔ የማያስፈልጋቸው መስለው የሚታዩ ረቂቅ ሕጎች ሲገኙ የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ከምክር ቤቱ ምክትል ሊቀመንበር ጋር በመስማማት በቀጥታ ወደ ሕግ ኮሚቴው ይመራቸዋል ።

የሕግ ኮሚቴው ሊቀመንበር የሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ሲሆን ይህ ጽሑፍ ሲጠናቀር በአባልነት የተመደቡትም የሚከተሉት ነበሩ ።

ሀ/ የትምህርት ሚኒስቴር [9]

ለ/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

ሐ/ የገንዘብ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር

መ/ የማዕድንና ኃይል ማመንጫ ምክትል ሚኒስትር

ሠ/ ከማዕከላዊ ፕላን ብሔራዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት አንድ ተወካይ

ረ/ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ቢሮ የሕግ ጉዳይ ኃላፊው

ሰ/ ረቂቁን ያቀረበው ሚኒስቴር ወይም ኮሚሽነር ።

ኮሚቴው ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ለሥራው የሚያስፈልገውን ማናቸውንም የሚያገኘው ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ቢሮ የሕግ ጉዳይ

መምሪያ ነው ። ሕጉ እንደገና እንዲረቀቅ የሚያስፈልግ ሆኖ ሲገኝም የሚሠራው ይህ መምሪያ ነው ። ኮሚቴው በዚህ አኳኋን በዝርዝር አጥንቶ የሚስማማበትን የሕግ ረቂቅ በኮሚቴው ሊቀመንበር በተፈረመ ደብዳቤ አባሪነት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ ያቀርባል ። በአባሪው ደብዳቤ ውስጥ በረቂቁ ላይ የተደረጉ ዓበይት ለውጦች ካሉ ፣ አከራካሪ የሆኑ ጉዳዮች አጋጥመው ከሆነ ፣ የተደረሰው ውሳኔና የኮሚቴው አስተያየት ይገለጻሉ ።

ሕግ በአወጣጡ ሂደት የሚጓዝበት ሥርዓት አላይ በተገለጸው መልክ ሲሆን ለየት ያለ መንገድ የሚከከተሉ ጥቂት ረቂቅ ሕጎች አሉ ። አንዳንድ ረቂቅ ሕጎች ይህንን ረቂቅ ያጠና ዘንድ ወደተቋቋመ ልዩ ኮሚቴ ይመራሉ ። አንዳንዶም ረቂቅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከሕግና ከአስተዳደር ኮሚቴዎች ተውጣጥቶ ወደ ተቋቋመ ጥምር ኮሚቴ ወይም ከሕግና ከኢኮኖሚ ኮሚቴዎች ተውጣጥቶ ወደ ተቋቋመ ጥምር ኮሚቴ ሊመራ ይችላል ።

የሕግ ኮሚቴው ወይም ልዩ ኮሚቴው ወይም ጥምር ኮሚቴው ያጠናቀረውን ረቂቅ ሕግ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል ። የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ከምክር ቤቱ ምክትል ሊቀመንበር ጋር በመስማማት ረቂቅ ሕጉ በምክር ቤቱ አጀንዳ ላይ እንዲሰፍር ያደርጋል ። ምክር ቤቱ በረቂቁ ሕግ ይወያያል ፤ ካጸደቀውም ለጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እንዲቀርብ ያደርጋል ። ምክንያቱም ሕግ የማውጣት ሥልጣን ያለው የደርጉ ጉባኤ ነውና ።[10] ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ረቂቁን ሕግ ካጸደቀው ወደ ሚኒስትሮቹ ምክር ቤት ይልከውና ምክር ቤቱም በበኩሉ ሕጉ በነጋሪት ጋዜጣ ይታወጅ ዘንድ ወደ ምክር ቤቱ ሊቀመንበር ቢሮ ይልከዋል ። ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚላከው የጸደቀው አዋጅ ቅጂ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ዋና ጸሐፊ ይፈረማል ። አዋጆቹ የሚወጡት በደርጉ ስም ይሆናል ። በረቂቁ ሕግ ላይ የሚኒስትሮቹ ምክር ቤት የሚያደርገው ለውጥ ቢኖር አስፈላጊውን ማስተካከል የሚፈጽመው በምክር ቤቱ ሊቀመንበር ሥር የሚገኘው የሕግ ጉዳይ መመሪያው ነው ።

ደንቦች ማለትም ሚኒስትሮች በአዋጅ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት የሚያወጥዋቸው በደረጃ ዝቅ ያሉ ሕጎች እንዲጸድቁ ተብሎ ወደ ጊዜያዊ አስተዳደር ደርግ መላክ አያስፈልጋቸውም ። እነዚሁ ደንቦች የምክር ቤቱ ጉባኤ ካጸደቃቸው በነጋሪት ጋዜጣ ይታወጁ ዘንድ በቀጥታ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ቢሮ ይላካሉ ። ሲታወጁም ባወጣቸው ሚኒስቴር ወይም ኮሽነር ስም ነው የሚወጡት ።

የሕጎች በነጋሪት ጋዜጣ መታወጅ የሚመለከተው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ቢሮ ሥር የሚገኘውን የሕግ ኮሚቴ መምሪያን ነው ።

በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ወቅት

የአዋጅ አወጣጥ ሂደት በሠንጠረዥ ሲቀመጥ

(ልዩ ሁኔታ አልቀረበም ።)

የሕግ አፍላቂው ሚኒስቴር ወይም ቢሮ (1)

የሚኒስትሮች ምክር ቤት (2)

(2.ሀ)	(2.ለ)	(4)
በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕግ ኮሚቴ	የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ	በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሊቀመንበሩ ቢሮ
(3)	(5)	
ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ	ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት	

መፍቻ

1. አፍላቂው ሚኒስቴር (ቢሮ) ረቂቁን አዋጅ አዘጋጅቶ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ይልካል ።
2. ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ውስጥ የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ከምክትል ሊቀ መንበሩ ጋር በመስማማት ረቂቁን አዋጅ ወደ ሕግ ኮሚቴው (2.ሀ) ወይም ወይም ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ ይልከዋል (2.ለ) ።
3. የሕግ ኮሚቴው የቀረበለትን ረቂቅ መርምሮና አስፈላጊ ከሆነ እንደገና አር ቅቆ ረቂቁን አዋጅ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ ያቀርባል (2. ለ) ።
4. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉባኤ (2.ለ) የተስማማበት ረቂቅ አዋጅ ይጸድቅ ዘንድ ወደ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ይላካል (3) ።
5. የጸደቀው ረቂቅ አዋጅ ወደ ምክር ቤቱ ተመልሶ ይላካል (2) ።
6. ምክር ቤቱም በበኩሉ አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ እንዲታወጅ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር ቢሮ ይልከዋል (4) ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

* በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕግ መምሪያ ኃላፊ — ኤል. ኤል. ቢ. ሕግ ፋኩልቲ (አአዩ) ቀኃይ) ፡ ኤል. ኤል. ኤም. (ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ) ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ፋኩልቲ የትርፍ ጊዜ አስተማሪ ፤

1. ነጋሪት ጋዜጣ ፡ 34ኛ ዓመት ቁ. 1 ፡ አንቀጽ 5 እና 6 ።
2. ነጋሪት ጋዜጣ ፡ 34ኛ ዓመት ቁ. 1 ፡ አንቀጽ 4 ።
3. የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ አካል የሚከተሉትን ያጠቃልላል ።

   የደርግ አባላት በሙሉ የሚገኙበት ጠቅላላ ጉባኤ ፡ በጠቅላላው ጉባኤ የሚመረጡ አርባ አባላት የሚገኙበት ማዕከላዊ ኮሚቴና አሥራ ሰባት የደርግ አባላት የያዘ በጠቅላላው ጉባኤ የተመረጠ ቋሚ ኮሚቴ ። (የአዋጅቁ. 110/1969 ዓ.ም. አንቀጽ 2 ነጋሪት ጋዜጣ ፡ 36ኛ ዓመት ቁ. 13 ይመለከቷል።)
4. አንቀጹ እንደሚከተለው ይነበባል ፡ “ እያንዳንዱ ሚኒስትር የክፍሉን ሚኒስቴር ሥራ በሚገባ ለማካሔድና በርሱ ሥልጣን ሥር ያለውን ማናቸውንም ነገር በትክክል ለመፈጸም <u>የሚያስችለውን የሕግ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል ።</u>

   (ሠረዝ የተጨመረ) ፤
5. ነጋሪት ጋዜጣ ፡ 41ኛ ዓመት ቁ. 61 ።
6. ነጋሪት ጋዜጣ ፡ 41ኛ ዓመት ቁ. 3 ።
7. ነጋሪት ጋዜጣ ፡ 41ኛ ዓመት ቁ. 6 ።
8. ነጋሪት ጋዜጣ ፡ 40ኛ ዓመት ቁ. 15 ።
9. የትምህርት ሚኒስትሩ የኮሚቴው ምክትል ሊቀመንበር ነው ።
10. የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 110/1969 ዓ ም አንቀጽ 5/6/ ፡ ነጋሪት ጋዜጣ ፡ 36ኛ ዓመት ቁ. 13 ፡ ይመለከቷል ።

ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ የሕግ አወጣጥ ሥርዐት

ክፍል ሁለት

የሕግ አወጣጥ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብ ሊክ ሕገ መንግሥት ፡ ትንታኔና ሀሳብ ።

* ሺፈራው ወልደሚካኤል

የሕግ አወጣጥ ሂደት የጽሑፍ ሕገ መንግሥት ባላቸው አገሮች በሕገ መን ግሥቱ ውስጥ ሳይጠቀስ አይታለፍም ። የሕግ አወጣጥ ሂደቱ ማመንጨትን ፡ መደ ንገግን ፡ መፈረምንና በነጋሪት ጋዜጣ ማሳተምን ያካትታል ። በአንዳንድ አገ ሮች የሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ አንዱ ሌላው ጠቃሚ ደረጃ ክለሳና ቅንብር የሚ ባለው ይገኝበታል ።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የካቲት 1979 ዓ ም በውሳኔ ሕዝብ በጸደቀው የኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት ውስጥ የሕግ አወጣጥ ሂደትን የሚመለከቱ አንቀጾችን ለመመር መርና የዚህን ሂደት ደረጃዎችም አጢኖ ምናልባትም በዚሁ ሕግ ያልተጠቀሱ ነገ ሮች ቢኖሩ እንደማሟያ የሚያገለግሉ አንዳንድ ሀሳቦችን ለመሰንዘር ጭምር ነው።

ሕግ ማመንጨት ።

የሕግ ማመንጨት ደረጃ በሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ ቀዳሚ ነው ። የኢሕ ዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 71 ይህንን ይመለከታል ። በዚህ አንቀጽ መሠረት ሕግ የማመንጨት መብት ያላቸው የሚከተሉት ናቸው ።

- የመንግሥት ምክር ቤት
- የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት
- የብሔራዊ ሸንጐ ኮሚሽኖች
- የብሔራዊ ሸንጐ አባሎች
- የሚኒስትሮች ምክር ቤት
- ጠቅላይ ፍርድ ቤት
- ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
- የአስተዳደር ክልሎችና የራስ ገዝ ክልሎች ሸንጐዎች እና
- ሕዝባዊ ድርጅቶች በብሔራዊ አካሎቻቸው አማካይነት ።

ሕግ የማመንጨት መብት አንድ ሕግ እንዲወጣ ሃሳብ የማቅረብ መብት ማ ለት አይደለም ። ምክንያቱም ይህንን ሀሳብ በአንቀጽ 71 በሰፊው ከተዘረዘሩት ውስጥ ያልተጠቀሰ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት ሊያቀርብ ይችላል ና ። ይ ልቁንም ሕግ የማመንጨት መብት ሕግ መደንገግ ለሚችል አካል ይኸውም ለብ ሔራዊ ሸንጐ ፡ ለመንግሥት ምክር ቤት ፡ ለሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት ወይም ለሚኒ

ስትሮች ምክር ቤት ረቂቅ ሕጉን ማቅረብ መቻል ማለት ነው ። ለምሳሌ ስለአካባቢ ደህንነት ሕግ እንዲወጣ ፍላጐት ያለው አንድ ግለሰብ የአካባቢን ደህንነት የሚያስጠብቅ ረቂቅ ሕግ ሊያቀርብ ይችላል ። ነገር ግን ግለሰቡ ይህንን የረቂቅ ሕግ ሀሳቡን በብሔራዊ ሸንጐ አጀንዳ ውስጥ እንዲያዝለት ለማቅረብ በሕገ መንግሥት የተሰጠ መብት የለውም ። ቢሆንም ይህ ግለሰብ ይህን ረቂቅ ሕግ በኢሕዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 71 መሠረት ሕግ ለማመንጨት መብት ከተሰጣቸው አካሎች ውስጥ ለአንደኛው በማቅረብና ይህንን ረቂቅም የተባለው ባለመብት አካል ካመነበትና ከተቀበለው ረቂቅ ሕጉ እንዲደነገግ ሕግ ለማውጣት በሕገ መንግሥቱ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ማቅረብ ይችላል ።

የመነጨው ሕግ ዓይነት በሸንጐ የሚወጣ ከሆነ አዋጅ [1] ፣ በመንግሥት ምክር ቤት ከሆነ ድንጋጌ [2] ወይም ልዩ ድንጋጌ [3] ፡ እንዲሁም በሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት ከወጣ የፕሬዚዳንቱ ድንጋጌ [4] ሊባል የሚችል ዓይነት መሆን አለበት ። ልዩ የፕሬዚዳንቱ ድንጋጌ (አንቀጽ 87 (2) ሹመትን ብቻ የሚመለከት ስለሆነ ይህ ጽሁፍ አይመለከተውም ። የመነጨው ሕግ በሕገ መንግሥቱ መብት በተሰጣቸው አካላት እንደ ደንብ ሆኖ ሊወጣ ይችላል ።

መደንገግ ፤

በሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ የመደንገግ ደረጃ የሚባለው ረቂቅ ሕግ ለማጽደቅ ሥልጣን ባለው አካል ይኸው ረቂቅ ሕግ የሚጸድቅበትና ሕግ የሚሆንበት ደረጃ ነው ። በኢሕዴሪ ሕገ መንግሥት መሠረት የአንዳንድ ሕጐች የድንጋጌ ሁኔታ ቁልጭ ብሎ የተቀመጠ ሲሆን የአንዳንድ ዓይነት ሕጐች አደነጋገግ ግን ግልጽ አይደለም ።

በኢሕዴሪ ሕገ መንግሥት የሕጐች ዓይነት ተዘርዝሮ የተቀመጠ ቢሆን ኖሮ ምናልባት ይህ አርእስት በደንብ ተብራርቶ በተተነተነ ነበር ። በተዋረድ ሲታዩ የሕግ ዓይነቶች እንደሚከተለው ሊቀመጡ ይችላሉ ።

የሕግ ዓይነት	አውጪው አካል
አዋጅ	ብሔራዊ ሸንጐ
ድንጋጌ	የመንግሥት ምክር ቤት ፣ የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት
ደምብ	የሚኒስትሮች ምክር ቤት
አዋልድ ደንቦች	ሥልጣን የተሰጠው አካል

ከላይ ካለው የሕጐች ዝርዝር ውስጥ የሚታየው ግልጽ ግድፈት የመንግሥት ምክር ቤት ልዩ ድንጋጌ አለመኖሩ ነው ። ይህም ሕግ የሚወጣው በመንግሥት ምክር ቤት ሲሆን የሚወጣበትም ጊዜ ብሔራዊ ሸንጐ በጉባኤ ላይ በማይቀመጥበት ጊዜና ከስሙ እንደሚታየው " ልዩ ሁኔታ " በሚኖርበት ጊዜ ነው ። ልዩ ድንጋጌው የጸና ሆኖ የሚቆየው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ለሚቀጥለው የብሔራዊ ሸንጐ ጉባኤ እስከሚቀርብበት ድረስ ያለውን ጊዜ ያካትታል ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ልዩ ድንጋጌው ከፍተኛው የመንግሥት ሥልጣን አካል በሚያወጣው አዋጅ ላይ እንኳ የበላይነት ይኖረዋል ። ልዩ ድንጋጌው ለብሔራዊ ሸንጐው ከቀረበ በኋላ ወይ በሸንጐው ተቀባይነት ያጣና ሕግ መሆኑ ይቀራል ወይም ደግሞ ተቀባይነት ያገኝና በብሔራዊ ሸንጐው አማካይነት በአዋጅ መልክ ይወጣል ።

ከላይ በተመለከተው የሕጎች ዝርዝር ውስጥ ሌላው ያልተጠቀሰው የሕግ ዓይነት ደግሞ የፕሬዚዳንቱ ልዩ ድንጋጌ ነው ። የፕሬዚዳንቱን ልዩ ድንጋጌ የማውጣት ሥልጣን የሚመነጨው ከሕገ መንግሥት አንቀጽ 87 ነው ። ይህን ሥልጣን መጠቀም የሚቻለው ሸንጎው በጉባኤ ላይ በማይኖርበት ጊዜ ብቻ ነው ። የፕሬዚዳንቱ ልዩ ድንጋጌ በብሔራዊ ሸንጎ የተመረጡ ባለሥልጣኖች በፕሬዚዳንቱ መሾማቸው ወይም መሻራቸው ለሕዝብ የሚገለጽበት " ሕግ " ነው ። በአጠቃቀሙ አነስተኛነትና በተደጋጋሚ በሥራ ላይ የማይተረጐም በመሆኑ በዝርዝር አልመለከተውም ።

በመሠረቱ አዋጆች በብሔራዊ ሸንጎ ነው የሚታወጁት ። የመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌ ና ልዩ ድንጋጌ በመንግሥት ምክር ቤት ነው የሚታየወጁት ። የፕሬዚዳንቱ ድንጋጌ ደግሞ በፕሬዝዳንቱ ነው የሚታወጀው ። የደንቦች በአዋጅ መነገር ግን እላይ እንደ ተነጋገርንባቸው ሕጐች በአዋጅ መነገር ዐይነት ግልጽ ሆኖ አይገኝም ።

ደንብ የሚለው ቃል የተወሳው በሕገ መንግሥቱ በሁለት አንቀጾች ውስጥ ብቻ ነው ። በሁለቱም አንቀጾች ውስጥ ቃሉ የተነሳው ለመንግሥት አካሎች ከሚሰጥ ሥልጣን ጋር በተያያዘ መልክ ነው ። መጀመሪያ የተነሳው በአንቀጽ 82/1/ሐ/ ላይ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ አንቀጽ 92/1/ ላይ ነው ። " ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ የሆኑ የመንግሥት አካላት የሚያወጧቸውን ደንቦች ለመሻር . . . " የሚያስችል ሥልጣን አንቀጽ 82/1/ ሐ/ ለመንግሥት ምክር ቤት ይሰጣል ። የዚህን ንዑስ አንቀጽ ሁለንተናዊ መልኮች ለማየት ሙሉ ምርምር ከማካሄዳችን በፊት ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ የሆኑት የመንግሥት አካሎች የትኞቹ እንደሆኑ በመጠኑ ማየት ተገቢ ነው ። ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ የሆኑ የመንግሥት አካሎች (ከመንግሥት ምክር ቤትና ከሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት በቀር) የሚከተሉት ናቸው ።

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት
2. ጠቅላይ ፍርድ ቤት
3. የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ
4. ብሔራዊ የሥርተ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴ
5. የጠቅላይ (የዋናው) ኦዲተር ጽ/ቤት
6. የአስተዳደርና ራስ ገዝ ክልሎች ከፍተኛ ሸንጐዎች ።

ከእነኝህም ውስጥ ሁለቱ አካሎች ማለትም ብሔራዊ የሥርተ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴና (በሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው የሚል አቋም ካልተወሰደ በቀር) የጠቅላይ ኦዲተር ቢሮ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 71 ሕግ የማመንጨት ሥልጣን አልተሰጣቸውም ። ከዚህም በላይ በአንቀጽ 63/3/ ሠ/ እና /ረ/ እና 64/ሠ/ ብሔራዊ የሥርተ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴና የጠቅላይ ኦዲተር ቢሮ አመሠራረትና የኃላፊዎቻቸው " አመራረጥ " ከመጠቀሱ በቀር ስለሥልጣናቸው ጭራሽ የተጠቀሰ ነገር የለም ።

ከዚህ በላይ በተዘረዘረው መሠረት ጥሬ ሀሳቡን ካየን በኋላ ወደ ዋናው ጥያቄያችን ማለትም ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ የሆኑ ሁሉም የመንግሥት አካ

ሎች ደንብ የመደንገግ ሥልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም የሚለውን ነጥብ እን መልከት ።

እስቲ ወደ አንቀጽ 82/1/ ሐ/ እንመለስ ። የዚህ አንቀጽ ዋነኛ ምናልባትም ብቸኛ ዓላማ ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጎ የሆኑ የመንግሥት አካላት የሚያ ወጧቸውን ደንቦችና መመሪያዎች ለመሻር የሚያስችል ሥልጣን ለመንግሥት ምክር ቤት ለመስጠት ነው ። እንዲህ ሲባል ደግሞ ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸ ንጎ የሆነ ማናቸውም የመንግሥት አካላት ደንቦች የማውጣት ሥልጣን አላቸው ማለት አይደለም። ነገር ግን መብት ያላቸው እንደነኙህ ያሉት አካላት የሚያወጧቸ ውን ደንቦች የመንግሥት ምክር ቤት ለመሻር መብት አለው ማለት ነው። ይህ ንዑስ አንቀጽ ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ የሆኑ አካላት ደንቦችና መመሪያዎችን ሊያወጡ እንደሚችሉ አድርጐ ይቆጥራቸዋል ማለት ይቻላል። ስለዚህም በትክክል ለማጠቃለል ያህል ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ ለሆኑ አካላት ደንብ እንዲ ያወጡ የሚያስችል ሥልጣን ይህ አንቀጽ አይሰጣቸውም ።

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 92/1/ በሕግ መንግሥቱ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ደ ንብ የሚለው ቃል የሚገኝበት ርዚህ ጉዳይ ላይ እንደሚከተለው ይነበባል ።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል ፤

1. . . . ደንቦችና መመሪያዎች ማውጣት ፤

በሌላ በኩል ደግሞ አንቀጽ 97 2/ ን ብንመለከት የአስተዳደራዊና ራስ ገዝ ክል ሎች ሸንጐዎች መመሪያዎችን ብቻ ለማውጣት ሥልጣን አላቸው ።

ስለዚህ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ለማውጣት ሕገ መንግሥታዊ ሥል ጣን ሲኖረው የአስተዳደራዊና ራስ ገዝ ክልሎች ሸንጐዎች ግን ይህ ሥልጣን የላ ቸውም ። አንቀጽ 82/1/ ሐ/ ለአስተዳደራዊና ራስ ገዝ ክልሎች ሸንጐዎች መመ ሪያ እንዲያወጡ ሥልጣን ይሰጣቸዋል ብሎ ለመከራከር መሞከር (በአንቀጽ 97/2/ መሠረት እንኳ ቢሆን/ አንቀጹ እንዲሰጥ የማይጠብቀውን ወይም የማያስበውን ነገር እንዲሰጥ ማሰብ ማለት ነው ።

ሌሎቹ የመንግሥት አካላትም ማለትም ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፥ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ ፡ ብሔራዊ የሠርቶ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴና የጠቅላይ ኦዲተር ቢሮ ልክ እንደአስተዳደራዊና ራስ ገዝ ክልሎች ከፍተኛ ሸንጐዎች ሁሉ ደንብ የማውጣት ሕግ መንግሥታዊ ሥልጣን የላቸውም ።

በተቃራኒው በኩል ደግሞ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አካላት መብቶች በሙሉ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተጠቀሱ ቢሆን ኖሮ ስለደንብ አወጣጥ አንድ አንቀጽ ይኖር ነበር ብሎ መከራከር ይቻላል ። ይህ እንደገማቹ ሁኔታ እየታየ ግምት ብቻ —የተሳሳተ ወይም ጥሩ ዓይነት— ሊሆን ይችላል ።

ወደ ሌላ ነጥብ ከመሻገራችን በፊት በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተጠቀሰው “ ደንብ ” የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ እናብራራ ። በተዋረድ ሲታይ አ ዋጅ ከመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌ ወይም ከሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት ድንጋጌ ይልቅ በበላይነት ደረጃ ላይ ይገኛል።ቢሆንም ሁለቱም የበላይ ሕጐች ናቸው ። በተ መሳሳይ ሁኔታም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 92/1/ እንደተጠቀሰው ደንብ ምንም እንኳ በተዋረድ ሲታይ ከሌሎቹ የበላይ ሕጐች በሞላ የበታች ቢሆንም በደረጃው ግን ቀዳማዊ ሕግ ነው ።

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 92/1/ መሠረት የሚወጡ ደንቦች አዋልድ ደንቦች አይደሉም ። ደንቦች የሚለው ቃል ትርጉሙ አዋልድ ደንቦች ወይም የበላይ ከሆኑ ሕጐች ማለትም ከአዋጅ ወይም ከመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌ ላይ የተመሠረቱ የአፈጻጸም ሕጐች ለማለት ቢሆን ኖሮ ምንም አንቀጽ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የአፈጻጸም ሕጐች ለማለት ቢሆን ኖሮ ምንም አንቀጽ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ባላስፈለገ ነበር ። ይህ ጉዳይ በተሻለ ሁኔታ ሊታይ የሚችለው የአፈጻጸም ሕግ እን ዲወጣ ሥልጣን በሚሰጠው ቀዳማዊ ሕግ ውስጥ ነው ።

ደንቦች የሚለው ቃል በአንቀጽ 82/1//ሐ/ እና በአንቀጽ 92/1/ ውስጥ አንድ ዓይነት ይዘት አለው ብሎ መገመት ስህተት ነው ። የብሔራዊ ሸንጐ ፣ የመንግሥት ምክር ቤት ወይም የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚያወጧቸውን ሕጐች የሚቃረኑ ማና ቸውንም ደንቦች (አዋልድ ይሁኑ ወይም ሌላ) ለመሻር የሚያስችል ሥልጣን በመ ንግሥት ምክር ቤት ሥልጣን ክልል ውስጥ ይወድቃል ። ማንኛውም ሕግ ከሕገ መንግሥቱ ጋር ተቃራኒ መሆን አለመሆኑን የሚወስንና ከላይ በተዘረዘሩት አካላት ላይ የበላይነት ያለው አካል መደበኛ ስብሰባውን በዓመት አንድ ጊዜ ከሚያካሂ ደው ከብሔራዊ ሸንጐ በቀር ሌላ ማንም የለም ። በተጨማሪም የመንግሥት ም ክር ቤት ሕገ መንግሥቱንና ሌሎች ሕጐችንም ጭምር ለመተርጐም ሥልጣን የተሰጠው አካል በመሆኑ (አንቀጽ 82/1/ ለ/) ፣ ደንቦችን የመሻር ሥልጣን (በአ ንቀጽ 82/1/ ሐ/) ይህ ሥልጣን በአንቀጽ 92/1/ ለተዘረዘሩት ዓይነት ደንቦች ብቻ የተወሰነ ነው ብሎ አቋም መውሰድ ስህተት ነው ።

ለማጠቃለል ያህል አዋልድ ያልሆኑና እንደቀዳማዊ ሕግ የሚቆጠሩትን ደን ቦች ለመደንገግ በሕገ መንግሥቱ ሥልጣን የተሰጠው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ብቻ ነው ። ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ የሆኑ ሌሎች የመንግሥት አካላት እንደነኝህ ዓይነት ደንቦችን ለማውጣት ሕገ መንግሥታዊ መሠረት የላቸውም ።

አዋልድ ደንቦችን ወይም የአፈጻጸም ሕጐችን ለማውጣት እነኝህ አካሎች ወይም እንደሚኒስትር መሥሪያ ቤት ያሉ ሌሎች አካላት በቀዳማዊ ሕግ የተሰጠ ሥልጣን ሊኖራቸው ይችላል ። ምናልባት ጠለቅ ያለ ምርምር የሚያስፈልገውን ችግር ቢኖር የስያሜ ጉዳይ ነው ፤ ማለትም የመንግሥት አካላት የሚያወጧቸው አዋልድ ደንቦች ምን ስም ሊኖራቸው ይገባል ? እነኝህ ገላጭ የሆነ ስም ሊኖራ ቸው ይችላል ፤ አዋልድ ደንቦች ወይም የአፈጻጸም ደንቦች ሊባሉ ይችላሉ ።

መፈረም ።

መፈረም በሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ አንዱ ደረጃ ነው ። መፈረም ከማጽ ደቅ በኋላ የሚመጣ ደረጃ ሲሆን ከፊርማ በኋላ ግን ማወጅ ይቀጥላል ። መፈረም ሥልጣን ነው እንኳ ተብሎ ቢቆጠርም እንዳስፈላጊነቱ ሊጠቀሙበት የሚቻል ሥልጣን አይደለም ። እንዲያውም ጠባየ ነክ ነው ። ማለትም ከመፈረም በፊት ያ ሉት ደረጃዎች መጠናቀቃቸው ከተረጋገጠ በኋላ ወዲያውኑ ሊወጡት የሚገባ ግ ግዴታ ነው ። ከታች እንደምናየው ይህ ሁኔታ ከብዙ ሶሻሊስት ሀገሮች ሕጐችና ልምዶች ጋር ተመሳሳይ ነው ። የአንዳንድ ሶሻሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች አንድ የጸደቀ ሕግ በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ሳይታተም ሊቆይ የሚችልበት ከፍተኛው ጊዜ እስከመቼ ሊሆን እንደሚችል የሚገልጽ አንቀጽ አላቸው ። ለምሳሌ ያህል በአ ልባኒያ ሕጐች በሕግ አውጪው ክፍል “ ከጸደቁ በኋላ ከ15 ቀን በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ” በኦፊሴላዊ ጋዜጣ ላይ መታተም አለባቸው ።[5] በቡልጋሪያ ብሔራዊ ጉባኤ የጸደቁ ሕጐች “ ከጸደቁበት ጊዜ ጀምሮ ከ15 ቀን በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ”

በመንግሥት ጋዜጣ ላይ መታተም አለባቸው ። [6] ይህ ሁኔታ በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክም [7] ሆነ በሩማንያ [8] ተመሳሳይ ነው ።

ሕግን መፈረም የሚችሉት አካላት የትኞቹ እንደሆኑ በአንዳንድ አገሮች ሕገ መንግሥት በግልጽ ተጠቅሰዋል ። በሩሲያ ውስጥ " የሶቪየት ኅብረት ሕጎች ፣ ድንጋጌዎችና ሌሎችም የሶቪዬት ኅብረት የበላይ ምክር ቤት ውሳኔዎች በበላይ ምክር ቤቱ ፕሬዚዲየም ሊቀ መንበርና ጸሐፊ ፊርማዎች በየሪፓብሊኮቹ ይታተማሉ ። [9] በሩማኒያ ሶሻሊስት ሪፑብሊክ የታላቁ ብሔራዊ ጉባኤ ሕጎች በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ይፈርማሉ ። [10] የመንግሥት ምክር ቤት ሊቀመንበርና ጸሐፊ በሴይም (የፖላንድ ሕዝባዊ ጉባኤ) የሚወጡትን ሕጎች ይፈርማሉ ። [11] በኩባ በብሔራዊ ጉባኤው የጸደቁትን ሕጎች የመፈረም ኃላፊነት የተሰጠው ለሕዝባዊ ኃይል ብሔራዊ ጉባኤ ፕሬዚዳንት ነው ። [12] በሀንጋሪ ፓርላማ የተላለፉት ሕጎች የሚፈረሙት በሀንጋሪ ሕዝባዊ ሪፓብሊክ ፕሬዚዲየም ሊቀ መንበርና ጸሐፊ ነው ። [13]

በዚህ ጉዳይ ላይ የኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት ምንም ነገር አይገልጽም ። ምናልባት ትንሽ ፍንጭ ቢኖር ከአንቀጽ 86/5/ በመነሳት ይሆናል ። ይህን ነገር በተመለከተ ይህ አንቀጽ እንደሚከተለው ይነበባል ።

> የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ፕሬዚዳንት በዚህ ሕገ መንግሥትና በሌሎችም ሕጎች መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ።
>
> በብሔራዊ ሸንጎ ፣ በመንግሥት ምክር ቤትና በሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚወጡትን ሕጎች በነጋሪት ጋዜጣ ማወጅ ።

በሕዝባዊ ጉባኤ የወጡትን ሕጎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ መፈረምና እነዚሁ ሕጎች በኦፊሴላዊ ጋዜጣ እንዲታተሙ መፈረም ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው ። የመጀመሪያው ተግባር የሚከናወነው (በተለይ በሁሉም ሶሻሊስት አገሮች) በጉባኤው ስብሳቢ አማካይነት ነው ። የኋለኛው የሚከናወነው ግን በመንግሥት ምክር ቤት ፕሬዚዲየም ሊቀ መንበር አማካይነት ነው ።

ሕግን በነጋሪት ጋዜጣ ማወጅና ሕግን መፈረም የተገናኙ ነገሮች በመሆናቸው ከአንቀጽ 86/5/ በመነሳት በብሔራዊ ሸንጎ ፣ በመንግሥት ምክር ቤትና በፕሬዚዳንቱ የሚወጡ ሕጎች በፕሬዚዳንቱ (ማለትም የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት) ይፈረማሉ የሚል አስተያየት መስጠትና መከራከር ትክክለኛ ነው ።

ይህ ሁኔታ ስለመፈረም ጉዳይ ከፊል መልስ ሊሆን ይችላል ። በአንቀጽ 86/5 እና ከላይ በቀረበው ሀሳብ መሠረት የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት የመንግሥት ምክር ቤት የሚያወጣቸውን ድንጋጌዎችና ልዩ ድንጋጌዎች እንዲሁም ራሱ የሚያወጣቸውን ድንጋጌዎችና ልዩ ድንጋጌዎች ብቻ ይፈርማል ። በዚህ አንቀጽ የመጀመሪያ ክፍል እንደ ተጠቀሰው በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወጡ ደንቦችና በበላይ ሕግ መብት በተሰጣቸው አካሎች የሚወጡ አዋልድ ደንቦች አሉ ። ፕሬዚዳንቱ በነጋሪት ጋዜጣ የሚያውጃቸው ሕጎች በሕገ መንግሥቱ የተዘረዘሩ በመሆናቸው ፕሬዚዳንቱ ሌሎች ዝቅተኛ አካሎች የሚያወጣቸውን ሕጎች ይፈርም ማለት የማይጣጣም ሀሳብ ስለሚሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወጡትን ደንቦች ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀ መንበር ነውና ፣ እንዲፈርምባቸው ፣ እንዲሁም አዋልድ ደንቦችን ለማውጣት መብት የተሰጠው አካል የሚያወ

ጣቸውን ደንቦች የዚህ አካል የበላይ ኃላፊ እንዲፈርምባቸው ቢደረግ አግባብ ነው ብዬ አምናለሁ ።

በነጋሪት ጋዜጣ ማሳተም

በሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ የመጨረሻው ደረጃ የተደነገጉትን ሕጎች ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀ ጋዜጣ ላይ ማሳተም ነው ። የዚህ ሂደት ደረጃ አጠቃላይ ዓላማ ሕጎችን ኅብረተሰቡ ወይም ሕዝቡ እንዲያውቃቸው ለማድረግ ነው ።

ሕጎችን በጋዜጣ ማሳተም ልክ ሕጎችን እንደመፈረም ሁሉ ሁልጊዜም ያለ ማቋረጥ መደረግ ያለበት ነው ። ምክንያቱም በጋዜጣ ማሳተም ሥልጣን ሳይሆን የሕግ አወጣጥ ሂደት አንዱ አካል ነውና ። ይህንን ኃላፊነት የወሰደው አካል ሕጉ በትክክለኛው አካል መደንገጉንና መፈረሙን ካረጋገጠ በኋላ ለዚሁ ሲባል በተቋቋመ ጋዜጣ አማካይነት ያውጃል ።

በጋዜጣ ማሳተም ሕጎች ለታተመባቸው ጋዜጦችና ለእያንዳንዱም የሕግ ዓይነት ተከታታይ ቁጥር መስጠትን ያካትታል ።

በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት መሠረት ሕጎች በአንድ አካል ወይም በአንድ ግለሰብ አማካይነት ብቻ በነጋሪት ጋዜጣ ላይ አይታተሙም ። የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት “ በብሔራዊ ሸንጎ ፣ በመንግሥት ምክር ቤትና በሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚደነገጉትን ሕጎች ”[14] በነጋሪት ጋዜጣ ያውጃል ። ይህ ደግሞ አዋጆችን ፣ የመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌዎችና ልዩ ድንጋጌዎችን ፣ የፕሬዚዳንቱን ድንጋጌዎችን ና ልዩ ድንጋጌዎችን ጭምር ያካትታል ። ነገር ግን ቀደም ሲል ካየነው የሕጎች ዝርዝር ውስጥ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወጡ “ ሕገ—ደንቦች ” እና መብት በተሰጣቸው የመንግሥት አካላት የሚወጡ አዋልድ ሕጎች ወይም የአፈጻጸም ደንቦች ይገኙበታል ። ስለዚህ እነኚህ ሕጎችና ደንቦች እንደሌሎቹ ሕጎች ሁሉ በነጋሪት ጋዜጣ መታተም ይኖርባቸዋል ። ከዚህ ጋር በማያያዝ እነኚህን ደንቦች በነጋሪት ጋዜጣ የሚያውጃቸው ማነው የሚለው ጥያቄ ይከተላል ። ለዚህ ጥያቄ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የሚሰጠው መልስ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሚደነገጉ ሕጎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፣ በመንግሥት አካሎች ለሚወጡ የአፈጻጸም ደንቦች ደግሞ የነኝህ አካሎች ተጠሪዎች ያውጃሉ የሚል ይሆናል ።

በደረጃ ቀደም ተከተል ሲታዩ አብዛኛቹ ሕጎች በአዋጅ ፣ በመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌና በፕሬዚዳንት ድንጋጌ መልክ ስለሚወጡ ነጋሪት ጋዜጣው እነኝህን ሕጎች በነጋሪት ጋዜጣ ለማወጅ ሥልጣን በተሰጠው በሪፓብሊክ ፕሬዚዳንት ቢሮ ሥር ቢተዳደር የተሻለ ይሆናል ።

ክለሳና ቅንብር

በሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ የክለሳና የቅንብር ደረጃ ከማመንጨት ደረጃ ቀጥሎ የሚመጣ ደረጃ ነው ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ይህን ጉዳይ ወደኋላ እንዲመጣ ያደረግሁት ይኸው የጽሑፍ የመጨረሻ ክፍል አስተያየቶችን የያዘ ክፍል በመሆኑ ነው ።

ለጥናታችን የተመረጡትን አንዳንድ አገሮች ልምድ ከመመርመራችን በፊት ክለሳና ቅንብር ራሱ ምንን እንደሚያካትት ባጭሩ ለመመልከት እንሞክራለን ። በሕግ አወጣጥ ሂደት ውስጥ ይህ ደረጃ ሲደረስ እያንዳንዱ ረቂቅ ሕግ በሚከተሉት አንጻር ይመረመራል ፣ እንዲሁም ይገመታል ።

1. ከሕገ መንግሥቱ ፡ (ከቻርቲ) ከመንግሥት ፓሊሲና ዕቅድ ጋር አለ መቃረኑ ፤
2. ከሕግ ማርቀቅ ቴክኒክና የሕጎች መርህ ጋር መጣጣሙ
3. ለእያንዳንዱ የሕግ ዓይነት ከተቀመጠው ቅርጽ ጋር መጣጣሙ
4. በሕጉ ውስጥ ውስጣዊና ውጫዊ ቅራኔዎች መጥፋታቸውና
5. ረቂቅ ሕግ ሊያስወግድ የፈለገውን ችግር ማቃለል የሚችሉ አንቀጾች መኖራቸውን ማረጋገጥ ።

በዚህ ሂደት ውስጥ የሚያልፍ ማንኛውም ረቂቅ ሕግ ያለምንም ማመንቃት ሁሉም ባይሆኑም አብዛኞቹ ስህተቶቹ ይወገዳሉ ።

ስለዚህ ጠቃሚ የሕግ አወጣጥ ደረጃ ጉዳይ ከሌሎች አገሮች ልምድ ለማወቅ መጣር በትምህርታዊነቱ ብቻ ሳይሆን ለፖሊሲ አውጪዎችም በጣም ጠቃሚ ነው ሆላንዶች እላይ የተጠቀሱትን ተግባሮች የሚያከናውን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቢሮ ውስጥ የሚገኝ የሕግ ኮሚሽን አላቸው ። [15] በፈረንሳይ ክለሳና ቅንብር በካውንስል ዴኤታ [16] ሲካሄድ በፌዴራል ጀርመን ግን ይህ ተግባር በፍትህ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ይሚላል ። [17]

በኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መንግሥት የረቂቅ ሕጎችን ክለሳና ቅንብር ያከናውን የነበረው የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕግ ኮሚቴ ነበር ። [18] እያንዳንዱ ሕግም የሚመነጨው ወይም የሚያልፈው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ነበር ።

በኢሕዴሪ መንግሥት ሁኔታው የተለየ ነው ። ቀደም ሲል እንደዓየነው ሕጎች ቀጥታ ተጠሪነታቸው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ካልሆነ አካሎች ይመነጫሉ ። ይህ ሁኔታ የሚኒስትሮችን ምክር ቤት ሕግ ኮሚቴ መብት እንዳይኖረው ስለሚያደርገው የሁሉንም ሕጎች የክለሳና የቅንብር ተግባር እንዳያሟላ ያደርገዋል ። በአዲሱ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አወቃቀር የዚህ ኮሚቴ ህልውና እንደሚቀጥል አድርገን ብንገምት ከዚህ አካል የሚወጡት ሕጎች ምናልባት በበፊት ሁኔታ ሊከለሱና ሊቀናበሩ ይችላሉ ።

ይህ ሁኔታ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 71 የተዘረዘሩት ቀሪዎቹ በስምንት አካሎች የሚያመነጯቸውን ረቂቅ ሕጎች እጅግ አስፈላጊ የሆነውን የክለሳና የቅንብር ተግባር የሚያከናውን አካል አልባ ያደርጋቸዋል ። ከእነኝህ ስምንት አካላት የሚወጡትን ሕጎች ለመከለስና ለማቀናበር የሚችል አካል መፍጠር ይቻላል ። ነገር ግን በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ አስተያየት በአሁኑ ሰዓት በአገሪቱ ውስጥ ካለው የሕግ ባለሙያዎች እጥረት አኳያ ሲታይ አለአስፈላጊና ከአቅም በላይ ሆኖ ይታያል ። በተጨማሪም ሌላ የክለሳና የቅንብር ማዕከል እንዲኖር ማድረግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕግ ኮሚቴ (ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሚመነጩ ሕጎች) እና ሌላው አቀናባሪ አካል (በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 71 ከተዘረዘሩት ስምንት አካላት ለሚወጡ ሕጎች) የከለሷቸውንና ያቀናበራቸውን ሕጎች እንደገና መከለስና ማቀናበር በሚያስፈልግበት ጊዜ ሌላ አንድ ተጨማሪ አቀናባሪ እንዲኖር ግድ የሚል ይሆናል ።

ይህ ሁኔታ ደግሞ ሕግ አውጪ ማዕከልን የማቋቋምና ሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕግ ኮሚቴን ማፍረስ ያሻል ወደሚል ሀሳብ ያመራናል ። በዚህ ሕግ አውጪ ማዕከል ተነጻጻሪ እጩዎች የሚከተሉት ይሆናሉ ።

- የመንግሥት ምክር ቤት
- የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት ቢሮ
- የሚኒስትሮች ምክር ቤትና
- የፍትህ ሚኒስቴር

የመንግሥት ምክር ቤት የሕግ ማውጣት ተግባሮችን በሚመለከት ረገድ ዋነኛ ማዕከል ነው ። የመንግሥት ምክር ቤት የብሔራዊ ሸንጎው ቋሚ አካል መሆኑ ፣ ከፍተኛው ሕግ አውጪ አካል መሆኑ ፣ ድንጋጌዎችን የማውጣት ሥልጣኑ ፣ ሕገ መንግሥቱንና ሌሎች ሕጎችን መተርጐም ከመቻሉ ጋር ተጣምሮ ፣ እንዲሁም ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ሸንጐ የሆኑ የመንግሥት አካሎች የሚያወጧቸውን ደንቦችና መመሪያዎች የመሻር ሥልጣኑን ስንመለከት የመንግሥት ምክር ቤት ሕግ አውጪ ማዕከል ይሁን ለሚለው ሀሳብ በቂ ድጋፍ ከሚሰጡት ምክንያቶች ዋነኞቹ ናቸው ።

የሪፓብሊኩ ፕሬዚዳንት ቢሮ ሕግ አውጭ ማዕከል ይሁን የሚለው ሀሳብ የሚነሳው በአመዛኙ በሁለት ምክንያቶች ነው ። አንደኛው ድንጋጌ ለማውጣት ፕሬዚዳንቱ ሥልጣን ያለው መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አዋጆችን ፣ የመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌዎችንና ልዩ ድንጋጌዎችን ፣ የፕሬዚዳንቱ ድንጋጌዎችንና ልዩ ድንጋጌዎችን በነጋሪት ጋዜጣ የማወጅ ኃላፊነት የተሰጠው የፕሬዚዳንቱ ቢሮ በመሆኑ ነው ።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሕግ አውጪ ማዕከል ይሁን ለሚለው ሀሳብ ምክንያት የሚሆነው በዚህ አካል ሊመነጩ የሚችሉት ሕጐች ብዛት ስላላቸው ብቻ ነው ። አብዛኞቹ የመንግሥት ተግባሮች የሚከናወኑት በሚኒስትር መሥሪያ ቤቶችና በሌሎች ከፍተኛ የመንግሥት አካሎች ስለሆነ በአዋጅ ፣ በመንግሥት ምክር ቤት ድንጋጌዎች ፣ በፕሬዚዳንቱ ድንጋጌዎች ደንቦች መልክ የሚወጡት ሕጐች በጣም በብዛት የሚወጡት ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው ። ደንቦችን ለመደንገግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያለውን ሥልጣን ደግሞ ካየን ይህን አቋማችንን የሚደግፍ ነው ።

ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ መጨረሻ ላይ የተጠቀሰው እጩ የፍትህ ሚኒስቴር ነው ። ለሕግ አውጪ አካልነት ይህን ሚኒስቴር የምናጩው አስፈላጊው የባለሙያ ኃይል በበቂ ሁኔታ ይገኝበታል የሚለውን ግምት በመውሰድ ነው ።

ከላይ በቀረበው ትንታኔና በግልጽ እንደሚታየው ሕግ አውጪ ማዕከል የመንግሥት ምክር ቤት መሆን አለበት ወደሚል ማጠቃለያ ያመራናል ።

ረቂቅ ሕጐች ከተለያዩ ምንጮች ወደ ሕግ አውጪው ማዕከል መላካቸውና ሕግ በማርቀቅ ሂደት ውስጥ ያለውን ውስብስብነትና ቴክኒክ ልብ ካልን በኋላ በኔ በኩል የምሰጠው አስተያየት ማናቸውም ረቂቅ ህጐች ወደሚደነግጋቸው አካል ከመሄዳቸው በፊት እነኝህኑ ረቂቆች የሚከልልና የሚያቀናብር ኮሚቴ መቋቋም አለበት የሚል ይሆናል ። ኮሚቴው የተወከለና የሕግ ማርቀቅ ውጣ ውረድ በደንብ የሚያውቅ መሆን አለበት ።

የኮሚቴው አባሎች ከሚከተሉት ቢውጣጣ የተሻለ ይሆናል ።

- ከመንግሥት ምክር ቤት
- ከፍትህ ሚኒስቴር
- ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ
- ለሚረቀቀው ሕግ ኃላፊነት የወሰደው አካል
- ስለሕግ ማርቀቅ ጥሩ ዕውቀት ያላቸው ከ3 የማይበልጡ ግለ ሰቦች

የግርጌ ማስታወሻ ፣

* በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሕግ መምሪያ ኃላፊ ፡ ኤል ኤል ቢ ፣ ሕግ ፋኩልቲ አ. አ. ዩ. (ቀ.ኃ.ዩ.) ኤል ኤል ኤም ፡ (ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ) ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ፋኩልቲ በትርፍ ጊዜ አስተማሪ ።

1. የኢሕዲሪ ሕግ መንግሥት አንቀጽ 63 ።
2. ከዚያው ጠቀሳ ፡ አንቀጽ 82/3/ ።
3. ከዛው ጠቀሳ ፡ ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ 86/4/ ።
4. ይህ ጉዳይ በአንድ ወይም በሁለት ፓራግራፎች ብቻ የሚጠቃለል አይደለም። የሕግ መንግሥቱ አንቀጽ 83 ከብዙ አጨቃጫቂ አንቀጾች አንዱ ከመሆኑም በላይ ሕገ መንግሥትን የሚያጠኑ ተመራማሪዎች ብዙ ምርምር እንዲያካሂዱበት የሚጠይቅ ነው ።
5. የአልባኒያ ሕዝብ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት ፡ አንቀጽ 74 ።
6. የቡልጋሪያ ሕዝብ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 84/1/ ።
7. የጀርመን ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 65/5/ ።
8. የሮማኒያ ሶሻሊስት ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 57 ።
9. የዩ.ሶ. ሶ. ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 116 ።
10. የሩማኒያ ሶሻሊስት ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 57 ።
11. የፖላንድ ሕዝብ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 25/2/ ።
12. የኩባ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79/ዲ/ ።
13. የሀንጋሪ ሕዝባዊ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 26 ።
14. የኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 87/5/ 1/ ።
15. አር አርዘቭስኪ ፡ “ ዘ ሲስተም ኤንድ ሞድ ኦፍ ክሪኤቲንግ ሎው ኤንድ ዘ ፓሊሽ ፒፕልስ ሪፓብሊክ ” “ዘ ሎው ኢን ፖላንድ ” ፡ (1978) ከገጽ 7-38
16. ደብሊዩ ዲል ፡ ሌጂስሌቲቭ ድራፍቲንግ ፡ ኢኒው አፕሮች ፡ ከገጽ 334-335
17. ከላይ የተጠቀሰው
18. ሺፈራው ወ/ሚ ፡ በዚሁ እርእስት “ ክፍል አንድ ፡ የሕግ አወጣጥ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት ” እላይ ገጽ — ተመልከት ።

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

አራተኛ ችሎት ፡፡

ይግባኝ ባይ የአየለች ወልደ ገብርኤል ሞግዚት መልስ ሰጭ ጥሩነሽ ተሰማ
የፍትሐ ብሔር ይግባኝ መ. ቁ. 394/72

የመውሰድ ጥያቄ—ከጋብቻ ውጭ የተወለደ ልጅን አባት ማንነት ስለማረጋገጥ—አባትነትን በማወቅ የተሰጠን ቃል ለማረጋገፍጥ ሊቀርብ ስለሚገባው ማስረጃ ፡፡

የፍትሐ ብሔር ሕግ 747 ፡ 748 ፡ 751 ፡ 752 ፤

ይግባኝ ባይዋ ከጋብቻ ውጭ በተፈጸመ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት የወለደቻት አየለች ወልደገብርኤል የሚች የአቶ ወልደገብርኤል ተክለማርያም ልጅ መሆኗ ይረጋገጥልኝ በማለት ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርባ ፡ ፍ/ቤቱ አመልካቿ የቆጠረቻቸው ምስክሮች ያስረዱት ፍሬ ነገር ስለማይታመን ጥያቄዋ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ይግባኝ ነው ፡፡

ውሳኔ ፦ ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ አየለች የአቶ ወልገብርኤል ተክለማርያም ልጅ ናት ተብሎ ተበይኗል ፡፡

1. በሕግ ከታወቁት ግንኙነቶች ውጭ የተወለደ ልጅ የአባቱን ማንነት ለማረጋገጥ የሚችለው አባቱ ነው የተባለው ሰው አባትነቱን ያወቀለት ከሆነ ነው፡፡
2. በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 748/2/ በተደነገገው መሠረት አባትነት ማወቅ ውጤት የሚኖረው በጽሑፍ ከሆነ ነው ፡፡
3. አባትነትን በማወቅ የሚሰጥ ቃል በጽሑፍ መሆን ካለበት ቃሉን ለማስረዳት የሚቀርበው ማስረጃ ጽሑፍ እንዲሆን የግድ ነው ፡፡
4. በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 146 ከተደነገገው ውጭ አባትነትን በማወቅ የተሰጠን ቃል በምስክሮች ማረጋገጥ አይቻልም ፡፡
5. በፍ. ሕ. ቁጥር 747/2/ መሠረት አባትነትን በማወቅ የሚሰጥ ቃል የአባትነትን ውጤት እንዲያስከትል ታስቦና ታቅዶ መደረግ ስለሚያስፈልገው ፤ በቁጥር 748/2/ መሠረት ደግሞ ጽሑፉ አባትነቱን በሚያውቀው ሰው በግል ያልተጻፉ ሌሎች ነዋሪ ሰነዶችንም የሚጨምር መሆን ስለሚገባው ፤ አየለች የአቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም ልጅ መሆኗን በማረጋገጥ በምትማርበት ተቋም ተመዝግቦ የተገኘው ፍሬ ነገር ብቁ ማስረጃ ሆኖ ተቀባይነት የማያገኝበት ምክንያት የለም ፡፡

ታኅሣሥ 14 ቀን 1975 ዓ ም ዳኞች መክብብ ጸጋው በየነ አብዲ መኰንን አናጋው ፡፡

ይግባኝ ባይዋ ሙሉነሽ ዓለሙ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበችው የክስ አቤቱታ ፡ ከመዋቹ ከአቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም ጋር በነበረን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ተማሪ አየለችን ወልጄላቸዋለሁ ፡ መዋቹ አየለች ልጃቸው መሆኗን ተቀብለው ልብስ ሲሰጡና ቀለብ ሲሰፍሩ ለዘመድ ለወዳጅ አስታውቀው ሲያስተምሯት ቆይተዋል ፡፡ ስለዚህ ተማሪ አየለች የአቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም ልጅ

መሆኗ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ የሚል ነው ። መልስ ሰጭ የመዋቹ ባለቤት ስትሆን ይግባኝ ባይዋ ያቀረበችውን ጥያቄ ተቃውማለች ። መቃወሚንም የመሰረተችው መዋቹ ልብስም ሰጥተው ፣ ቀለብም ሰፍረው አያውቁም ፣ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ሕጉ በሚያዘው መሠረት ልጅነቷን በጽሑፍ አልተቀበሏትም ፣ መዋቹ ልጅነቷን በጽሑፍ ካልተቀበሏት በቀር ያቀረበችው ጥያቄ ውጤት የለውም ፣ ልጅነቷን በምስክር ልታስረዳ አትችልም በሚሉ ነጥቦች ላይ ነው ። ከፍተኛው ፍርድ ቤት በግራቀኙ በኩል የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የአመልካቿ ምስክሮች ያስረዱት ፍሬ ነገር አይታመንም ሲል ጥያቄዋን ባለመቀበል መስከረም 29/1972 ዓ ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቷል ። የአሁኑ ይግባኝ የቀረበውም ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው ።

በዚህ ጉዳይ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገርና በሕጉም ስለአባትነት ማረጋገጥ ጉዳይ የተጻፉትን ድንጋጌዎች በሚገባ መርምረናል ። እንደመረመርነውም አየለች ወልደ ገብርኤል የአባቷን ማንነት ለማረጋገጥ መነሻ ያደረገችው እናቷ፣ አባት ነው ከተባለው ከወልደ ገብርኤል ተክለማርያም ጋር የጋብቻ ወይም እንደባልና ሚስት የሚቆጠር ከጋብቻ ውጭ የሆነ ግንኙነት ነበረው በማለት አይደለም ። አየለች ተወለደች የተባለው ከጋብቻ ወይም ጋብቻን ከሚመስል ግንኙነት ውጭ ነው ። እንደልማዳዊ አጠራሩ በዲቃላ የተወለደች ልጅ መሆኗ ነው ። በዚህም ምክንያት አየለች አባት ነው ከተባለው ሰው መወለዷን በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 740/1/ ወይም 745/1/ በተጣሉት ግምቶች ማስረዳት አይቻላትም ። አየለች ዲቃላ በመሆኗ የመዋቹ ልጅ ነኝ ለማለት የምትችለው ይኸው ሰው አባትነቱን አውቆልኛል በማለት ነው ። /ቁ. 742/ ። አባትነትን ማወቅ ውጤት የሚኖረው በጽሑፍ ከሆነ ነው ፣ / ቁ. 748/1 በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 146 ሕግ ቁጥር 146 ከተደነገገው ውጭ የአባትነትን ማወቅ በምስክሮች ማረጋገጥ አይፈቀድም (ቁ. 748/2/) ። እርግጥ በቁጥር 146 የተጻፈው ድንጋጌ እስካሁን እሥራ ላይ አልዋለም ። በሕጉ በታቀደው መሠረት የክብር መዝገብ ጽ/ቤት በኢትዮጵያ አልተቋቋመም ። የክብር መዝገብ ጽ/ቤት ባለመቋቋሙም አስቀድሞ የተመዘገበ ነገር ስለማይኖር ዳኞች በቁጥር 146 መሠረት በምስክሮች እንዲጣራ የሚፈቅዱት ነገር የለም ። በዚህ አንጻር የአሁኑ ጉዳይ ሲታይ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይዋ አባቴ ነው የምትለው ሙዋቹ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም አባትነቱን ያወቀላትና ልጅነቷን የተቀበላት መሆኑን ቀድሞውንም በምስክሮች እንድታስረዳ የፈቀደላትና የቆጠረቻቸውንም ምስክሮች አስቀርቦ የሰማላት በማይገባ ሆኖ አግኝተነዋል ።

እንግዲህ በ1953 ዓ ም በወጣው የፍትሐ ብሔር ሕግ አባትነትን ማወቅ በጽሑፍ ካልሆነ በቀር ውጤት አይኖረውም ። ይህን ድንጋጌ ማውጣት ያስፈልገው ከ1953 ዓ ም በፊት የነበረው የአባትነት ማረጋገጥ ሥርዓት ነው ። ሕጉ ከመውጣቱ በፊት አባትነት የሚረጋገጥበት የታወቀ ደንብ ባለመኖሩ ፣ መወለድን በማንኛው ዓይነት ማስረጃ ከማስረዳት የሚከለከል ነገር አልነበረም ። ይህም የተዝረከረከ የማስረጃ አቀራረብ ሁኔታ አስከፊ ውጤትን ማስከተሉ አልቀረም ። የሥርዓቱ ልልነት አንድን ሰው በሀብትና በማኅበራዊ አቋሙ በመምረጥ ልጅን ለማስታቀፍ የተመቸ ነበር ። በተለይ እናት በማለች ብቻ አባትነት የሚታወቅበት ጊዜ በመኖሩ ይህዓይነቱ ማስረጃ ብቁ ነው መባሉና ተቀባይነት ማግኘቱ እውነተኛው አባት ቀርቶ እናት ልጅዋን ለፈለገችውና ለመረጠችው ሰው ለመስጠት ያስችላት እንደነበረ የታወቀ ነገር ነው ። ከእናት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከፈጸሙ ወንዶች አንዱን ከሌላው በማማረጥ ልጅን በሀብቱና በማኅበራዊ አቋሙ የተሻለ ሆኖ ለተገኘው አባት ማስታቀፉ እየተስፋፋ በመሄዱ ፣ የኢትዮጵያን ሕጎች ዘመናዊ ለማድረግ በመምከር የጋብቻ ሕጉ ሲጻፍ ይኸው ጉዳይ በሚገባ ታስቦበታል ። ዛሬ

በመሥራት ያለው የፍትሐ ብሔር ሕግ በ1952 ዓ ም ሲወጣ ስለጋብቻ በተጻፉት ድንጋጌዎች በአንድ በኩል ልጅ ያለአባት እንዳይቀር ፣ ከሌላ በኩል ደግሞ አባት ያልሆኑ ሰዎች አላግባብ አባት እንዳይሆኑ ጥረት ተደርጓል ። ልጅ ያለአባት እንዳይቀር ጥረት የተደረገው በጋብቻና ጋብቻ ሳይኖር እንደ ጋብቻ በሚቆጠር ግንኙነት የተወለዱትን ልጆች አባትነት በሚመለከት ረገድ ነው ። በጋብቻ የተወለደ ልጅ የእናትየዋ ባል ልጅ (ቁጥር 740) ፤ እንዲሁም ጋብቻ ሳይኖር እንደ ጋብቻ በሚቆጠር ግንኙነት የተወለደ ልጅ እናትየዋን ይዞ የተቀመጠው ሰው ልጅ (ቁ.745)፣ እንደሚሆን በሕጉ ግምት ተጥሏል ። የመወለድ ጥያቄ አስቸጋሪ የሚሆነው ከጋብቻና እንደ ጋብቻ ከሚቆጠር ግንኙነት ውጭ በተፈጸመ ሩካቤ ሥጋ የተገኘ ልጅ አባት ማንነት በሚረጋገጥበት ጊዜ ነው ። ሕጉም ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደረገው በዲቃላ የተወለደ ልጅ አባት የሚታወቅበትን ደንብ በማጥበቅ አባት ያልሆነ ሰው በማያስተማምን ማስረጃ ያልወለደው ልጅ አባት ነህ እንዳይባል ነው ። በዚህ ምክንያት የአባቱ ማንነት በሕጉ ግምት ያልታወቀለት ልጅ መወለዱን ማረጋገጥ የሚቻለው አባቴ ነው የሚለው ሰው ያወቀውና የተቀበለው ከሆነ ነው ። አባትነትን ማወቅ ደግሞ በጽሑፍ እንዲደረግና ማስረዳትም የሚቻለው በጽሑፍ ማስረጃ መሆን እንዳለበት በሕግ ታዞአል ። ሕጉ ሲነደፍ በዲቃላ የተወለደን ልጅ አባትነት ማወቅ በጽሑፍ እንዲሆን ያነሳሳውና የገፋፋው ምክንያት ምን እንደሆነ ከፍ ብለን ገልጠነዋል ። ሕጉ ከመውጣቱ በፊት የነበረውን የተዝረከረከ አሠራር ሥርዓት ለማስያዝና ልቅ በሆነ በማያስተማምን ማስረጃ አንድ ሰው ከእናት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በማድረጉ ብቻ በእናት ፍላጐትና ምርጫ የአባትነት ግዴታ እንዳይጣልበት ለማድረግ መሞከሩ ተገቢና ተቀባይነት ያለው ነገር ነው ። ነገር ግን አንዱን ችግር ለመወጣት ሲሞክር የሕጉ መጥበቅ የባሰ ሌላ ችግር አስከትሏል ። ሕጉ በሚወጣበት ጊዜ የዲቃላን ልጅ አባትነት ማረጋገጥ የሚቻለው አባት ነህ የተባለው ሰው ልጁን በጽሑፍ ካወቀውና ከተቀበለው ነው ተብሎ መደንገጉ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ችግር በሚገባ በማመዛዘን የተወሰደ እርምጃ ሆኖ አይታይም ። ሕጉ ከታወጀበት ጊዜ ከመቶ ዘጠና በላይ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንበብና መጻፍ የማይችል መሐይም እንደነበረ የሚያከራክር አይደለም ። ዛሬም ከሃያ ዓመታት በኋላ ትክክለኛው መቶኛ በውሉ ተለይቶ አይታወቅ እንጂ በቅርቡ የተጀመረው ዘመቻ ሙሉ በሙሉ ውጤት እስኪያገኝ ድረስ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከማሐይምነት እንዳልተላቀቀ አፍ የሚያካፍት አይመስለንም። ታዲያ ይህ ዓይነቱ ነባራዊ ሁኔታ የነበረና ያለም መሆኑ እየታወቀ ስንቱ ሰው መጻፍና ማንበብ ችሎ ነው በዲቃላ የተወለደን ልጅ አባትነት ማወቅ ውጤት የሚኖረው በጽሑፍ ከተደረገ ነው ተብሎ የተደነገገው የሚለው ነገር በብዙ ሰዎች በተለይም በዳኞች አእምሮ ሁሉ ጊዜ የሚጉላላ ጥያቄ ነው ። የማንበብና የመጻፉ ችሎታ ብቻ ሳይሆን ችሎታው እንኳ ቢኖር በጽሑፍ አባትነትን የመቀበል ነገር በብዙ ሥነ ልቦናዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች የተወሰነ ነው ። ስንት አባቶች ናቸው በዲቃላ የወለዱትን ልጅ አባትነታቸውን በጽሑፍ በማወቅ ነገሩን ይፋ ለማድረግ ፈቃደኛ የሚሆኑት ? ፤ ስንትስ እናቶች ናቸው አባት ነህ የተባለውን ሰው የጽሑፍ ማረጋገጫ ሰጠን ብለው አስቀድመው ለመጠየቅ የሚቃጡት ? ዳኛው የሚኖረው በኅብረተሰብ ውስጥ ፡ የሚዳኛቸውም ባለጉዳዮች የኅብረተሰቡ አባላት በመሆናቸው ፡ እነዚህን ሁሉ ነባራዊ የግልና ማኅበራዊ ችግሮች ይገነዘባቸዋል ። እርግጥ ዳኛው ችግሩን ብቻ መሠረት አድርጎ የተጻፈውን ሕግ ወደ ጐን ትቶ በራሱ አስተያየትና ርትአዊ ዝንባሌ ይፈርድ ዘንድ አይቻለውም ። ዳኛው ሊያደርግ የሚችለው ነገር ቢኖር ሕጉ አሻሚ በሚሆንበት ጊዜ የአካባቢውን ሁኔታ በማመዛዘን መሆን ይገባዋል ብሎ በሚያምንበት መንገድ ለሕጉ ድንጋጌዎች ተገቢውንና ተስማሚውን ትርጓሜ መስጠት ነው ። በያዝነው ጉዳይ ለሁለቱ ወገኖች ክር

ክር አግባብነት ያለው በቁጥር 748(1) የተጻፈው ድንጋጌ ነው ። በዚህ ድንጋጌ አባትነትን ማወቅ በጽሑፍ መሆን አለበት ሲባል ጽሑፉ በማን ፣ ለምንና እንዴት መደረግ ይኖርበታል የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ እናገኘዋለን ። በተለይም በቁጥር 747/2/ አንድ ሰው አባትነቱን በማረጋገጥ የሚሰጠው ቃል አባትነትን የማወቅ ውጤት እንዲያስገኝ ታስቦና ታቅዶ መሆን የለበትም ተብሎ መደንገጉ አሻሚነቱን የበለጠ ጉልህ ያደርገዋል ። ሕጉ ሲወጣ አብዛኛው ሕዝብ ማንበብና መጻፍ እንደማይችል አስቀድሞ ሲረቀቅ በኋላም ተመክሮበትና ተዘክሮበት በሚታወጅበት ጊዜ ይዘነጋል ብለን አንገምትም ። ይህ ካልተዘነጋ ደግሞ የተፈለገው ክብደት ያለው በጽሑፍ የሰፈረ ማስረጃ እንጂ ጽሑፍ አባትነቱን በሚያውቀውና በሚቀበለው ሰው የግድ መደረግ ይኖርበታል ተብሎ ነው እንልም ። አሳብና ፈቃዱ አባት ነህ የተባለው ሰው መሆን ይኖርበታል እንጂ አባትነቱን የሚያውቀው ሰው ቃሉን ሶስተኛ ሰው በጽሑፍ እንዲያሰፍርለት በማድረግ ጽሑፉን ራሱ በፊርማው ሊያረጋግጠው ይችላል ። ረቂቁን ያዘጋጁት ምሁርና በኋላም ሕጉን ያወጣው ክፍል አባትነትን ማወቅ በጽሑፍ ካልሆነ ውጤት የለውም ሲል በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረውንና ያለውን የመሐይምነት ሁኔታ ጭራሽ ካልዘነጉት በቀር ጽሑፍ በሶስተኛ ሰው ሊዘጋጅ ይችላል በሚል ግምት ተነሳስተው ነው እንላለን ። አፈጻጸሙ በዚህ መልክ እንደሚሆን ታስቦና ታቅዶ ነው ብንል እንኳ ፣ ችግሩን በከፊል እንጂ በሙሉ አንወጣውም ። አባትነቱን ያወቀው ሰው ማንበብና መጻፍ ባለመቻሉ ቃሉን በሶስተኛ ሰው አጽፎ የጣት ምልክት ፊርማውን በጽሑፍ ግርጌ በሚያሰፍርበት ጊዜ በዚሁ ሕግ ቁጥር 1728/3 የተጻፈው ድንጋጌ ሳይሙዋላ ይቀርና ሌላ ችግር ይዞ ብቅ ሊል ነው ። አባትነቱን ያወቀው ሰው መሐይም ከሆነ ፣ በቁጥር 1728/3/ በተነገረው መሠረት ፊርማውን የውል አዋዋይ ሹም ወይም ሬጅስትራር ወይም ዳኛ በሥራው ላይ ሆኖ ካላረጋገጠው ላያስገድደው ነው ማለት ነው ። እንኳን ለድብቅነት ከፍተኛ ዝንባሌ ያለው በዲቃላ የተወለደ ልጅን አባትነት በማወቅ የሚሰጠው ቃል ቀርቶ ፣ ግልጥ የሆኑት ሌሎች የፍትሐ ብሔር ተግባራት ሲፈጸምም በቁጥር 1728/3/ የተጻፈው ድንጋጌ ሁሉ ጊዜ ተመዋልቶ አይገኝም ። አባትነትን በማወቅ የተሰጠ የጽሑፍ ማስረጃ ቢቀርብ እንኳ በሕግ የታዘዘውን ፎርማሊቲ አሙዋልቶ የማይገኝ በመሆኑ ፣ ይህም ሌላ ክርክር ሊያስነሳ ነው ።

ይህ ብቻ አይደለም ። በዲቃላ የተወለደ ልጅን አባትነት በማወቅ የሚሰጥ ቃል በጽሑፍ መሆን አለበት ከተባለ ፣ ነገሩ የፎርምን ጉዳይ የሚመለከት ነውና ጽሑፉ ውጤት እንዲኖረው በሁለት ምስክሮች እንዲረጋገጥ የግድ ነው የሚል አስተሳሰብ አይጠፋም ። ይህን የአስተሳሰብ ፈለግ ከሚከተሉት አንዱ ፕሮፌሰር ጆርጅ ችችኖቪች ናቸው ። ችችኖቪች “ ሙወለድ በኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ ” በሚለው ጽሑፋቸው አባትነትን ማወቅ በጽሑፍ ሁኖ በሁለት ምስክሮች ፊርማ መረጋገጥ አለበት የሚል ትችት ሠንዝረዋል (የኢ. ሕ. መጽሔት ቅጽ 3 ቁጥር 2 ገጽ 497) ። ችችኖቪች እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሱት በቁጥር 748 የተጻፈውን ድንጋጌ ከቁጥጥር 172/2/ ጋር አጣምሮ በማየት ይመስላል ። ቁጥር 1727/2/ የሚገኘው በፍትሐ ብሔር ሕግ የውልን ጉዳይ በሚመለከተው ክፍል ነው ። እንደ ሚታወቀው ሁሉ ውል የሁለት ወገኖችን ፈቃድና ድርድር የሚመለከት ነገር ነው ። አባትነትን በማወቅ የሚሰጥ ቃል ግን በአንድ ወገን የሚፈጸም ተግባር ነው ። እርግጥ አባትነትን በማወቅ የሚሰጥ ቃል መሠረት ያለው መሆኑን እናት እንድንታጸድቀው (ቁጥር 751/1/ ፣ እንዲሁም ልጁ አካለ መጠን ሲያደርስ እንዲቀበለው ያስፈልጋል (ቁ. 752) ። እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ግን አባትነትን በማወቅ የሚሰጥ ቃል እናት እንድታጸድቀውና ልጁም አካለ መጠን ሲያደርስ እንዲቀበለው ያስፈልጋል ሲባል ተግባሩ በውል ድርድር ዓይነት የሚፈጸም አለመሆኑን ነው ። ከዚ

ህም ሌላ አባትነትን በማወቅ የሚሰጥ ቃል በጽሑፍ ሆኖ በምስክሮች መረጋገጥ አለበት ከተባለ ፡ በቁጥር 747/2/ የተጻፈው ድንጋጌ ዋጋ ቢስ ሊሆን ነው ። ጽሑፉ በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ የሚያስፈልገው ቢሆን ኑሮ አባትነትን በማወቅ የሚሰጥ ቃል የአባትነትን ማወቅ ውጤት እንዲያስገኝ ተብሎ መደረግ የለበትም የሚለው ድንጋጌ ባላስፈለገም ነበር ። አባትነትን በማወቅ ፡ የሚሰጥ ቃል የአባትነትን ማወቅ ውጤት ማወቅ ውጤት እንዲያስገኝ ታቅዶና ታስቦመሆን አያስፈልግውም ተብሎ ከተደነገነገ ሰነዱ ለሌላ ነገር ታቅዶ የአባትነትን ማወቅ እግረመንገዱን የሚሰጥ ማረጋገጫ ስለሆነ ፡ በጽሑፍ ላይ ምስክሮች እንዲፈርሙበት ያስፈልጋል ሊባል አይቻልም ። ለዚህም ግልጥ አስረጂ ሊሆነን የሚቻለው ደብዳቤ ነው ። በደብዳቤ አባትነትን በማወቅ እግረ መንገዱን ማረጋገጫ ሊሰጥ ይቻላል ። ማንም ሰው ቢሆን ደብዳቤ ለዘመዱና ለወዳጁ ሲጽፍ ምስክሮች አያስፈልግም ። ሌላው ለአንድ መሥሪያ ቤት የሚጻፍ አቤቱታ ነው ። አባት ነህ የተባለው ሰው በአቤቱታው ውስጥ አባት መሆኑን እግረ መንገዱን ቢጠቀስ ፡ አቤቱታው በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ አለበት አይባልም ። ለአንድ መሥሪያ ቤት የሚጻፍ አቤቱታ ምን ጊዜም ቢሆን በምስክሮች አይረጋገጥም ። ይህን ሁሉ ሕጉን በትክክል ከተረጐምነው ክርክሩ አያስኬድም ለማለት እንዲያው ለነገሩ አነሳነው እንጂ ድንጋጌው በመጀመሪያ ሲነደፍ አባትነትን በማወቅ የሚሰጥ ቃል በጽሑፍ ሆኖ በአራት ምስክሮች መረጋገጥ አለበት የሚል ነበር ።

የፍትሐ ብሔር ሕጉን ያረቀቁት ፕሮፌሰር ሬኔ ዳቪድ " የጋብቻ ሕግ በኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ " ከሚለው ማብራሪያቸው እርሳቸው አባትነት ማወቅ በአራት ምስክሮች መረጋገጥ ይኖርበታል ያሉትን ኮሚሽኑ በምርስክሮች መረጋገጥ ይኖርበታል የሚለውን ክፍል ሠርዞ ድንጋጌውን አሁን ባለበት ቅርጹ እንደተወው ገልጠውታል / ገጽ 66 ፡ ግርጌ ማስታወሻ ቁ. 103ን ይመለከታል ። በዚህም ምክንያት አባትነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ጽሑፍ በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ ይኖርበታል የሚለው ክርክር እምብዛም ክብደት ያለው ሆኖ አይታይም ። ክብደት ባይኖረውም ይህ የክርክር ነጥብ አስቀድሞ የተነሳና ወደፊትም የሚነሳ በመሆኑ አባትነትን በማወቅ የተሰጠውን ቃል ለማስረዳት የሚቀርብ የጽሑፍ ማስረጃ ምን ያህል አወዛጋቢ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም ።

እንግዲህ ይህን ሁሉ ችግር አጣምረን ስናየው በዲቃላ የተወለደን ልጅ አባትነት በማወቅ ረገድ የተፈለገው ግልጥና አስተማማኝ የሆነ በጽሑፍ የሠፈረ ማስረጃ እንጂ ፡ ጽሑፉ ሁል ጊዜ የግድ አባትነቱን በሚያውቀው ሰው መዘጋጀትና መረጋገጥ አለበት ተብሎ ነው አንልም ። ለምሳሌ አንድ ሰው ፍርድ ቤት ቀርቦ በሌላ ጉዳይ የምስክርነት ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ እግረ መንገዱን " ከልጄ ከእገሌ ጋር ሆኜ እንዲህ በማድረግበት ጊዜ ይህን ወይም ያን ሁኔታ ተገነዘብኩ " በማለት የሚሰጠው ቃል በመዝገብ ሠፍሮ ሊገኝ ይችላል ። ከጊዜ በኋላ እገሌ ተብሎ የተጠቀሰው ልጅ ከዚሁ ሰው መወለዴ ይረጋገጥልኝ በማለት አቤቱታ አቅርቦ አባት ነህ የተባለው ሰው ቀደም አድርጐ በሌላ ጉዳይ ያስመዘገበውን የምስክርነት ቃል በአስረጂነት ቢቆጥር ፡ ይህ በፍርድ ቤት መዝገብ ሰፍሮ የሚገኘው ፍሬ ነገር ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ለማለት ይቻላልን ? በእኛ አስተያየት ፍርድ ቤት እምነት የሚጣልበት የሕዝብና የመንግሥት ባለአደራ በመሆኑ ፡ ባለጉዳዩ በፊርማው ባያረጋግጠውም በመዝገብ ሠፍሮ የተገኘው ፍሬ ነገር ብቁና አስተማማኝ ተብሎ ማስረጃነቱ ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል እንላለን ። ፍርድ ቤቱ የገለልተኛነት አቋም ያለው ወይም ይኖረዋል ተብሎ የሚገመት በመሆኑ በመዝገቡ ውስጥ ሠፍሮ የሚገኘውን ፍሬ ነገር አስረጂነቱን አንጠራጠረውም ። በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 747 /2/ አባትነህ የተባለው ሰው የሚሰጠው ቃል በተለይ የአባትነትን ማወቅ

ውጤቶች እንዲያስከትል ተብሎ የተደረገ መሆን አያስፈልገውም ተብሎ ሲደነ
ገግ እንደዚህ ዓይነቱን ሁኔታም እንዲጨምር ነው ብለን እንገምታለን ፡፡

የአሁኑን ጉዳይ በምናጣራበት ጊዜ አቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም በወ/
ሮ ቀለመወርቅ ትምህርት ቤት በሚሠራበት ጊዜ አየለችን በ1965 ዓ ም እዚሁ ትም
ህርት ቤት አስገብቷት እስከ 1971 ዓ ም ድረስ ስትማር መቆየቷን ትምህርት ቤቱ
ጥቅምት 11/1972 ዓ ም በቁጥር 39/65/11 በተጻፈ ደብዳቤ አረጋግጦልናል ፡፡ አቶ
ወልደ ገብርኤል አየለችን ስለማንና በምን ሁኔታ እዚሁ ትምህርት ቤት ሊያስገባት
እንደቻለ ጉዳዩን የሚያውቅ የትምህርት ቤቱ ባለሥልጣን አግባብነት ያላቸውን
ማስረጃዎች ይዞ ቀርቦ ሁኔታውን እንዲያስረዳን አድርገናል፡፡ባለሥልጣኑንም የጠራ
ነው የአባትነት ማወቁን ነገር በግል አስረጅነት እንዲያረጋግጥ ሳይሆን በትምህ
ርት ቤቱ መዝገብ ምን እንደሠፈረና በምን ሁኔታ ሊመዘገብ እንደቻለ ፣ እንዲሁም
የትምህርት ቤቱን የአሠራር ሁኔታ እንዲያስረዳን ነው ፡፡ በዚህም መሠረት የትም
ህርት ቤቱ ጸሐፊ አቶ ማርቆስ ይልማ ቀርቦ አቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም
ዘበኛ እንደነበረ ፣ የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ከአብራካቸው የተከፈሉትን አንዳ
ንድ ልጆች እዚሁ ትምህርት ቤት እንዲያስገቡ በተፈቀደው መሠረት አቶ ወልደ
ገብርኤልም በ1965 ዓ ም አየለች ከአብራኩ የተከፈለች ልጁ መሆኗን ገልጠ እንድ
ትማር ያስመዘገባት መሆኑን ፣ ልጅቱም አየለች ወልደገብርኤል ተብላ ተመዝግ
ባና የአቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም ልጅ መሆኗ በትምህርት ቤቱ ዘንድ ታ
ውቆ እስከ 1971 ዓ ም በዚሁ ትምህርት ቤት ስትማር መቆየቷን አረጋግጦልናል ፡፡
የትምህርት ቤቱ ጸሐፊ አቶ ወልደ ገብርኤል ተክለ ማርያም አየለችን በሚያስመ
መዘግብበት ጊዜ በቃል እንጂ በጽሑፍ የጠየቀውና በአየለች ሪፖርት ካርድ ላይም
በፊርማው ያረጋገጠው ነገር አለመኖሩን ገልጦልናል ፡፡ ይህም እንዴት ሳይደረግ
እንደቀረ ጠይቀነው ፣ ስለማስመዝገቡ መዋቹ የትምህርት ቤቱ ሠራተኛ በመሆ
ናቸው ልጄ ናት ብለው በቃል ካረጋገጡ በቂ እንደሚሆንና ሪፖርት ካርዱም መፈ
ረም አለመፈረሙን ትምህርት ቤቱ ምንጊዜም የማይቆጣጠረው ነገር እንደ
ነበረ አስረድቶናል ፡፡ እንግዲህ ይህን ሁሉ ስናየው የምንደርስበት መደምደሚያ
ምን መሆን ይገባዋል ? የወ/ሮ ቀለመወርቅ ትምህርት ቤት የመንግሥት ተቋም
ነው፡፡ በመንግሥት ተቋምነቱም ገለልተኛና የሕዝብን አደራ ጠባቂ ነው ብለን እን
ገምታለን ፡፡ ይህ ግምት በተቃራኒ ማስረጃ እስካልፈረሰ ድረስ ኃላፊዎቹ የሚያረ
ጋግጡትንና በመዝገቡ ሠፍሮ የሚገኘውን ፍሬ ነገር እንጠራጠረውም ፡፡ በያዝነው
ጉዳይ መዋቹ አቶ ወልደገብርኤል ተክለማርያም አየለች ልጁ መሆኗን በማረጋገጥ
እሚሠራበት ት/ቤት እንዲያስተምራት እንዲፈቀድለት በጽሑፍ የጠየቀው ነገር
ባይኖርም ፣ በአየለች ሪፖርት ካርድም ላይ ፊርማውን ባያሰፍርም ፣ እርሱ በሚሠ
ራበት ትምህርት ቤት ፣ የእርሱ ልጅ መሆኗን ራሱ በቃል ባረጋገጠው መሠረት
የእርሱ ልጅ ናት ተብላ በትምህርት ቤቱ ዘንድ ታውቃ ፣ አየለች ወልደገብርኤል
ተብላ ተመዝግባ ስትማር መቆየቷ ተረጋግጦልናል ፡፡ ከፍ ብለን የገለጥነው ግምት
እስካለ ድረስ የትምህርት ቤቱን ገለልተኛነትና ሐቀኛነት አንጠራጠረውም ፡፡ እዚህ
ላይ ሳናነሳውና ሳንተችበት የማናልፈው ነጥብ ቢኖር አንድ ሰው አባት ነኝ ብሎ
አንድን ልጅ ትምህርት ቤት ማስገባቱ ብቻ አባት መሆኑን አያረጋግጥም በማለት
ከአንዳንድ ወገኖች ሊሠነዘር የሚችለውን አስተያየት ነው ፡፡ በእርግጥም አስተያ
የቱ በተለይ በአሁኑ ጊዜ መሠረት እንደሚኖረው እናምናለን ፡፡ በትምህርት ቤት
አካባቢ የሚሠሩ አንዳንድ ሰዎች ከአብራካቸው ያልተከፈለውን ልጅ አባቱ ነኝ
በማለት የሚሠሩበት ትምህርት ቤት ሊያስመዘግቡና ሊያስገቡ እንደሚችሉ እንገ
ምታለን ፡፡ መታወቅ ያለበት ቁም ነገር ግን በመጀመሪያ ደረጃ በአሁኑ ጊዜ እንደ
ዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የተፈጠረው የተማሪዎች ቁጥር በመጨመሩና ትምህርት ቤቶች

በመጣበባቸው ምክንያት ነው ። ሁለተኛ ደግሞ በትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚሠሩ ሰዎች ራሳቸው ያልወለዱትን ልጅ አባት አስመስለው በማቅረብ የሚሠሩበት ትምህርት ቤት የሚያስመዘግቡትና የሚያስገቡት የማያውቁትን ሰው ሳይሆን የዘመዳቸውን ወይም የወዳጃቸውን ወይም የጐረቤታቸውን ልጅ ነው ። በያዝነው ጉዳይ አየለች ወ/ሮ ቀለመወርቅ ትምህርት ቤት የተመዘገበችበትን ጊዜና ሁኔታ ፣ እንዲሁም ሙዋቹ አቶ ወልደገብርኤል ተክለማርያም አየለችን ልጄ ናት ብሎ በሚሠራበት ትምህርት ቤት ለማስመዝገብና ለማስገባት ሊነሳሳበት የሚችለውን ምክንያት አዛምደን ስናየው ከፍ ብለን ለገለጥነው አስተያየት በር የሚከፍት ሆኖ አላገኘነውም ። እየለችም ወ/ሮ ቀለመወርቅ ትምህርት ቤት ተመዝግባ የገባችው በ1965 ዓ ም ነው ዛሬ 1973 ዓ ም በመሆኑ ከስምንት ዓመታት በፊት የነበረው የተማሪዎች ቁጥርና የትምህርት ቤቶች መጣበብ ባሁኑ ጊዜ ካለው ሁኔታ ጋር በምንም ዓይነት አንድ ሊሆን አይችልም ። ያን ጊዜ የተማሪዎች ቁጥር እንዳሁኑ አልበረከተም ፣ ትምህርት ቤቶች እምብዛም አልተጣበቡም ፡ ልጁን ወደ ትምህርት ቤት ለማስገባት በትምህርት ቤት አካባቢ የሚሠሩ ሰዎችን ርዳታ በመሻት የማስመሰል የአባትነት ግንኙነት መፍጠር ያስፈልግ ነበር አንልም ። ከዚህም ሌላ መዋቹ አቶ ወልደ ገብርኤል ተክለ ማርያምና የአየለች እናት እንዳችም የሥጋ ዝምድና የላቸውም ። ንጹህ ወዳጅ ነበረችም አልተባለም ። አባት ነህ የተባለው ሰውና የአየለች እናት የሚኖሩት በተለያዩ ሠፈሮች በመሆኑ ጐረቤቶችም አልነበሩም ። ታዲያ ይህን ሁሉ አገናዝበን ስናየው አቶ ወልደገብርኤል ተክለማርማም የአየለች እናት ዘመዱ ወይም ንጹህ ወዳጁ ወይም ደግሞ ጐረቤቱ ካልሆነች ፣ አየለችን እሚሠራበት ትምህርት ቤት ልጄ ናት ብሎ ያስመዘገባትና ያስገባት በእርግጥ ልጁ ብትሆን ነው የሚለውን መደምደሚያ የሚያጠናክር ሆኖ እናገኘዋለን ።

አየለች የአባቷ ማንነት እንዲረጋገጥላት ለፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረበችው ከተወለደች ከአሥራ አንድ ዓመታት በኋላ ነው ። አቤቱታውን በምታቀርብበት ጊዜ አባት ነው የተባለው አቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም በሞት ተለይቱል ። አቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም በሕይወት በነበረበት ጊዜ የአየለች መወለድ ክርክር አስነስቶ አደባባይ አልወጣም ። አንድ ሰው በፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ መብቱን ለማረጋገጥ የሚሞክረው ሌላው ወገን ግዴታውን ሳያከብርለት ሲቀር በመሆኑ ፣ አየለች አቶ ወልደገብርኤል በሕይወት በነበረበት ጊዜ አቤቱታ ሳታቀርብ አሥራ አንድ ዓመት ሙሉ የቆየችው አባቴ ነው ያለችው ሰው ልጅነቷን ስለተቀበላት ነው ብለን እንገምታለን ። አቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም ዛሬ በሕይወት ቢኖር ምናልባት ይህ ነገር ክርክር ማስነሳቱ እጅግ ያጠራጥረናል ። እርሱ በሕይወት ባለመኖሩም አሳቡን ልናውቀው አልቻልንም ። እርሱ በሞት በመለየቱ ምክንያት በቁጥር 750 በተደነገገው መሠረት በእግሩ ተተክተው አባትነቱን ለማወቅ በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው ወደ ላይ የሚቆጠሩ ዘመዶቹ እንዳሉ ፈቃዱን ያሙዋሉለት እንደሆነ ፤ በማለት አስቀርበን ለመጠበቅ ብንሞክርም እነርሱም አለመኖራቸውን ተረድተናል ። አቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም ከሕግ ሚስቱ ልጅ አላስወለደም ። ከይግባኝ ባይዋ እናት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም የተነሳሳውና አየለችንም ለማስወለድ የበቃው ያለልጅ እንዳይቀር በማሰብ ይመስላል ።

አቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም በዚህ አሳብ ተነሳስቶ አየለች ተወልዳ ለትምህርት ቤት ስትደርስ ልጄ ናት ብሎ በዘበኛነት በሚሠራበት ትምህርት ቤት አስገብቶ ፣ አየለች በትምህርት ቤቱ አስተዳደርና አካባቢ የእርሱ ልጅ መሆኗ ታ

ውቆ ፣ በእርሱ አባትነትን ስም ስትጠራና የመወለዷም ነገር አባት ነው የተባለው ሰው በሕይወት በነበረበት ጊዜ አንድም ክርክር ሳያስነሳ ቆይቶ ዛሬ እርሱ በሞት ሲለይ የአባቷ ማንነት የሕግን ቡራኬ እንዲያገኝ ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ሲቀርብ በነገሩ ለማያገባት ወገን ጥያቄውን ስለተቃወሙት ብቻ የሙዋቹን አሳብ እንዳናከሽፍበት ፣ ዓላማውን እንዳናደናቅፍበት ፣ ፈቃዱን እንዳናጓድልበት ብለን እንሠጋለን ። መልስ ሰጭዋ በነገሩ የማያገባት ወገን ናት ያልነውም ያለምክንያት አይደለም ። እርግጥ መልስ ሰጭና የሙዋቹ በሕግ የታወቀች ሚስት እንደነበረች አያከራክርም ። በሚስትነቷም ከሙዋቹ ጋር ጋብቻው ጸንቶ በቆየበት ጊዜ ያፈራቸውን የጋራ ሀብት ድርሻዋን የሚነፍጋት የለም ። መልስ ሰጭዋ የሙዋቹ ሚስት እንጂ ወራሽ ባለመሆኗ ፣ የአየለች ልጅነት ቢታወቅ የእርስዋ መብት በምንም ዓይነት አይነካም ። የአየለችን ጥያቄ መቃወም የሚችሉ በሙዋቹ ውርስ ተጠቃሚ የሆኑ ወገኖች ብቻ ነበሩ ። ነገር ግን ለሙዋቹ በሕግ ወይም በኑዛዜ ወራሽ ነኝ በማለት ከመልስ ሰጭዋ በቀር በተቃዋሚነት የቀረበ የለም ። መልስ ሰጭዋ ደግሞ የሙዋቹ የሕግ ወይም የኑዛዜ ወራሽ አለመሆኗን ከፍ ብለን ገልጠነዋል ። ከሙዋቹ ስላልወለዶች የራሴን እንኳ ባይሆን ለውርሱ በመጀመሪያ ደረጃ ተጠሪዎች ሊሆኑ የሚችሉትን የልጆቼን መብት አስከብራለሁ የማትለው ነገር ነው ። በአጭሩ አየለች የአቶ ወልደገብርኤል ልጅ መሆኗ ፣ ቢታወቅ በግለሰብ ደረጃ መብቱ የሚነካ አንድም ወገን የለም ። ምናልባትም በዚህ ነገር በከፊል ይጐዳል ከተባለ የሚጐዳው ኅብረተሰቡ ብቻ ነው ። የዛሬው ሕጻን የነገው ተተኪ ዜጋ በመሆኑ ፣ እስከተቻለ ድረስ የእያንዳንዱ ዜጋ የቤተሰብ ግንኙነት እንዳይበጠስ ፣ ማኅበራዊ አቋሙ እንዳይፋለስ ፣ ልጅ ያላባት ቀርቶና የዝምድና ሐረጉ ተቆርጦ ሸክም እንዳይሆን ኅብረተሰቡ አጥብቆ የሚያስብበት ጉዳይ ነውና በኅብረተሰቡ ላይ ሊደርስ የሚችለው ጉዳይት የአየለች አባት ማንነት በመታወቁና በመረጋገጡ ከሚሰጠው ጥቅም ጋር ሲመዛዘን በጣም አነስተኛ ነው ።

እንግዲህ ነገሩን ስናጠቃልለው አየለች በዲቃላ የተወለደች ልጅ በመሆኗ ፣ የአባቷን ማንነት ማረጋገጥ የምትችለው አባቴ ነው ያለችው አቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም አባትነቱን ያወቀላት ከሆነ ነው ። በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 146 ከተደነገገው ውጭ አባትነቱን አውቆለኛል ፣ ልጅነቴን ተቀብሎኛል የሚለው ነገር በምስክሮች ማረጋገጥ አይቻልም ። አባትነትን ማወቅ ውጤት የሚኖረው በጽሑፍ ከሆነ ነው ። ነገር ግን ሕጉ ሲወጣ በነበረውና በአሁኑም ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የመሀይምነት ሁኔታ አንጻር ሲታይ አባትነቱን አውቆልኛል የሚለውን ፍሬ ነገር ለማስረዳት የሚቀርበው የጽሑፍ ማስረጃ ሁሉ ጊዜ አባትነቱን በሚያውቀው ሰው የግድ መደረግ አለበት አይባልም ። ያባትነትን መታወቅ ለማስረዳት የሚቀርብ የጽሑፍ አስረጂ በማን ፣ ለምንና እንዴት መደረግ አለበት የሚለው ነገር በብዙ አቅጣጫ ሲታይ አሻሚና አከራካሪ ስለሆነ ፣ ሕጉ ከነበረውና ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ይጣጣም ከተባለና በቁጥር 748/1/ የተነገረው ድንጋጌ አባትነቱን በሚያውቀው ሰው በግል ያልተጻፉ ሌሎች ነዋሪ ሰነዶችንም የሚጨምር ከሆነ የተፈለገው ክብደት ያለው በጽሑፍ የሠፈረ አስተማማኝ ማስረጃ ነው የሚለው አስተሳሰብ ተገቢ ሥፍራ ሊሰጠው ይገባል ። ይህ ከሆነ ደግሞ አየለች ስትማርበት የነበረው የወ/ሮ ቀለመወርቅ ትምህርት ቤት ምንም እንኳ እንዲዚህ ዓይነቱን ጉዳይ እንዲያረጋግጥ በተለይ አደራ ባይጣልበትም ፣ ገለልተኛ ከሆነ ወይም ነው ተብሎ በሚገመት መንግሥታዊ ተቋም ተመዝግቦ የተገኘው ፍሬ ነገር በቁጥር 748/1/ መሠረት በታዘዘው ጽሑፍ ዘንግ የማይመደብበት ምክንያት የለም ። አየለች ከአቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም መወለዷ ቢረጋገጥ ፣ በግለሰብ ደረጃ መብቱ የሚነካበት ጥቅሙ የሚጓደልበት የሙዋቹ የሕግ ወይም የኑዛዜ ወራሽ አላገኘንም ። መ

ልስ ሰጭዋም የአየለችን ጥያቄ የተቃወመችው በነገሩ ውስጥ ለመግባት የሚያስ ችላት አንዳችም መብት ሳይኖራት ነው ። የአየለች መወለድ ምናልባት የተለየ ውጤት ሊያስከትል ይችል የነበረው ሙዋቹ በሕይወት ከነበረበት ጊዜ ቢክዳትና ክርክር ቢነሳ ነበር ። አቶ ወልደገብርኤል ተክለማርያም ግን በሕይወት በነበረበት ጊዜ የአባትነቱ ጥያቄ ክርክር ያላስነሳ በመሆኑ ፤ ዛሬም እርሱ በሕይወት ባ ኖር የአየለችን ልጅነት መካዱን አልፎ ተርፎም ነገሩ ክርክር አስነስቶ አደባባይ መውጣቱ እጅግ ያጠራጥረናል ። እያንዳንዱ የአባትነት ማወቅ ጥያቄ በኢትዮጵያ ግዙፍ ሁኔታዎች አንጻር እንደ ነገሩ ሁኔታ ታይቶና ተመዛዝኖ መወሰን ካለበት ፤ በተለይ በዚህ ጉዳይ የቀረበውን ማስረጃ የምንጥልበት አጥጋቢ ምክንያት አላገኘ ንም ። ስለዚህ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ ሽረን አየለች የአቶ ወልደ ገብርኤል ተክለማርያም ልጅ ናት በማለት ወስነናል ። ፍርዱ መሻሩን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይተላለፍለት ብለናል ።

የጠቅላይ ፍርድ ቤት

ፓናል

ይግባኝ ባይ አቶ ታደሰ ጉርሙ መልስ ሰጭ ወ/ሮ ጥሩወርቅ ኢያሱ
የፍትሐ ብሔር ይግባኝ መ. ቁ. 1111/74

ቤተዘመድ ፤ መወለድ ፤ አባትነትን ስለማወቅ ፤ ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብሮ ስለመኖር ፣

የፍትሐ ብሔር ቁጥሮች 708 ፡ 709 ፡ 718 ፡ 721 ፡ 740 ፡ 746—761 ፡ 769 ፣ 771 ፡

ይግባኝ ባይ ልጁ የእሱ ነው ሊያሰኝ የሚችል ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት የመኖር ሁኔታ በእኔና በከሣሽ መካከል ሳይኖርና ሌላ በቂ የመወለድ ማስረጃ ሳይቀርብ የከፍተኛ ፍ/ቤት ልጅህ ነው ሲል የተሰጠውን ውሳኔ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት የቀረበ ይግባኝ ነው ።

<u>ውሣኔ</u> ፡—የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ ጸንቷል ።

ከነገሩ አነሳስና አመጣጥ ሲታይ ተከሣሽ ከሳሽዋ ሆስፒታል ስትገባ ተያዥ ሆኖ መመዝገቡ ስልኩን ፤ መስጠቱና ገንዘቡ ሲመለስም በካርነው ላይ መፈረሙ በጽሑፍ የሕጻኑን አባትነት እንዳወቀ ስለሚያስቆጥረው ይግባኝ ባይ አቶ ታደሰ ጉርሙ የሕጻን ሰለሞን አባት ነው ።

ሐምሌ 13/1975 ዳኞች ቀኛ/ እንዳለው መንገሻ ፤ አቶ ዓለማየሁ ኃይሌ ፣ አቶ ጌታቸው አፍራሳ ፣ አቶ ሠይፉ ፈይሳ ፡ አቶ ሊበን አመዴ ፣ አቶ ጌታቸው ፍ/ማርያምና አቶ አስምሮም ሥዩም ።

ይህ ክስ የተመሠረተው በከፍተኛው ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የአሁን መልስ ሰጭ ተከሣሽ ደግሞ የአሁን ይግባኝ ባይ ናቸው ። ክሱም በ11/11/72 በተጻፈ ማመልከቻ ላይ የተመሠረተ ሆኖ ጥያቄውም ከሣሽና ተከሣሽ “ እንደባልና ሚስት ሆነው . . . ጥር 10/67 በጋንዲ ሆስፒታል ወልደዋል ። የሆስፒታል ተከሣሹ ከፍለዋል ፣ ለሕጻኑም ልብስ ገዝተዋል ። ተከሣሽ በኋላ ሃሳባቸውን ለውጠው መርዳት ስላቆሙ ” . . . ከጋብቻ ውጭ በወዳጅነት በአደረጉት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሕጻን ሰለሞን ታደሰ የተወለደ መሆኑን በማስረጃነትም የምስክሮች ዝርዝርና ከሣሽ ሆስፒታል ሲተኙ ተከሣሽ ገንዘብ ለማስያዛቸው ፣ ከሆስፒታል ሲወጡም ቀሪውን ገንዘብ ተከሣሽ ለመረከባቸው የሚገልጽ ካርኒ ወይንም ሰነድ ጠቅሰዋል ።

ተከሣሹም ቀርበው በ1/5/73 መልስ ሰጥተዋል ። ፍሬ ቃሉም ከሣሽዋ በሴትኛ አዳሪነት ከ1963—71 ድረስ የኖረች ናት ፣ እኔ ከወንድሞቼና ከእህቶቼ ጋር የምኖር እንጂ ከከሣሽዋ ጋር አልኖርኩኝም ፣ እንደባልና ሚስት (አንቀጽ 708) የሚለው ግንኙነትም በመካከላችን የለም ፡ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሕጋዊ ውጤት አያስከትልም ፡ ስለሆነም ልትከሰኝ አይገባም ፣ ከሣሽዋ መጠጥ ለመጠጣት የምሄደውን የምታስተናግድ እንጂ እንደምትለው በወዳጅነትም አብራኝ አልኖረችም፣ ሆስፒታል በገባችበት ዕለትም በአካባቢው ስለተገኘሁ በመኪና እርዳታ እንዳደርግ ተጠይቄ ወሰድኩኝ ፣ ለሆስፒታል የተከፈለውንም ገንዘብ ከሳሽዋ ሰጥታኝ አስይዤላታለሁ ፡ ገንዘቡ የተያዘው በስሜ ስለነበር ተራፊው ለማውጣት ፈረምኩኝ ፤ ልብስም አልገዛሁም ፣ ዘመዶቼም ስለጉዳዩ የሚያውቁት ነገር የለም በማለት በመካድ መልስ ሰጥተዋል ። በማስረጃነትም በሴተኛ አዳሪነትና የአልኰል

ንግድ በመነገድ ማንኛውንም ጠጪ በማስተናገድ የምትኖር የነበረችና የአለችም ለመሆኗ የሚያውቁ ምስክሮች ናቸው የተባሉ ፣ ተከሣሹ ከማንም ጋር እንደ ባልና ሚስት ግንኙነት ያልነበራቸው መሆኑ የሚያውቁ ምስክሮች ናቸው የተባሉ ዝር ዝር ፣ ከሣሽዋ በመጠጥ ነጋዴነት ትኖር የነበረ መሆኑን የሚጠቁም የንግድ ፈቃድ መኖሩን ገልጸዋል ።

በ25/5/73 ከሣሽ በጻፉት ማመልከቻ ንግድ ፈቃድ ቢኖረኝም ተከሣሹ እን ደባል ሆነው በቁጥጥራቸው ሥር ነበርኩ፡ የተጠቀሰው ሕግ የእኛን ግንኙነት አይ መለከትም ፤ "... ከሣሽ ... በወለዱ ጊዜ ልጁም የተጠሪው መሆኑን ተጠሪው ራሳቸው ስለሚያውቁ አመልካችዋን ጋንዲ ሆስፒታል አስገብተው የማዋለጃው ንም ሆ ነ የተኙበትን የሐኪም ቤት ውጪ ተጠሪው ..." የከፈሉ ናቸው ማስ ረጃው ተሰምቶ ልጅነቱ ይታወቅልኝ በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል ።

የከፍተኛው ፍ/ቤት ከጋንዲ ሆስፒታል የተጠቀሰውን ማስረጃ አስቀርቧል ። የማስረጃውም ፍሬ ቃል የበሽተኛው ስም ከነአባት ጥሩወርቅ ኢያሱ ፣ የሂሣቡ ሃላፊ ከፋይ ታደሰ ጉርሙ ስልክ 152025 የሚል ሆኖ " ቀኑም በ15/5/62 መሆኑን የሚ ያመለክትና የተፈረመበት ሲሆን በምስክርነትም ከከሣሽና ተከሣሽ ሌላ አራት ምስክሮችን ሰምቷል ። ከሣሽዋ ከተከሣሽ ጋር ግንኙነት የነበራቸው መሆኑን ፣ ልጅ እንዲወለድላቸው መፈለጋቸውን ፣ ሲወለድም የሆስፒታል ክፍያ ማድረጋቸውን ፣ የተለያዩትም በመጣላታቸው መሆኑን ፣ አንድ ጊዜ ከሣሽ ቤት ሌላ ጊዜ ተከሣሽ ቤት ማደራቸውን ፣ ከተከሣሽ ወላጆች ይሸሽጉ የነበረ መሆኑን ገልጸው መስክረ ዋል ። ሌሎች ምስክሮች ከሣሽና ተከሣሽ ወዳጅነት የነበራቸው መሆኑን አንዳንድ ወጭዎችን ተከሣሽ ለከሣሽ ይከፍሉ የነበረ መሆኑን መስክረዋል ።

ከተከሣሽ መከላከያ ምስክሮች ውስጥ አንደኛው ከሣሽዋ ከወንዶች ጋር ጓዳ የምትገባና የምትወጣ መሆኗን ፣ ጋብዙን እያለች ትጋበዝ የነበረ መሆኑን ፣ ከ ከ ሣሽ ጋርም አብረው ገብተው የጠጡ መሆናቸውን ሲመሰክር ፣ ሁለተኛው ምስክ ርም በተመሳሳይ ሁኔታ መስክሯል ። ሌሎች ምስክሮችም ከሣሽ ሌላ ሰው ወዳጅ እንደነበራቸው መስክረዋል ። የምስክሮቹ ቃል ከሞላ ጎደል ይህ ነው ።

ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከሣሽ የግብረ ሥጋ ግንኙ ነት የነበራቸው ለመሆኑ ፣ በመጨረሻም ሆስፒታል መውሰዳቸው ፣ ገንዘብ መክፈ ላቸውና የመሳሰሉት ሲታይ ተከሣሽ ልጁ ልጃቸው መሆኑን ያመለክታል ፣ የመከ ላከያ ማስረጃዎች ከሣሽና ተከሣሽ እንደባልና ሚስት አብረው መኖራቸውን ፣ ገን ዘብ መክፈላቸውን አያስተባብልም ፤ ተከሣሹ ከሣሽን እንደሚስት ይዞ በሚቀመጥ በት ጊዜ የተወለደ መሆኑ ስለተረጋገጠ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ያሳያል ፣ በመሆ ኑም ስለሞን ታደሰ የአቶ ታደሰ ልጅ ነው ሲል ወስኗል ።

ተከሣሽ ይህን ይግባኝ ያቀረቡት በዚህ ውሣኔ ላይ ነው ። ቅሬታውም የተመ ሠረተው ልጁን የእኔ ልጅ የሚያሰኘው በእኔና በከሣሽም መካከል እንደባልና ሚ ስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የለንም ፣ ገንዘቡ በስሜ መያዙ ሲለቀቅም ፊርማ መገ ኘቱ የራሴን ገንዘብ መስጠቴን እያመለክትም ፣ ለልጅነት በቂ ማስረጃ አይደለም የሚል ነው ። መልስ ሰጭዋም ቀርባ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲጸናላት ጠይ ቃለች ።

በመዝገቡ ውስጥ የሠፈረው ፍሬ ነገር በአጭሩ ይህ ነው ። አባትነት የሚታ ወቅበት ሁኔታ በፍ.ሕ. ቁ. 740 ላይ ተደንግጎ ይገኛል ። ይኸውም 1ኛ. ልጅ በተ ጸነሰበት ወይንም በተወለደበት ጊዜ በእናትየውና አባት ነው በሚባለው መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት ሲኖር (የፍ/ሕ. ቁ. 746—757) 2ኛ. አባት ልጅ ነው

ሲል የተቀበለ እንደሆነ (የፍሕ/ቁ. 746—757/ ፡ 3ኛ. እናት በመጠለፍ ወይንም በመደፈር ተገድዳ ስትገኝ ዳኛ ልጅህ ነው ሲል (የፍ/ሕ. ቁ. 758—761) ናቸው ፡፡

መልስ ሰጭዋ የሰለሞን ታደሰ ጉርሙ ልጅነቱ ይታውቅልኝ ስትል እላይ ከተ ገለጹት ሁኔታዎች ውስጥ የትኛውን አሟልታ ነው ? ይህን ከሕግ ጋር በማገናዘብ ለማየት እንሞክራለን ፡፡

በፍ. ሕ. ቁ. 740/1/ ላይ ሕጋዊ ግንኙነቶች የሚባሉት በፍ.ሕ. ቁ. 741 ላይ የተጠቀሰው የባልና ሚስት ግንኙነት ሲኖር ፣ ወይንም በፍ/ሕ. ቁ. 745 መሠረት ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ አብሮ የመኖር ግንኙነት ሲኖር ነው ፡፡ የመጀመሪያው ሕጋዊ ሁኔታ ግልጽ ሲሆን ሁለተኛው ሕጋዊ ግንኙነት ደግሞ በፍ. ሕ. ቁ. 708 ላይ የተገለጸው ሁኔታ ሲኖር ነው ፡፡ ይህም ሁኔታ ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት ሆኖ አብሮ መኖር ሲያጋጥም ነው ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በወንድየውና በሴትየዋ መካከል የግብረ ሥጋ ግንኙነት ተግባር በመፈጸሙ ወይንም በተለምዶ አንጋገር በወዳጅነት በማስቀመጥ ብቻ የሚመጣ ሳይሆን (አንቀጽ 721/709/3/ ተመል ከት) የአለው ግንኙነት በኅብረተሰብ መካከል እንደባልና ሚስት የሚያስቆጥር) (718/2/ ፡ 709/1/) ግንኙነት መኖሩን ማስረዳት ሲቻል ነው ፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ ያሉ ወንድና ሴት ሕግ በሚደነግገው መሠረት ጋብቻ መሥርተው አለመገኘታቸ ው ብቻ እንጂ በሌላ ሁኔታ ሲታይ ከባልና ሚስት ምንም ልዩነት የላቸውም ፡፡

መልስ ሰጭዋ ክሷን ስትመሠርት ከዚህ በላይ በፍ. ሕ. ቁ. 740 ላይ ከተደነ ገጉት ሁኔታዎች በየትኛው ላይ እንደምትመሠርት ግልጽ አድርጋ አላቀረበችውም። በክስ ማመልከቻው ላይ ተገልጾ የሚገኘው አንቀጽ የፍ.ሕ. ቁ. 771 ነው ፡፡ ይህ አን ቀጽ የሚያወሳው በፍ. ሕ. ቁ. 770 ላይ የተደነገገው የልጅነት ሁኔታ በምስክር ማስረዳት የሚቻል መሆኑን ነው ፡፡ ይህ ሕግ በመሠረቱ ልጅነትን ለማሳወቅ የማ ስረጃ አቀራረቡን ሥርዓት የሚመራ እንጂ ፤ፍ. ሕ. ቁ. 740 ውጭ ሌላ የልጅነት ማሳወቂያ ግንኙነት የሚጠቁም አይደለም ፡፡ በፍ.ሕ. ቁ. 740 ላይ የተደነገጉት ሁኔ ታዎች በአሉበት ወቅት ልጅነት በምስክር ወረቀት /የፍ. ሕ. ቁ. 769/ መረጋገጥ እንዳለበት ፣ ይህም በሌለበት ወቅት በምስክር ማስረዳት እንደሚቻል ቢገል ጽም በፍ. ሕ.ቁ. 740 ላይ ከተደነገገ ሁኔታዎች ውጭ ምስክር በማሰማት ልጅነትን ማስረዳት የሚቻል መሆኑን የሚጠቁም አይደለም ፡፡ ያም ሆነ ይህ ከሣሽ ለክሷ መ ሠረት የምታደርገው የትኛውን ነው ለሚለው ግልጽ ሆኖ ያልተጠቀሰ ቢሆንም በክስ ማመልከቻው ላይ ከሠፈረው የፍሬ ነገር ስሕተት ሁለት ሁኔታዎችን ለማስ ረዳት እንደሞከረች መረዳት ይቻላል ፡፡

እነዚህም ሀ. ልጁ በተወለደበት ወቅት በከሣሽና በተከሣሽ መካከል የባልና ሚስት ግንኙነት ባይሆንም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መኖሩን ፣ ለ. የአባትነትን የማወቅ ተግባር መፈጸሙን ማስረዳት ናቸው ፡፡

ከሣሽ ያቀረበቻቸው ማስረጃዎች ወይንም ምስክሮች ከሣሽዋ የመጠጥ ቤት ቢኖራትም በተከሣሽ ቁጥጥር ሥር የነበረች መሆኑን ፡ ለልዩ ልዩ ወጭዎች ይከፍ ልላት የነበረ መሆኑን ፡ አንድ ሌሊት ከሣሽ ቤት ሌላ ጊዜም ተከሣሽ ቤት በማደር ምሽቱን ያሳልፉ የነበረ መሆኑን በመልስና አንዳንድ ቦታዎችም ተጠርቶ አብሮ መገኘታቸውን በመመስከራቸው እንደባልና ሚስት አብሮ የሙኖር ግንኙነት መኖ ሩን ለማስረዳት ተሞክሯል ፡፡ ተከሣሽ በበኩሉ ከሣሽ የነበራት ግንኙነት ተከሣሽ ራሱ ካመነው ውጭ ከሌሎች ወንዶች ጋር እንደነበር ፣ ሌሎች ወንዶች ይጋብዟት የነበረ መሆኑን ፣ ትወጣ ትገባም የነበረ መሆኑን አከላክሏል ፡፡ ከሣሽም በሰጠችው ምስክርነት ቃል ላይ የተከሣሽን እናትና አባት ትሸሽ የነበረ መሆኑ ሲታይ ምንም

እንኳን በሁለቱ መካከል ወዳጅነት ቢኖርም ይህ ግንኙነታቸው እንደ ሕጉ አባባል እንደባልና ሚስት ይኖሩ ያልነበረ መሆኑን የሚያሳይ ነው ። በከሣሽ ዘመዶች ብቻ ተከሣሹ እንደባል መታየታቸው እንደባልና ሚስት ግንኙነት መኖሩን እያመለክትም ፡ ምክንያቱም ቤተዘመዶቻቸው የሚለው ቁ. 718/2/ ይህ ግንኙነት በግራ ቀኙ ጎረቤትና ቤተዘመዶችም ታቅፎ ሲገኙ ነው ። ከሣሽም ከሌሎች ወንዶች ብትጋበዝ ግን በግብረ ሥጋ ግንኙነት ከተከሣሹ ጋር ብቻ ተቆጥባ ብትኖርም ይህን እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ ተቀዳጅታለች ማለት አይደለም ። መጠጥ ቤት በመቀመጥ ግብዣ እየተቀበለች መኖሯ ይህ ዓይነቱ ግንኙነት የነበረ መሆኑን ከሚያሳይ ይልቅ ሁለቱ በዛ ቢል በወዳጅነት ተፋቅረው መኖራቸውን የሚጠቁም ነው ። ስለሆነም ሰለሞን ታደሰ የፍ. ሕ. ቁ. 740/1/ ፡ 745 በሚያነግገው መሠረት ከሣሽና ተከሳሽ እንደባልና ሚስት በመሆን አብረው ሲኖሩ የተወለደ ነው የሚለው አባባል ተቀባይነት ያለው አይደለም ።

ተከሣሹ የሰለሞን ታደሰን ልጅነት ተቀብለውታል የሚለውን አባባል ደግሞ እንመለከት ። ከሣሽ ይህን ሁኔታ ለማስረዳት የጠቀመችው ማስረጃ ልጅ ሲወለድ ተከሣሽ ተደስቶ እንግዳ መቀበሉን ፡ ልብስ መግዛቱን ፡ ወስዶ ማሳከሙና አንዳንድ ተናግሯቸዋል የተባለቸውን በማስመስከርና ሐኪም ቤት ወስዶ ከሣሽን ያስተኛ ለመሆኑ የሚገልጸውን የጽሑፍ ማስረጃ ነው ። በፍ. ሕ. ቁ. 746 ፡ 747/1/ ላይ አባት ነው የሚባለው ለልጅ አባት እኔ ነኝ ሲል በሚሰጠው ቃል እንደሚረጋገጥና ይህም በጽሑፍ መሆን እንዳለበት የፍ—ሕ. ቁ. 748/1/ ይገልጻል ። የጽሑፍ ማስረጃ በቀጥታ የልጅነቱን ማወቅ ተግባር ለመፈጸም ሲባል የተደረገ ሊሆንም ይችላል ። ወይንም በቀጥታ ይህን ውጤት ለማስገኘት ታቅዶ ሳይሆን የጽሑፍ ማስረጃ አባት ከሚባለው ሰው ሊደረግ ይቻላል የሚባሉትን ድርጊቶች ፈጽሞ መገኘት ነው ። እንቀጽ 747/2/ ለምሳሌ አንድ ሰው አንድን ልጅ ወስዶ ት/ቤት ሲያስገባ የልጅን አባት ሥም የራሱ ስም አድርጐ ቢያስመዘግብ ፡ ወይንም ይህን የመሳሰሉ ድርጊቶች ፈጽሞ ሲገኝ በማስረጃነቱ እየተመዘነ ተቀባይነት ሊኖረው እንደሚችል የዚህን አጻጻፍ ያስረዳል ። ከሣሽዋ ሆስፒታል በገባችበት ምሽት ተከሣሽ ከከሣሽ ቤት የነበረ መሆኑን ፡ ከዚያም ማታውኑ ከአንዲት ሌላ ሴት ጋር በመሆን ሆስፒታል እንደወሰዳት ሲመሰከር ፡ ሆስፒታል ደግሞ ለከሣሽዋ በገንዘብ አስያዥነት እንደተመዘገበ ፡ ስልኩን እንደሰጠ ፡ ገንዘብ ሲመለስም በካርኒው ላይ ተከሣሽ እንደፈረመ የተረጋገጠ ሲሆን እርሱም የካደው ነጥብ አይደለም ። ይህ የጽሑፍ ማስረጃ አባት መሆኑን አይጠቁምም ፡ ከከሣሽ የወሰደኩትን ገንዘቡ ባስይዝላት ፡ ተቸግራ ብረዳት ፡ ገንዘቡ ሲያዝም በመመዝገቡ ፡ ሲወጣም እንድፈርም ተጠርቼ መፈረም ለክሱ አግባብ ሊሆን አይችልም ሲል ተከራክሯል ።

አንድ በሽተኛ መንገድ ላይ ወድቆ አግኝቶ ሆስፒታል ሲያቀርቡትና የራሱን ወይንም የበሽተኛውን ገንዘብ በማስያዝ በዝንጋታ አስያዥነት ስምን አስመዝግቦ መገኘት ለሕክምናው ሃላፊነት አለብኝ ማለቱን ሊያመለክት ይችላል ። ነፍሰ ጡር ወድቃ ብትገኝና ሆስፒታል ገንዘብ በስም አስይዘው መገኘት ብቻውን የባልና ሚስት ግንኙነት መኖሩን ወይንም የሕጻኑን ልጅነት መቀበል ላያሳይ ይችላል ። ይህን መሳይ ማስረጃ በአጠቃላይ መልኩ የሚታይ ሳይሆን እንደነገሩ አመጣጥ እየታየ ይህ ማስረጃ ይህን ያመለክታል ፡ ይህ ደግሞ ይህን ግንኙነት አያመለክትም እየተባለ የሚወሰንበት ነው ። ተከሣሹ የተያዘው ገንዘብ የከሣሽ ነው ይበል እንጂ አንደ አባባሉ ለመሆኑ አላስረዳም ። ገንዘብ ሲመለስ ፈረምኩ እንጂ ተመላሹን ገንዘብ ለመውሰዴ አልተረጋገጠም የሚል ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም ። የከሣሽና ተከሣሽ ግንኙነት መንገድ ላይ ወድቆ እንደተገኘው ተረጂና እንደበጎ አድራጊው ሳምራዊ ያለ ግንኙነት ሳይሆን ከዚያም በፊት መሠረት ያለው ግንኙነት ያላ

ቸው ለመሆኑ ተመስክሯል ። እንደተከሳሽ አባባል ከአንዲት ሴት ጋር ብር 10.00 ከፍሎ ለአንድ ምሽት ብቻ ያሳለፈ ወንድ በመውለጃዪ ቀን በአጋጣሚ አካባቢው ተገኝቶ ሆስፒታል አድርሰኝ ሲባል ማድረስ ፣ ከዚያም ገንዘብ ከኪስ አውጥቶ በስም አስመዝግቦ ማስተኛት ፣ ለሌላ አጋጣሚም ቢፈለግ ሊገኙ የሚችሉበትን የስልክ አድራሻ በመተው ማስመዝገብ ያለበቂ ምክንያት ነበር ብለን አናምንም ። ከተነገረባቸው ግንኙነት አንጻር ይህ ድርጊት በፍ. ሕ. ቁ. 747/2/ 748/ 1/ መሠረት ልጅነትን ለማወቅ በቂ ማስረጃ ነው ብለን ተቀብለናል ።

ስለዚህ በተለያየ ምክንያት ቢሆንም ከፍተኛው ፍ/ቤት ሕጻን ሰለሞን ታደሰ የአቶ ታደሰ ጉርሙ ልጅ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ ተቀብለን አጽንተነዋል ። ኪሣራና ወጭ ይቻቻሉ ፤ ውሣኔው መጽናቱን እንዲያውቀው ግልባጩ ለከፍተኛው ፍ/ ቤት ይተላለፍ ።

ይህ ውሣኔ በጠቅላይ ፍ/ቤት በፓናል ችሎት ዛሬ ሐምሌ 13/ 1975 ዓ ም በድምጽ ብልጫ ተሰጠ ።

የዳኞች ፊርማ ቀኛ/ እንዳለው መንገሻ

አቶ ዓለማየሁ ኃይሌ

» ጌታቸው አፍራሳ

» ሠይፉ ፈይሳ

» ጌታቸው ፍቅረ ማርያም

የሀሣብ ልዩነት ፤

በተራ ቁ. 5ኛው እና 7ኛ የተሰየምነው ዳኞች በድምጽ ብልጫ ከተሰጠው ውሣኔ በመለየት የሚከተለውን የሃሣብ ልዩነት ሰጥተናል ።

የዚህን ክርክር ሁኔታ መርምረን እንደተረዳነው በፍሬ ነገሩም ሆነ በሕግ ረገድ የሚከተለው ሆኖ አግኝተነዋል ።

1. የሥር አቤቱታ አቅራቢዋ ማለት የዛሬ መልስ ሰጭ አቤቱታውን ሲመሠርቱ ከሥር ተጠሪው ከዛሬ ይግባኝ ባይ ጋር ከ1963 ዓ ም ጀምሮ እስከ 1967 ዓ ም ድረስ በኔና በእሱ ቤት ውስጥ እንደባልና ሚስት ሆነን በወዳጅነት አብረን በመኖር ከጋብቻ ውጭ በፈፀምነው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ተማሪ ሰለሞን ታደሰን ወልደናል ። ልጁ ሲወለድ የሆስፒታል ገንዘብ ተጠሪው ከፍሏል ልብስና የልጅ አልጋም ገዝቷል ፣ የዕቁብ ገንዘብ ይጥልልኝ ነበር ፣ ልጅነቱን አምኖ የተቀበለ ስለሆነ ልጅነቱ ሊታወቅልኝ ይገባል በማለት አቤቱታ ሲመሠርቱ የሥር ተጠሪ የዛሬ ይግባኝ ባይ የሰጡት መልስ አቤቱታ አቅራቢዋ በሴትኛ አዳሪነት ተዳዳሪና የመጠጥ ንጋደ ዘወትር ወንድ በማስተናገድ ላይ የምትገኝ እንደመሆኗ መጠን ደረጃና ሁኔታ ግንኙነት ከማድረግ በቀር እንደባልና ሚስት ሆነን አብረን ኖረን አናውቅም ። እኖር የነበረው ከግል መኖሪያ ቤቱ ከቤተሰቦቼ ጋር ብቻዬን ነው ። ልጁን አልወለድሁም የኔ ነው ብዬ አልተቀበልሁም ፣ ወልጃለሁ የኔ ልጅ ነው በማለት ለወዳጅ ዘመድ አልተናገርሁም ፣ በሕመም መቸገሯን በሌላ ሰው ስለተነገረኝ ሰርዳታ ሆስፒታል ማድረሴና የራሷን ገንዘብ በኔ ስም ማስያዝ ብቻ የኔን አባትነት ሊያረጋግጥ አይችልም ከዚህም በቀር ከማንኛውም ወንድ ጋር በየቀኑ ወይም በየጊ

ዜው ግንኙነት በመፍጠር በምታደርገው ግንኙነት የተወለደው ልጅ ያለው ግንኙነት ከእናቱ ጋር ብቻ እንጂ ከሌላው ወንድ ጋር ግንኙነት የለውም በዚህ ምክንያት በማንኛውም ምክንያት ግንኙነት ነበረ ተብሎ መከራከሪያ ልታደርገውም አትችልም በዚህም ሁኔታ በማንኛቸውም ረገድ ሕጋዊ መተሳሰር ሊኖረን አይችልም ። በዚህ ሁሉ ምክንያት አቤቱታው ሊሠረዝ ይገባዋል በማለት ተከራክረዋል ።

ይህን ክርክር መሠረት በማድረግ የከፍተኛው ፍ/ቤት ከግራ ቀኙ የቀረበውን ማስረጃ በመመርመር የሰጠውን ውሣኔም መርምረናል ። በአጠቃላይ የክርክሩን ሁኔታ እንደተገነዘብነው ሁሉ በሥር አቤቱታ አቅራቢ በዛሬ መልስ ሰጭ አማካይነት ስለልጅነት ሁኔታ ለመረጋገጥ የተሰማው ማስረጃ ግንኙነት የነበራቸውና አንዳንድ እርዳታ በወዳጅነት መልክ ይቀባበሉ እንደነበረ እንጂ የልጅነትን ሁኔታ ወይም የአባትነትን ሁኔታ ሊያሳውቅ በሚያስችል ረገድ አጥጋቢ የሆነ ማስረጃ የቀረበ ሆኖ አላገኘነውም ።

ከዚህም በቀር የልጅነት ሁኔታ የሌለው ልጅ አባትነትን ለማሳወቅ ወይም ወይም ለማረጋገጥ አቤቱታ ማቅረብ የሚገባው ፦

ሀ. በጋብቻ ጊዜ የተጸነሰ ወይም የተወለደ መሆኑን ወይም ፣

ለ. ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብረው በአንድነት ተቀምጠው በፈጸሙት የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተጸነሰ ወይም የተወለደ መሆኑን ፣

ሐ. ልጅነቱ በጽሁፍ የታወቀ ወይም መውለዱ ታምኖ አባት ነህ የሚባለው ሰው የተቀበለ ለመሆኑ ሁኔታዎቹን ለማረጋገጥ ብቻ መሆን አለበት ።

በዚህ ክርክር ላይ ግን ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው አቤቱታው ሲመሠረትም ሆነ በተሰማው ማስረጃ ልጅ በተወለደ ጊዜ ወይንም በተጸነሰ ጊዜ ግራ ቀኙ ተከራካሪዎች እንደ ባልና ሚስት ሆነው በሚኖሩበት ጊዜ ወይንም በሥርዓት እንደ ተጋቡ ባልና ሚስት ዓይነት መስለው ይገኙ እንደነበረ የተመሰከረ ነገር የለም ።

ይህን መሠረታዊ የሆነ ነጥብ መልስ ሰጭ ሳያስረዱ አባት ነው ይባል የሚባለው ሰው በወዳጅነት አንዳንድ ርዳታ አድርጓል በመባሉ ብቻ ለልጅነቱ መታወቂያ መሠረታዊ እና በቂ የሆነ ማስረጃ ይሆናል ተብሎ በተሰጠው የድምጽ ብልጫ ውሣኔ አልተስማማንም ። የአካባቢም ማስረጃ በቂ ሊሆን ይችል የነበረውም ከላይ በዝርዝር ከተነገሩት ሕጋዊ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ እንኳን ለመኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ መሆን ስላለበት ነው ።

ከላይ ከተገለጹት ሕጋዊ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ አንኳን ጭብጥ ለመኖሩ ለማስረዳት ካልተቻለ ለሆስፒታል ገንዘብ መክፈል ፣ ልብስ መግዛት ፣ ዕቁብ ገንዘብ መክፈል ለልጅነት መታወቂያ አጥጋቢና በቂ ማስረጃ ሆኖ ሊገኝ አይችልም ።

ከዚህም በቀር የሥር አመልካች የዛሬ መልስ ሰጭ ሴትኛ አዳሪ በመሆን የመጠጥ ንግድ ሥራ የሚያከናውኑና ብዙ ሰው የሚያስተናግዱ ለመሆኑ የታመነና የተረጋገጠ ስለሆነ በእንደዚህ ያለ የኑሮ ሁኔታ ላይ የሚደረገው የግብረ ሥጋ ግንኙነት በሕግ ፊት ምንም ዓይነት ውጤት የሌለውና በማንኛውም ምክንያት መከራከሪያ ሊሆን እንደማይችል በሕግ የተደነገገ በመሆኑ በዚህ ሁኔታ የተወለደ ልጅ ከእናቱ ጋር በቀር ከሌላ ሰው ጋር በማንኛቸውም ሕጋዊ ምክንያት መተሳሰር እንደሌለ ሕግ የሚያዝ ሆኖ በመገኘቱ ነው ።

ስለዚህ በዚህ ሁሉ ምክንያት የልጅነት ይታወቅልኝ ክርክር በሕግና በፍሬ ነገሩ በማስረጃም ጭምር ያልተደገፈ ሆኖ በማግኘታችን በድምጽ ብልጫ ልጅ ነው ተብሎ ከተሰጠው ውሣኔ በሃሣብ በመለየት ስለሞን የይግባኝ ባዩ ልጅ ነው ሊባል አይገባም በማለት በሃሣብ ተለይተናል ።

ፊርማ ሊበን አመደ

አሥመሮም ሥዩም

በፍርድ ጉዳይ ላይ የቀረበ ትችት

ከጋብቻ ውጪ ወይም ከጋብቻ ውጪ ከሚገኝ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኑሮ ውጪ የሚወለድ ልጅን አባትነት ስለማወቅ

መስፍን ገ/ሕይወት

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

1. ከሳሽ አየለች ወ/ገብርኤል ተከሳሽ ጥሩነሽ ተሰማ
2. ከሳሽ ታደሰ ጉርሙ ተከሳሽ ጥሩወርቅ ኢየሱ

(የፍትሐብሔር መዝገብ ይግባኝ ቁጥር 394/72 እና 111/74 በተከታታይ)

ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአየለችን ጉዳይ [1] በተመለከተ በሰጠው ውሳኔ በአንድ የትምህርት ቤት መዝገብ ውስጥ በትምህርት ቤቱ ባለሥልጣን የሠፈረ ጽሑፍ አስመዝጋቢው ሰው ተመዝጋቢው ተማሪ ልጁ ነው ሲል በሰጠው የቃል መግለጫ ላይ የተመረኮዘ ከሆነ በአንቀጽ 748/ [2] በመመሥረት ይኸው ጽሑፍ ዋጋ ያለው የአባትነት ማወቅ ነው ሲል ወስኗል ። በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ በታደሰ ጉርሙ ጉዳይ ላይ በሰጠው ውሳኔ በዚሁ አንቀጽ ትርጉም መሠረት በጉዳዩ ውስጥ የተመለከተውን ልጅ ለማዋለድ የተደረገውን ክፍያ የሚያሳዩ በአንድ የሆስፒታል ገንዘብ ተቀባይ አባት ነው በተባለው ሰው ስም የተሰጠ የክፍያ ደረሰኝ እንደዚሁ ዋጋ ያለው የአባትነት ማወቅ ነው ሲል ወስኗል ። የትችታችን ዓላማ ፍርድ ቤቱ ከላይ እንደ ተጠቀሰው በመወሰኑ በፍሬ ነገር ግምገማም ሆነ በህግ አተረጓጎም ረገድ የፈጸመውን ስህተት ለማሳየት ነው ።

እንደ ፍርድ ቤቱ አባባል በአንቀጽ 748/1/ [3] ውስጥ የተመለከተው በራሱ በጸሐፊውም [4] ሆነ በሌላ ሰው የተዘጋጀ ማናቸውም “ ክብደት ያለውና በጽሑፎቹ የተደረገ አስተማማኝ ማስረጃ ” ነው ። ከዚህ አጠቃላይ መንደርደሪያ በመነሳት ፍርድ ቤቱ የሚከተሉትን የአባትነት ዝምድናን በአባትነት ማወቅ ለመመሥረት በቂ አድርጎ ተቀብሏል ።

1/ አባት ነው በተባለው ሰው በፍርድ ቤት ፊት ተሰጥቶ በፍርድ ቤቱ ጸሐፊ የተመዘገበ የምስክርነት ቃል ፣

2/ አባት ነው በተባለው ሰው መግለጫ ላይ በመመርኮዝ በመንግሥት ባለሥልጣኖች የሠፈረ ማናቸውም ጽሑፍ ወይም ቃለ ጉባኤ ፣

3/ ለማናቸውም መሥሪያ ቤት [5] አባት ነው በተባለው ሰው የተጻፈ ማናቸውም ማመልከቻና ፣

4/ ማናቸውም አባት ነው በተባለው ሰው ለዘመድ ወይም ለጓደኛ የተጻፈ የግል ደብዳቤ ።

ፍርድ ቤቱ በአየለች ጉዳይ የትምህርት ቤቱን ጸሐፊ እንደዚሁም በታደሰ ጉርሙ ጉዳይ የሆስፒታሉን ገንዘብ ተቀባይ እንደገለልተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች በመቁጠር የትምህርት ቤቱን መዝገብና የሆስፒታሉን ደረሰኝ የአባትነት ማወቅ በትክክል የተደረገባቸው የማስረጃ ሰነዶች አድርጎ ወስዷቸዋል ።

አባትነትን ማወቅ በጽሑፍ መሆን እንዳለበት አንቀጽ 748/1/ ውስጥ የተደነገገው ከሚገባው በላይ ላልቶ ተተርጉሟል። እንዲያውም “ ክብደት ያለውና በጽሑፍ የተደረገ አስተማማኝ ማስረጃ ” የሚሉት ቃሎች ከሚጠቀሙት ሀሳብ ይበልጥ ላልቷል ። የዚህን አባባል ትክክለኛ መሆን ወይም አለመሆን ከመመልከታችን በፊት የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የተመሠረተበት ማስረጃ በህጉ መሠረት የታዘዘውን ፎርም (ዓይነት) ይዟል አልያዘም የሚለውን ወደጐን በመተው የዚሁኑ ማስረጃ በቂነት መገምገሙ ተገቢ ይመስለናል ።

የፍርድ ቤቱ የፍሬ ነገር ግምገማ

በአየለች ጉዳይ ይገባኙ የቀረበው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው ማስረጃ አቶ ወ/ገብርኤል ተ/ማርያም በእርግጥ የአየለች አባት መሆናቸውን አያሳይም በማለት ለመልስ ሰጭዋ የፈረደውን ፍርድ በመቃወም ነው።[6] ከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔውን የሰጠው ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል ላይ በመመርኮዝ ነው ። በይግባኝ ክስ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይዋን እንደ ልጅ መታወቅዋን በምስክሮች እንድታረጋግጥ በመፍረዱ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በአንቀጽ 748/2/ መሠረት ሕገ ወጥ ነው በማለት ውሳኔውን ሽሮታል ። ከዚያም ፍርድ ቤቱ አንቀጽ 747/1/ን በመተርጐም ከዚህ በፊት ወደተጠቀሱት ውሳኔዎች ላይ ደርሰዋል ።

እስቲ አሁን ፍርድ ቤቱ የተቀበለውን ማስረጃና አያይዞም ያደረገውን ግምገማ በመጠኑ ጠለቅ ብለን እንመርምር ። የአባትነት ማወቅን ለማረጋገጥ የቀረበው ማስረጃ ለፍርድ ቤቱ ጥያቄ መልስ የሚሆን በቀለመወርቅ ት/ቤት የተጻፈ አየለች ወ/ገብርኤል በትምህርት ቤቱ ውስጥ ከ1974 እስከ 1979 ድረስ ተማሪ እንደነበረችና የተመዘገበችውም በአቶ ወ/ገብርኤል ተ/ማርያም ማለትም በዚያን ጊዜ የትምህርት ቤቱ ሠራተኛ በነበሩና ራሳቸውን የልጅቷ አባት አድርገው ለትምህርቱ ባለሥልጣኖች በገለጹት ሰው ጥያቄ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ነው ። ከደብዳቤው በግልጽ እንደሚታየው አባት ነው በተባለው ሰው “ በጽሑፍ ” የተዘጋጀ ስላልነበረ ደብዳቤው ራሱ እንደ አንድ በጽሑፍ እንደሠፈረ የአባትነት ማወቅ መግለጫ ሊወሰድ ባለመቻሉ ፍርድ ቤቱ ይኸው መግለጫ በእርግጥ በትምህርት ቤቱ መዝገብ ላይ ለመስፈሩ ደብዳቤውን እንደ ማረጋገጫ ወስዶታል ። ሆኖም ፍርድ ቤቱ የትምህርት ቤቱ መዝገብ ስላልቀረበለት[7] የትምህርት ቤቱን ጸሐፊ አቶ ማርቆስ ደልማን እንደምስክር ጠርቷል ። ፍርድ ቤቱ ምስክሩን የጠራበትን ምክንያት እንደሚከተለው ገልጾታል ።

> የትምህርት ቤቱን ባለሥልጣን የጠራንበት ምክንያት በራሱ በአባትነት ማወቅ ጥያቄ ላይ እንዲመሰክሩ ሳይሆን <u>በትምህርት ቤቱ መዝገብ ላይ በእርግጥ ምን እንደሰፈረ ፣ ስለአመዘጋገቡ ሁኔታና ትምህርት ቤቱ በምዝገባ ወቅት የሚከተለውን ሥርዓት እንዲያስረዱን በማለት ነው ።</u> (ለማትኮር የተሠመረው ተጨማሪ ነው ። —

በምስክርነት ቃላቸው አቶ ማርቆስ በትምህርት ቤቱ መዝገብ አየለች ወ/ገብርኤል የሚል ስም የሠፈረ መሆኑን ፣ ምዝገባውም የተካሄደው የልጅቷ አባት

* መ.ጉ.ሕ. የሚለው የዚህ ፍርድ ጉዳይ ትችት አቅራቢን መስፍን ገ/ሕይወትን ይጠቁማል /ከመጽሔቱ አዘጋጅ/

ነኝ ብለው በገለጹት በአቶ ወ/ ገብርኤል ተ/ማርያም ጥያቄ መሆኑ (ምናልባትም ግምት ላይ መድረስ ከተቻለ) በዚህ ጉዳይ ውስጥ ያለችው ይግባኝ ባይ በእርግጥም በመዝገቡ ውስጥ ስሟ ሰፍሮ የምትገኘው ልጅ መሆኗን ገልጸዋል ። በዚህ ደረጃ መመለስ ያለበት ጥያቄ የቀረበው ማስረጃ በእርግጥ አቶ ወ/ገብርኤል የአየለች አባት መሆናቸውን በጽሑፍ መግለጻቸውን በበቂ ሁናቴ ማረጋገጥ መቻል አለመቻሉ ነው ።

ከፍርድ ቤቱ ውሳኔና የትምህርት ቤቱ ጸሐፊ ከሰጡት የምስክርነት ቃል የሚከተሉትን መገመት እንችላለን ።

1/ በመዝገቡ ውስጥ ሠፍሮ የሚገኘው ትክክለኛው መረጃ አየለች ወ/ገብርኤል መሆኗን ፡

2/ ምዝገባው የተካሄደው የአቶ ወ/ገብርኤል ልጅ ናት ያሏትን አንዲት ልጅን አየለች ወ/ገብርኤል በሚል ስም እንዲመዘግብላቸው ለትምህርት ቤቱ ባለሥልጣን ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት በዚሁ ባለሥልጣን መመዝገቧን [8] እና ፤

3/ አመዘጋገቡም የተመረኮዘው በተለምዶ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ናቸው የተባሉት ሰዎች በመዝጋቢው ባለሥልጣን ፊት በሚሰጡት የቃል መግለጫ ላይ መሆኑን ነው ።

ከላይ ግልጽ ሆኖ እንደሚታየው ስለመዝገቡ መኖርና ስለይዘቱም ጭምር የፍርድ ቤቱ " እውቀት " የመነጨው ፍርድ ቤቱ የውሳኔዬ አንድያ መሠረት ነው ከሚለው " ከጽሑፉ " ብቻ ሳይሆን ትምህርት ቤቱ ከጻፈው ደብዳቤና የትምህርት ቤቱ ባለሥልጣን ከሰጡት የምስክርነት ቃልም ጭምር ነው ። ከዛው ከ "ጽሑፉ " አየለች ወ/ገብርኤል የሚለው ስም በእርግጥ የይግባኝ ባይዋ እንጂ የሌላ የሞክሼ ኢለመሆኑን እንዲሁም አባት ነው የተባለው ሰው የአየለች አባት ነኝ ብሎ መግለጹንና ምዝገባውም የተካሄደው ይህንኑ ገለጻ አስመርኩዞ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አያውቅም ። በሌላ አነጋገር ማናቸውም አየለችንና አባት ነው የተባለውን ሰው የሚያገናኝ ነገር የፈለቀው ከምስክር የምስክርነት ቃል ከመሆኑም ሌላ በጽሑፍ የሠፈረው " የአባትነት ማወቅ " "ጽሑፍ " እንኳ የተረጋገጠው ጽሑፉን ፍርድ ቤት በማቅረብ ሳይሆን በአንድ መኖሩን በሚገልጽ ደብዳቤ ሲሆን ይዘቱም " የተረጋገጠው " ይኸው ምስክር በሰጠው የምስክርነት ቃል ነው ። በዚህ ሁናቴ እንግዲህ በግልጽ እንደሚታየው ፍርድ ቤቱ የመዝገቡን መኖር በእርግጥ ስለማያውቅና ይኸው መዝገብ ቢኖርም አየለች ወ/ገብርኤል የተባለውን በብዛት የሚገኝ ስምን ከመጠቀም በቀር ምንም ስለማያረጋግጥ ፍርድ ቤቱ ውሳኔዬ የተመረኮዘው በመዝገቡ ላይ ነው ሲል የሰጠውን ቃል እንዳለ መውሰድ አይቻልም ። በተመሳሳይ ሁኔታ ማናቸውም ልጅንና አባት ነው የተባለውን ሰው የሚያያይዘው ነገር በአንድ ምስክር የምስክርነት ቃል ላይ ተመርኩዞ እያለ " የትምህርት ቤቱን ባለሥልጣን የጠራነው በራሱ በአባትነት ማወቁ ጥያቄ ላይ እንዲመሰክሩ ሳይሆን . . ." የሚለውን የፍርድ ቤቱን አባባል ክብደት ሰጥቶ መውሰድ አይቻልም ።

እስቲ አሁን አጠር ባለ መልኩ የታደሰ ጉርሙ ጉዳይን አስመልክቶ የቀረበውን ማስረጃ እንመልከት ። ከጋንዲ ሆስፒታል ከመጣው መዝገብ ውስጥ የሚገኘው መረጃ እንዲህ ይላል ። " የበሽተኛው ስም ጥሩወርቅ እያሱ ፤ ከፋይ ታደሰ ጉርሙ ፤ ስልክ ቁጥር 152025 ። " 15/5/62 እ. ኤ. አ. የሚለው ቀንና የገንዘብ ተቀባዩ ፊርማ ጭምር በደረሰኙ ላይ ይገኛሉ ። ይህንኑ መረጃ ከሚከተሉት ጋራ አቀና

ጅቶ መመልከት ተገቢ ነው ። የይግባኝ ባዩ ልጅ ነው የተባለው ልጅ ስም ማለትም ሰለሞን በደረሰኙ ላይ አይገኝም ። ሌላው ቀርቶ በሽተኛዋ ሆስፒታል የገባችው ለወሊድ ጉዳይ መሆኑ እንኳ አልተገለጸም ። [9] ጉዳዩ ወሊድን አስመልክቶ ቢሆን እንኳ ደረሰኙ የተወሰደው ልጅ ሰለሞን መሆኑንና እናት የተባለችውም በዚህ ጉዳይ ውስጥ መልስ ሰጭ የሆነችው ጥሩወርቅ እያሱ መሆኗን አይናገርም ። በሌላ አነጋገር ይህ ሁሉ የውሳኔው መሠረት ነው ከተባለው " ጽሑፍ " አይመነጭም ። ይህን ሁሉ ፍርድ ቤቱ አገኘ ቢባልም ያገኘው ቀድሞውኑ መስማት ነበረባቸው ካላቸው የምስክሮች ቃል ነው ። ጽሑፉን ሲመለከቱት ሕጻኑን ሰለሞንን አባት ነህ ከተባለው ከታደሰ ጉርሙ ጋራ የሚያያይዝ አንዳችም ነገር የለም ። ስለዚህ የፍርድ ቤቱን የሕግ አተረጓጎም ተቀብለን ማናቸውም " ጽሑፍ " ተቀባይነት አለው ብንል እንኳ ደረሰኙም ሆነ መዝገቡ ያረጋግጣሉ የተባለውን ነገር ስለማያረጋግጡ በቂነት የላቸውም ።

በታደሰ ጉርሙ ጉዳይ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የተመረኮዘው የአየለችን ጉዳይ አስመልክቶ በተሰጠው የሕግ አተረጓጎም ላይ ሲሆን ወደፊትም የሚነሱ ጉዳዮች በዚሁ ላይ የተመረኮዙ ይሆናሉ ተብሎ የማይታመንበት ምክንያት የለም ። ስለዚህ ፍርድ ቤቱ በህግ ጥያቄ ረገድ በወሰደው አቋም መወያየትና መገምገም አስፈላጊ ነው ።

የፍርድ ቤቱ የህግ አተረጓጎም ።

ፍርድ ቤቱ የጽሑፍ ማስረጃን አስመልክቶ በአንቀጽ 748 / 1 / ትርጉም መሠረት የወሰደውን የሕግ አቋም ስንተነትን " የተጻፈ ማስረጃ " ወይም በጽሑፍ የቀረበ ማስረጃ የሚሉት ቃላት በህግ ፍልስፍና የተሰጣቸውን ትርጉም መወያየቱ ተገቢ ይመስለናል ።

በጽሑፍ የተዩረጉ የሰዎች መግለጫዎች ሁለት ዓይነት ፎርም ሊኖራቸው ይችላል ። እነዚህም የግልና የግል ያልሆኑ ወይም በባለሥልጣን የተረጋገጡ ሰነዶች ናቸው ። የፊተኞቹ የሚመለከቱት በሚመለከታቸው ወገኖች ስም በነዚሁ ወገኖች የሚዘጋጁትን ሲሆን የኋለኞቹ ደግሞ የመንግሥት ሠራተኞች መንግሥታዊ ተግባራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚያዘጋጅዋቸውን ነው ። [10] በባለሥልጣን የተረጋገጡ ሰነዶች ማለት " የግል ያልሆኑ ሰነዶችን በህጉ መሠረት በተጠናቀቁበት ቦታ ከነአስፈላጊው ሥነ ሥርዓት ለማዘጋጀት ሥልጣን ያለው የመንግሥት ባለሥልጣን የተቀበላቸው ናቸው ።" [11] ስለዚህ የተረጋገጡ ሰነዶች ባጠቃላይ ማናቸውም ባለሥልጣን የተቀበላቸው መግለጫዎች ሳይሆኑ በህግ በተለይ የተወሰኑት የተቀበሉዋቸው ናቸው ። በክብር መዝገብ የሠፈሩ ጽሑፎች ለምሳሌ የሚዘጋጁት በክብር መዝገብ ሹማምንት ፤ በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ ውሎችንና ሰነዶችን በሚያጸድቅ መንግሥት ባወቀው አዋዋይ ብቻ ነው ። [12]

በአጠቃላይ ሲታይ [13] የግል ሰነዶች በሚዘጋጁበት ወቅት በጸሐፊው ላይ ከሚጣል የፊርማ ግዴታ ውጪ ምንም ዓይነት ሌላ ሥነ ሥርዓት የለም ። [14] ።

በባለሥልጣን በተረጋገጡ ሰነዶች ላይ በግል ፊርማ ከተጻፉ ሰነዶች የበለጠ እምነት ስለሚጣል የሁለቱ የአስረጂነት ኃይል ይለያያል ። [15] በባለሥልጣን በተረጋገጡ ሰነዶች ላይ ባብዛኛው እምነት የሚጣለው ሰነዶችን ለማዘጋጀት ሥልጣን የተሰጣቸው ባለሥልጣኖች የሚያዘጋጅዋቸውን ሰነዶች ይዘት ትክክለኛነት በተመለከተ ተጠያቂ ስለሚሆኑ ነው ። [16]

የግልም ሆኑ በባለሥልጣን የተረጋገጡ ሰነዶች፣ "በቅድሚያ የተዘጋጁ ማስረጃዎች" የተባሉ ብቸኛ የጽሑፍ ማስረጃ ዓይነቶች ናቸው ። ነገር ግን ይህ ማለት በተለይ ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች የግል ደብዳቤዎች፣ ይፋ ያልሆኑ ወረቀቶች፣ ወዘተ እንደ ማስረጃ ሊቀርቡ አይችሉም ማለት አይደለም ። እንደዚህ ያሉ ማስረጃዎች የአስረጂነት ኃይላቸው ለዳኛው ህሊና የተተወ ሲሆን ብዙውን ጊዜም የሚያገለግሉት ማስረጃ ለማቅረብ በመንደርደሪያነት ብቻ ነው ። እንደዚህ ያሉት ጽሑፎች ከላይ የተጠቀሱት ሰነዶች ከሚገኙበት ምድብ ውስጥ ስላይደሉ" ህጉ የጽሑፍ ማስረጃን በሚጠይቅበት ቦታ ዋጋ እንደሌላቸው ይቆጠራሉ ። [17]

እንደገና ለመግለጽ ያህል ህጉ የጽሑፍ ማስረጃ ሲጠይቅ በቅድሚያ የተዘጋጀ ማስረጃን ማለትም ወደፊት አለመግባባት ሲፈጠር ለማስረጃነት እንዲያገለግል ሆን ተብሎ የተዘጋጀን ጽሑፍ ማለቱ ነው ። የጽሑፉ ማስረጃ በባለሥልጣን በተረጋገጠ ሰነድ ፎርም እንዲሆን ከተጠየቀ ይኸው ጽሑፍ በሌላ በማንም የአስተዳደር ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን ሳይሆን እነዚሁኑ መግለጫዎች እንዲቀበሉ በተለየ በተሰየሙ የመንግሥት ባለሥልጣኖች መዘጋጀት አለበት ። የግል ሰነዶች በተጠየቁ ጊዜ ምንም እንኳ በሌላ በሶስተኛ ሰው ቢዘጋጁም በጽሑፉ ባለቤት መፈረም አለበት ።[18] ስለዚህ ከነዚህ ከሁለት ፎርሞች በአንደኛውም ያልተዘጋጀ ጽሑፍ ዋጋ ያለው የጽሑፍ ማስረጃ ባለመሆኑ በህጉ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም ። ከዚህም ተነስተን መደምደም የምንችለው ፍርድ ቤቱ ባጠቃላይ ማናቸውም የመንግሥት ባለሥልጣኖች መግለጫዎችን ወይም አባት ነው የተባለው ሰው ለማናቸውም መሥሪያ ቤት ያቀረበውን ማመልከቻ አስመርኩዞ የወሰዷቸውን ጽሑፎችና ቃለ ጉባኤዎች እንዲሁም የግል ደብዳቤዎችንና ሌሎች በዛው ሰው የተጻፉ ጽሑፎችን ዋጋ እንዳላቸው የአባትነት ማወቅ ማረጋገጫዎች ሲቀበል ስህተት መፈጸሙን ነው ።

ከመለፋቱ የተነሳ የሆስፒታል ደረሰኙን እንኳ ለመቀበል የበቃበት የፍርድ ቤቱ አተረጓጎም የተመሠረተው እንደሚከተለው በሚነበበው አንቀጽ 747/2/ ላይ ነው ። "ይህም የሚሰጠው ቃል አባትነት ማወቅ የሚያስከትለው ውጤት እንዲኖረው ሲል የተናገረ መሆኑ አስፈላጊ አይደለም ። " ፍርድ ቤቱ የአየለች ጉዳይ አስመርኩዞ በዚህ አንቀጽ ትርጉም ነው ብሎ የወሰደው በሚከተሉት ቃላት ይገልጻል ።

> " አንድ መግለጫ የግድ አባትነትን ማወቅ የሚያስከትላቸውን ውጤቶች ለማምጣት የተደረገ መሆን የለበትም ተብሎ ከተደነገገ አባትነትን ለማወቅ ሳይሆን ለሌላ ምክንያት የተዘጋጀ ጽሕፈት በምስክሮች መረጋገጥ የለበትም ። የግል ደብዳቤ እዚህ ላይ በግልጽ ምሳሌነት ሊያገለግለን ይችላል ። "

" ይኸው ጽሕፈት . . . አባትነትን ለማወቅ ሳይሆን ለሌላ ምክንያት ተብሎ ሊዘጋጅ ይችላል ። " ከሚለው ተገቢ መደምደሚያ ፍርድ ቤቱ አንድ ጽሕፈት ዋጋ እንዳለው የአባትነት ማወቅ ለመቆጠሩ " የግል ደብዳቤ . . . በግልጽ ምሳሌነት ሊያገለግለን ይችላል " ወደሚለው መደምደሚያ ይዘላል ። ፍርድ ቤቱ እንደዚህ በመደምደሙ በህግ የተጠየቀውን የማስረጃ ፎርም አንድ ሰው በታዘዘው ፎርም መሠረት ጽሕፈቱን ሲያዘጋጅ ማሟላት ካለበት ሥነ ሥርዓት (ፎርማሊቲ) ጋር አምታትቶታል ። በሌላ አነጋገር ፍርድ ቤቱ የሥነ ሥርዓት ጽንስ ሃሳብ ከፎርም

ጽንስ ሃሳብ አልለየውም ። ፍርድ ቤቱም የሚከተሉትን የህግ አርቃቂውን ቃላት የአየለችን ጉዳይ አስመርኩዞ መጠቀሙም ለዚሁ ማረጋገጫ ነው ።

> ምንም እንኳ አባትነትን ማወቁ በአንድ በተወሰነ ሥነ ሥርዓት (ፎርማሊቲ) መደረግ ቢኖርበትም የአባትነት አቀባበል ለማናቸውም ልዩ ፎርም ተገዥ አይደለም ። (ለማትኮር የተሠመረው ተጨማሪ ነው ። መ. ገ. ሕ.)[19]

በእግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 103 የዚሁ የሬኔ ዳቪድን ጽሑፍ ተርጓሚ እንዲህ ይላል ።

> በእዚህ አንቀጽ ውስጥ በቀደምትነት የቀረበው ረቂቅ የአባትነት መግለጫ በአራት ምስክሮች ፊት እንዲሰጥ ይጠይቅ ነበር ። በኮሚሽኑ የተሻሻሉት አንቀጽ 747 እና ይህንን ጥያቄ አይዙም ።[20]

" አባትነትን መቀበል " የሚያመለክተው በአንቀጽ 751 እንደተደነገገው በእናትየዋ ወይም እሷ ካልቻለች በሷ ምትክ ወደላይ በሚቆጠሩ ዘመዶች የሚደረገውን የአባትነት መቀበል ነው ። የአባትነቱ መቀበል የግድ ልዩ ፎርም እንዲኖረው ካለማስፈለጉ ሌላ እንዳውም በዝምታ ማለትም " ይህንኑ የአባትነት ማወቅ ካወቀበት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተቃውሞውን ባለማንሳት "[21] ሊሆንም ይችላል ። ይሄም አንቀጽ 748 1/ " አንድ የአባትነት ማወቅ በጽሑፍ ካልቀረበ ዋጋ አይኖረውም " ብሎ አጥብቆ ከሚያዘውና ከሚጠይቀው የተለየ ነው ። (ለማትኮር የተሰመረ) የተጨመረውም ዓይነት ፎርም ሊደረግና በማናቸውም ዓይነት ዘዴ ለምሳሌ በግል ደብዳቤ ሊረጋገጥ ይችላል ።[22] ፍርድ ቤቱ ማናቸውም ዓይነት ፎርም ያለው የጽሑፍም ሆነ የቃል ማስረጃ ከመቀበል አይከለከልም ።

ዳቪድ የአባትነት ማወቅን አስመልክተው በሚጠቅሱበት ጊዜ የሚጠቀሙት ፎርሙን ሳይሆን (በእርግጥም ፎርሙ በጽሑፍ መሆን ስላለበት) የተርጓሚው ማብራሪያ እንደሚያመለክተው በህግ አርቂቂው ኮሚሽን በኋላ የተዘለለውን በአራት ምስክሮች ፊት የማረጋገጥ ጥያቄን የሚጠቁመውን " አንድ ዓይነት ሥነ ሥርዓት (ፎርማሊቲ) " ነው ። የተጠየቀው ፎርም የጽሑፍ ማስረጃ ለምሳሌ የግል ሰነድ ከሆነ በምስክሮች የማረጋገጡ ሥነ ሥርዓት ሥር ሊወድቅም ላይወድቅም ይችላል ። ለምሳሌ ውሎች በጽሑፍ እንዲደረጉ በታዘዘበት ቦታ የግድ በምስክሮች መረጋገጥ የለባቸውም ። ይኸው አባባል ኑዛዜን በተመለከተም ትክክል ሲሆን አባትነት ማወቅን በተመለከተ ግን ቀድም እንደተገለጸው ትዕዛዙ በኮሚሽኑ ተቀባይነት ስላጣ ትክክለኛ አይሆንም ። ስለዚህ ፍርድ ቤቱ የፎርሙን ጥያቄ ሥነ ሥርዓት (ፎርማሊቲ) አስመልክቶ ከተደነገገው ጋራ በማምታታቱ ከህጉ መንፈስና ድንጋጌ እንዲሁም ከህሊና ግምት ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ አባትነት ማወቅን በእናት አባትነትን ከመቀበል ጋራ በአንድ ደረጃ አስቀምጧቸዋል ።

እርግጥ አንድ ዋጋ ተሰጥቶት ሊነሳ የሚችል ክርክር ቢኖር አንቀጽ 748 2/ የአባትነት ማወቅ በክብር መዝገብ ሹማምንት ወይም እነሱ ከሌሉ ውሎችንና ሰነዶችን በሚያጸድቅ መንግሥት ባወቀው አዋዋይ ፊት መደረግ እንዳለበት የሚጠቀመውን ግምት ውስጥ በማስገባት በባለሥልጣን የተረጋገጡ ሰነዶች ብቻ እንደ አባትነት ማወቅ እንዲቆጠሩ የሚለው አቋም ነው ።

ከዚህ በላይ ያለውን አባባል ከፈረንሳይ የአባትነት ማወቅ ህግ ጋራ በማመሳከርም ጭምር መመልከት ይቻላል ። በፈንንሳይ ሕግ አባትነትን ማወቁ በባለሥ

ልጣን በተረጋገጠ ሰነድ ፎርም እንዲሆን ሲጠየቅ በግል ጽሑፍ የሰፈረ መግለጫ ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም [24] በፕላኒዎል ቃልም እንደተገለጸው [25]

> ሕጉ ምንም ዓይነት ምስጢር አዘል የሆነ ፎርማሊቲ አያዝም ። የአባትነት ማወቁ የሠፈረበት በመንግሥት የታወቀው ሰነድ አጽዳቂው ሰው ጽሑፍ እንኳ ቢሆን ይሄንኑ ማወቅ በተለይ ለመቀበል ተብሎ የረቀቀ መሆን የለበትም ። በአባትነት ማወቁ ባጋጣሚ እንዳውም በውስጠ ታዋቂነት ጭምር በሰነዱ ውስጥ ሊገኝ ይችላል ። . . . ስለዚህ የአባትነት ማወቁ ጽሑፍ የተጻፈበት ዋና ዓላማ አካል ሳይሆን በሰነዱ ውስጥ ከሠፈሩ የሀሳብ መግለጫዎች ብቻ ሊመነጭ ይችላል ።

ከላይ ከተጠቀሰው በግልጽ እንደሚታየው ምንም እንኳን የፈረንሳይ ሕግ የአባትነት ማወቅ በባለሥልጣን በተረጋገጠ ጽሑፍ እንዲደረግ ቢጠይቅም በአንቀጽ 747 (2) ውስጥ የተደነገገውና በፈረንሳይ ሕግ የተደነገገው አንድ ዓይነት ነው ። ስለዚህ የአባትነት ማወቁ ውሎችንና ሰነዶችን የሚያጸድቅ መንግሥት ባወቀው አዋዋይ የሚዘጋጅ ሰነድን ፎርም ከያዘ ኑዛዜ ወይም ምንም እንኳ የሰነዱ ዓላማ " የአባትነት ማወቅ የሚያስከትላቸው ውጤቶች ከመፍጠር ውጪ " ቢሆንም ከማናቸውም ዓይነት በባለ ሥልጣን የተረጋገጠ ሰነድ ሊፈልቅ ይችላል። እንግዲህ አንቀጽ 747 /2/ መተርጐም ያለበት ባጠቃላይ ማናቸውንም ዓይነት አባት ነው በተባለው ሰው በጽሑፍ የሠፈሩ መግለጫዎችን እንደሚፈቅድ ሳይሆን ሰነዱ የተዘጋጀው በቅድሚያ በተዘጋጀ ማስረጃ ፎርም ማለት በባለሥልጣን በተረጋገጠ ሰነድ ወይም ተጽፎ በተፈረመ ሰነድ ፎርም ከሆነ መግለጫው እንዴት እንደተደረገ አንዳችም ሥነ ሥርዓት እንደማይጠይቅ ነው ።

<u>መደምደሚያ ፤</u>

ፍርድ ቤቱ ከጋብቻ ውጪ የተወለዱ ልጆች ያለአባት መቅረት የለባቸውም ከሚለው ትልቅ ዋጋ ከሚሰጠው ሃሳብ ተነስቶ የትምህርት ቤት መዛግብት ፣ የሆስፒታል ደረሰኞችና የግል ደብዳቤዎች ዋጋ እንዳለቸው የአባትነት እውቅናዎች በመቁጠሩ ከሚገባው አልፎአል ። እንደዚህ ያለውን አቋም መውሰድ የአንቀጽ 748/2ን ዓላማ ማለትም እንደማያስተማምን በይፋ በታወቀው የሰው ማስታወስ ላይ ከተመሠረተው የምርስክሮች የምስክነት ቃል ይበልጥ አስተማማኝ የሆነ የማያጠራጥር ማስረጃን በቅድሚያ ማዘጋጀትን ተጻሯል ። እዚህ ላይ በእርግጥ አንድ ሰው በመሐላ የተሰጠው የምስክሮች ቃላትን በታደሰ ጉርሙ ጉዳይ ዋጋ አለው ተብሎ እንዲቀርብ ከተፈቀደው ደረሰኝ ያነሰ አስተማማኝነት አላቸው ማለት ያስደፍራልን ? አይመስለኝም ። ፍርድ ቤቱ የግል ወይም የግል ባልሆኑ ሰነዶች መልክ " በቅድሚያ የተዘጋጁ ማስረጃዎች " ብቻ በመፍቀድ ራሱን መወሰን ነበረበት ።

የፍርድ ቤቱን የህግ አተረጓጐም ትክክለኛ ነው ብንል እንኳ ፍርድ ቤቱ የራሱን የህግ አተረጓጐም ሳያዛንፍ ተከትሎ በነዚህ በሁለት ጉዳዮች ጽሑፍን (ጽሑፍ ስንል በተለምዶው አነጋገር ያለውን ትርጉም ነው) ብቻ እንደማስረጃ አለመቀበሉና በእርግጥም ይበልጥ የተማመነው በምስክሮች የምስክርነት ቃል ላይ መሆኑ ግልጽ ነው ። ፍርድ ቤቱ በእርግጥ በተጨባጭ በማናቸውም ፎርም የቀረበን ማስረጃ ሲቀበል ራሱን በጽሑፍ በቀረበ ማስረጃ አልወሰነም ። ፍርድ ቤቱ የወሰደው አቋም ከህጉ ድንጋጌም ሆነ መንፈስ ከረር ባለ ሁናቴ የተለየ ሲሆን ይኸው አቋም በፍርድ ቤቱ የተገለጸው ጥንቃቄ የሞላበት ሀሳብ ሳያግደው ሕጉ ከመውጣቱ በፊት ወደነበሩበት ሁናቴዎች በተግባር መመለስ ማለት ይመስላል ።

የግርጌ ማስታወሻዎች ።

ሌክቸረር ፣ የሕግ ፋኩልቲ ፣አ. አ. ዩ. ኤል ቢ ፣ የሕግ ፋኩልቲ አ. አ. ዩ.

1. ለግምግማ የቀረቡት ሁለቱ ጉዳዮች ከአሁን በኋላ "የአየለች ጉዳይ" እና "የታደሰ ጉርሙ ጉዳይ" በመባል ይታወቃሉ ።
2. በዚህ ጉዳይ ውስጥ አንቀጾች ሁሉ የተጠቀሱት ከ1952 የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ ነው ።
3. አንቀጽ 748/1 እንደሚከተለው ይነበባል "የአባትነት ማወቁ በጽሑፍ ካልሠፈረ በቀር ውጤት አይኖረውም ።"
4. "ጸሐፊ" የሚለው የሰነዱን አዘጋጅ ይጠቁማል ።
5. መሥሪያ ቤት የሚለው ቃል የግል መሥሪያ ቤቶችንና ሕዝባዊ ድርጅቶችን ይጨምር ወይም በመንግሥት መሥሪያ ቤት ይወሰን ግልጽ አይደለም ።
6. ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ ንባብ እንደሚታየው በኢትዮጵያ እንደተለመደው ክርክሩ የተነሳው ይግባኝ ባይዋ በእናትዋና በአሳዳጊዋ በኩል በአንቀጽ 996 ትርጉም መሠረት እንደ አቶ ወ/ገብርኤል ወራሽ "የወራሽነት የምስክር የምስክር ወረቀት" እንዲሰጣት በጠየቀች ጊዜ ነበር ።
7. ፍርድ ቤቱ ዙሪያ ጥምጥም በመሄድ የፈለገውን ነጥብ ከማረጋገጥ ይልቅ ለምን መዝገቡን እራሱ ለምርመራ እንዳላቀረበ ግልጽ አይደለም ።
8. አቶ ማርቆስ በአቶ/ ወ/ገብርኤል ተገለጸ የተባለውን መግለጫ የተቀበለው ሰው ይሁን አይሁን ከጉዳዩ ግልጽ አይደለም ።
9. ጋንዲ ሆስፒታል የማዋለድ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የማኅፀን በሽታዎችን ባጠቃላይ ስለሚመለከት ደረሰኙ ከሆስፒታሉ መምጣቱ ምንም አይጠቅምም ።
10. ፕላኒዎል ፣ ትሬት ኤሌሜንቴር ድሯ ሲቪል ፣ /ፓርት/ ፣ 1939/ ገጽ 235—6
11. ፕላኒዎል ፣ እላይ የተገለጸው ፤ ቮል 2 ፤ ፓርት 1 ፤ ገጽ 53 በዛው ገጽ ላይ ፕላኒዎል የሚከተለውን በተጨማሪ ይገልጻሉ ፤ "በባለሥልጣን ከተረጋገጡ ሰነዶች ጋራ ተዋህደው ይታያሉ ።" እንደገና እንዲህ ይላሉ "የአስተዳደር ወኪሎች ብዙ በባለሥልጣን የተረጋገጡ ሰነዶች ያዘጋጃሉ ። ነገር ግን ፣ ማረጋገጫ የሚሰጡት በሥልጣናቸው ወሰን ሥር ለረቀቁት ብቻ ነው ።" ፕላኒዎል ፣ በማስታወሻ ቁጥር 10 እላይ የተጠቀሱት ፣ ገጽ 806 ፤
12. ከአንቀጽ 48 እና 146 ጋር አስተያዩ ። የፈረንሳይ ሕግ በአባትና እናት ማወቅ ጊዜ በማሃላ በፍርድ ቤት ፊት ተሰጥቶ በፍርድ ቤቱ ጸሐፊ ለተመዘገበ የምስክርነት ቃል በባለሥልጣን የተረጋገጠን ጽሑፍ ደረጃ ይሰጠዋል ። ፕላኒዎል ፣ ቮል 1 ፣ ፓርት 1 ፣ በማስታወሻ ቁጥር እላይ የተጠቀሱት ፣ ገጽ 806—7
13. በአንቀጽ 831 እና 1727 ከተጠቀሱት በምስክሮች መረጋገጥ ካለባቸው የግል ሰነዶች ጋር አስተያይ ።
14. "ፊርማው ለጽሑፉ የማስረጃ ኃይልነት ይሰጠዋል ። ፊርማ ያልሰፈረበት ጽሑፍ እንደ ጽሑፍ ማስረጃነት ከፍትሐብሔር ጉዳዮች እንኳ በመንደርደሪያነት ዋጋ አይኖረውም ።" ፕላኒዎል ፤ በማስታወሻ ቁጥር 11 እላይ የተገለጹት ፤ ገጽ ፣ 531 ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሳይሆን ሰነዱ የባዕድ ጽሑፉን ባዘጋጀው በራሱ በጸሐፊው መዘጋጀት የለበትም የሚለው ነጥብ በጥልቀት መርምሯታል ።" እነሱ (ማለትም የግል ጽሑፍ ጸሐፊዎች መ. ገ. ሕ.) በሌላ በሶስተኛ ሰው የተዘጋጀውን ጽሑፍ በመፈረም ብቻ ሊወስኑ ይችላሉ ።" ከዚያው ፤ ገጽ 43 ። በተጨማሪም አንቀጽ 88/1/ ፣ 1728 እና 1728 እና 1720 ን ኑዛዜን ውሎችንና ፎርምን ተመልክቶ በተከታታይ የተደነገገውን ተመልከት ።
15. "በግል ፊርማ የተጻፉ ሰነዶች" የሚባሉት በአብዛኛው "የግል ሰነድ" ከሚለው ጋራ ተመሳሳይ ትርጉም ስለሚሰጣቸው የጸሐፊው ፊርማ ሊቀር የማይችል መሆኑን ያሳያሉ ።
16. አንቀጽ 143 ተመልከት ።
17. ፕላኒዎል ፤ ቮል 2 ፤ ፓርት 1 ፣ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሱት ፤ ገጽ 556—566 ።
18. ፊርማው በጽሑፍ ይሁን ወይም በአውራ ጣት ምልክት ወይም በሌላ ማናቸውም መልክ የተደረገ ቢሆንም ፊርማው በአስተማማኝ ሁኔታ ማረጋገጥ ከተቻለ የፊርማው ጠባይ ግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም ።
19. ዲቪድ ፤ አር ፤ "ዘ. ፋሚሊ ሎው ኢን ኢትዮጵያን ሲቢል ኮድ" በአይኖግን ኬ ፤ ያልታተመ ገጽ 97 ።
20. ዴቪድ ፤ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 19 የተጠቀሱት ገጽ 27 ።
21. አንቀጽ 753 ።

22. ከጋብቻ ውጪ የተወለደን ልጅ እናትነት ብቻ መመሥረት በሚቻልበት በፈረንሳይ አገር እንኳ መወለድ ብቻ በቂ እንደሆነበት እንደ ኢትዮጵያ ሳይሆን በአባትነት ማወቁ በቅድሚያ በይፋ ከተደረገ በእናትየዋ የተደረገው የአባትነት መቀበሉ በግል ደብዳቤ ሊሆን ይችላል ።

23. የፍትሐብሔር 1ኛ መጽሐፍ ቻፕተር 3 ተመልከት ።

24. ፕላኒዎል ፤ ቮል 1 ፓርት 1 ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 1 የተገለጹት ፤ ገጽ 808 ።

25. ከዛው ፤ ገጽ 807—808 ።

የጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር የመጨረሻ ውሳኔዎችን መስማት ፣ ከተከራካሪ ወገኖች ለአንደኛው የተሰጠ ሌላ የይግባኝ መብት ?

የሴፍ ገ/እግዚአብሔር *

የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ጠቅላይ ፍ/ቤት ካሉት የግዛት ሥልጣናት መካከል አንዱ ፡

በጠቅላይ ፍ/ቤት ወይም በሌሎች ፍ/ቤቶች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ሲገኝ ወይም በሥነ ሥርዓት ሕጎች ውስጥ በተመለከቱት ሌሎች ምክንያቶች በሰበር መስማት ይገኝበታል ።[1]

ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንን ተግባር ያከናውን ዘንድ ሕጉ የሚከተለውን ይደነግጋል ።

በጠቅላይ ፍ/ቤት ወይም በሌላ በማናቸውም ፍ/ቤት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር የሚሰማው በጠቅላይ ፍ/ቤት ፡ በፕሬዚዳንቱ ወይም በምክትል ፕሬዚዳንቶቹ በአንዱ ሰብሳቢነት [2] በተጨማሪ ቢያንስ አራት የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎት [3] ይሆናል ።

ጉዳዮች በሰበር ይሰሙ ዘንድ የማንቀሳቀስን ሥልጣንና ኃላፊነትን በተመለከተም የሚከተለውን ተመልክተናል ።

> በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 4 መሠረት የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር የሚሰማው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሲፈቅድ ወይም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ተቃውሞ ሲያቀርብ ነው ። [4]
>
> እነዚህን ድንጋጌዎችም ሲመረመሩ የሚከተለውን ጭብጥ ያስነሳል ። በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ወይም በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ምርመራ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ስለመሆኑ የተገኘ የመጨረሻ ውሳኔ እኳያ የባለጉዳዮቹ ሚና ምንድን ነው ?

በልዩ ሁኔታ ሲቀመጥ ፣ ይህ አጠቃላይ ጭብጥ ወደሚከተሉት ጭብጦች ሊከፈል ይቻላል ።

/1/ ይህ ሰሚ እንደማንኛውም ተራ ይግባኝ ጠቅላይ ፍ/ቤት ባለጉዳዮችን እንደ ይግባኝ ባይና መልስ ሰጭን የሚጠራበት ሌላ ይግባኝ ነውን ?

/2/ ከሆነስ ፡ ሰሚው እንደማንኛውም ሌላ ይግባኝ በባለጉዳዮቹ ፍላጎት ላይ ይመሠረት ይሆን ?

ከላይ በ/1/ና በ/2/ ላይ ለተጠቀሱት ጭብጦች የምንሰጠው መልስ አፍራሽ ከሆነ ፡

/ሀ/ በሰበር ሰሚው የተሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ በተመለከተ ባለ ጉዳዮቹ ምንም የሚጫወቱቱ ሚና የለም ማለት ይሆን ?

/ለ/ ከሆነስ በሰበር ሰሚው በሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ በባለጉዳይነት የሚወርሱት እነማን ይሆናሉ ?

የሰበር ሰሚው በመጨረሻ ውሳኔዎች ላይ የሚያደርገው ምርመራ በወንጀልነክ ጉዳዮች ብቻ ያልተወሰነ መሆኑን ስንመለከት የባለጉዳዎችን ሚና በተመለ

ከት ያነሰ ነው ። ጭብጥ ከምንጊዜም የበለጠ ተገቢ ሆኖ እናገኘዋለን ። የፍትሐብሔር ጉዳዮችን በተመለከተም ጭምር የሚቻል ሆኖ ይገኛል ። የወንጀል ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ አወሳሰናቸው በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት [5] የማዘዝ ሥልጣን ሥር መሆኑ ግልጽ ነው ። ስለሆነም የወንጀል ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚቀርበው የመጨረሻ ውሳኔ ሰሚ አብዛኛውን ጊዜ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ የተቃውሞ አቤቱታ መሆኑን መገመት ተገቢ ሆኖ ይገኛል ። በዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት [6] ተግባራት መካከል አንዱ የግለሰቦችን አካላዊም ሆነ ሕጋዊ መብቶች መከበራቸውን ማረጋገጥ መሆኑን ስንመለከት ከላይ የጠቀስነው አስተያየት ከምን ጊዜውም የበለጠ ተጨባጭና እሙን ይሆናል ። ስለዚህ በወንጀል ነክ ጉዳዮች ላይ " መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት በተገኘ ጊዜ የመጨረሻው ውሳኔ በሰበር ይሰሙ ዘንድ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተቃውሞ አቤቱታ እንዲሰማ ዐቃቤ ሕጉ ያሳስባል ። " በዚህም ዐቃቤ ሕጉ እንደ አንደኛው ተከራካሪ ወገን ሊወሰድ ይቻላል ። የተደረገው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሚጎዳው የተከሰሰውን ተከላካይ ወገን ፍላጐት ቢሆንም እንኳን ዐቃቤ ሕጉ እንደ ዕለት ከዕለት ሥራው በመቁጠር አቤቱታውን እንዲያሰማ ይጠበቅበታል ። በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ ግን ይህንን ጉዳይ ለመፈጸም የሚችል የመንግሥት አካል የሆነ መሥሪያ ቤት በባለጉዳይነት አይቀርብም ። ስለዚህ " መሠረታዊ የሕግ ስህተት " ያለበትን ፍትሐብሔር ነክ የመጨረሻ ውሳኔ አንዱ ወገን ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም ለጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንቱ እስካላሳወቀ ድረስ የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ እንደሆነ ሊቆይ ይችላል ። ከእነኚህ ባለሥልጣናት መካከል አንዳቸው በሆነ መንገድ የሕግ ስህተት ያለበት ፍትሐብሔር ነክ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን ሊደርሱበትም ይችላሉ ። ከዚህ በላይ ከጠቀስናቸው አኳኋኖች ውጭ " መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያላቸው " ፍትሐብሔር ነክ የመጨረሻ ውሳኔዎች ከሕግ ውጭ ቢሆኑም እንኳን በሥራ ላይ ከመዋል የሚያግዳቸው ነገር አይኖርም ። ይህን የመሳሰሉ የመጨረሻ ውሳኔዎችን ወደ ሚመለከተው ባለሥልጣን ፊት ሊያቀርብ የሚችል መንግሥታዊ መዋቅር እስከሌለ ድረስ ከላይ የጠቀስነው ጉዳይ ሐቅ ይሆናል ።

ፍትሐብሔር የተበዳይ ወገኖች የግል ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን " መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት " ያለበት የመጨረሻ የፍትሐብሔር ውሳኔ ለምን እነዚህን ታላላቅ የመንግሥት ባለሥልጣናት ይጠቅሳቸዋል ? የሚል ተገቢ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል ። ነገር ግን የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሰበር ስለመስማት ከላይ የተጠቀሱት የሕግ አንቀጾች የፍትሐብሔርንም ጉዳይ የሚጨምሩ ሆነው እናገኛቸዋለን ።

በተጨማሪ በጠቅላይ ፍ/ቤት ልዩ ችሎት አንድ ጉዳይ በሰበር እንዲሰማ ማመልከቻ ሊቀርብ የሚችልበትን ጊዜ ማስተዋልም እጅግ ጠቃሚ ነው ። ይኸውም የሚሆነው ፦

> . . . ውሳኔ በተሰጠ በ6 ወራት ውስጥ ይሆናል ። ሆኖም የተለያዩ ምክንያቶች ካጋጠሙና ጥያቄው በወንጀል የእሥራት ቅጣት የተፈረደበትን ተከሳሽ የሚጠቅም ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ላይወሰን ይችላል [7]።

ከላይ እንደተጠቀሰው " መሠረታዊ የሕግ ስህተት " ያለበት ፍትሐብሔር ነክ የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር ታይቶ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ለሕጉ ሊያቀርበው የሚችል መዋቅር አለመኖሩ ሁኔታውን ማወቅ በአብዛኛው ለአስተሳሰብና ትምህርታዊ እንዲሆን አድርጎታል ። የግል ባለጉዳዮችም ቢሆኑ " መሠረታዊ የሕግ

ስህተት ” በሚታይበት ጊዜ ምቹ በሆነ ዘዴ ሕግ ፊት ሊያቀርቡት አለመቻላቸውን ተገንዝበው ከወዲሁ ተስፋ ስለሚቆርጡ ከነጭራሹ አይጨነቁበትም ። ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት ባለሥልጣናትም ቢሆኑ በውሳኔ ላይ የታየው “ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ” ቢስተካከል የግል ባለጉዳዮችም የሚጠቀሙበት ሆኖ ካላገኙት እንዲያው ኃላፊነት ብቻ ተሰምቷቸው ጉዳዩ በሰበር እንዲታዩ አያደርጉም ። ነገር ግን ይህ አመለካከት የግል ባለጉዳዮች በመጨረሻ ውሳኔዎች “መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ” በሚኖርበት ጊዜ ጉዳዩን በሰበር ይሰማ ዘንድ ሊጫወቱት የሚገባውን ሚና በተመለከተ ሙሉ መፍትሔ ሊሰጠን አይችልም ።

የጠቅላይ ፍ/ቤትም ቢሆን፣ም ይህንን ልዩ የሆነ ውሳኔዎችን የመከለስ ሥልጣን ለምን እንደተሰጠው ፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤትም ሆነ የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ጉዳዮችን ለማንቀሳቀስ ይህ ኃላፊነት ለምን እንደተሰጣቸው ለመረዳት ከላይ በዝርዝር የተመለከትነው ሁኔታ ሊያስረዳን አይችልም ።

ስለሆነም ጠቅላይ ፍ/ቤቱም ሆነ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ወይም ሁለቱም የመንግሥት አካላት በተሰጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት ከተቋቋመበትም ዓላማ አንጻር ሲታይ “ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ” ያለባቸውን የመጨረሻ ወንጀል ወይም ፍትሐብሔር ነክ ውሳኔዎችን ወደ ሕግ ፊት አቅርበው እንዲስተካከሉ ባያደርጉ የተሰጣቸውን ኃላፊነትና ሥልጣን ያልተወጡ እንዲሁም የተቋቋመበትን ዓላማ ዘንግተዋል ሊያሰኛቸው የሚችል ነገር ቢኖር መመርመሩ አስፈላጊ ይሆናል ። ሀብቱም መሥሪያ ቤቶች “ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ” ያለባቸውን ወንጀልም ሆነ ፍትሐብሔር ነክ የመጨረሻ ውሳኔዎች በሰበር ታይተው እንዲስተካከሉ ማድረግን በግድ የሚጠይቁ ሌሎች ዓላማዎችና ተግባራት ሊኖሩዋቸው ይችሉ ይሆናል ። የመጨረሻ ውሳኔዎች በሰበር መስተካከል ሊኖሩት ከሚችሉት ዓላማዎች መካከል ፍ/ቤቶች ከስህተታቸው ይታረሙ ዘንድ የሚሰጠው ጥቅም ለማንም የተሰወረ አይደለም ። ነገር ግን ይኸን የመሰለ ዓላማ እንኳን በማይኖርበት ጊዜ የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሰበር የማሰማት ጥያቄ ዐቃቤ ሕግ በባለጉዳይነት በማይወክልበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ የመጨረሻው ውሳኔ የሚመለከታቸው ባለጉዳዮች ምርጫ ይሆናል ከማለት በስተቀር ሌላ አማራጭ አይኖረንም ። ስለሆነም እስቲ ከላይ የጠቀስነው ዓላማ ፣ ሥልጣንና ኃላፊነት ለነዚህ መንግሥታዊ አካላት ተሰጥቶ እንደሆነ ለማረጋገጥ እነኝሁ አካላት የተቋቋመበትን ዓላማ ፣ ያላቸውንም ሥልጣንና የተግባር ኃላፊነት እንመልከት ።

የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ካሉት ሌሎች ዓላማዎች በተጨማሪ የሚከተሉትም ይኖሩታል ፡—

> የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ሕጎች ደንቦች ትዕዛዞችና መመሪያዎች ሳይዛቡና በሁሉም ቦታ በአንድ ዓይነት ተፈጻሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ ፤ [8] በሕገ መንግሥቱና በሌሎች ሕጎች የተረጋገጠ የዜጎች መብቶችና ነጻነቶች እንዲከበሩ ማድረግ ።

ሥልጣንና ተግባርን በተመለከተ የጠቅላይ የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ደግሞ ከሌሎች በተጨማሪ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል ።

> ሕግ መንግሥቱና ሌሎች ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች በሚኒስቴሮች የመስተዳደሩ አካል በሆኑ ሌሎች መሥሪያ ቤቶች በማምረቻ በማከፋፈያና በአገልግሎት ሰጪ ተቋሞች በሕዝባዊ ድርጅቶች በሕብረት ሥራ ማህበራት በአካባቢዎች ውስጥ በሚገኙ አስፈጻሚ አካላት በባለሥል

> ልማዶቻቸውና በማንኛውም ግለሰብ መከበራቸውንና በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን በመቆጣጠር ሶሻሊስት ሕጋዊነትን ማረጋገጥ ። [9]

በሌላ ወገን የጠቅላይ ፍርድ ቤትም ፣ ካሉት ሌሎች ዓላማዎች በተጨማሪ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል ።

> በሕግ የተጠበቁትን የግለሰቦች መብቶች ጥቅሞችና ነጻነቶች ማስከበር፤ የሕግና የሥርዓት መጠበቅ እንዲጠናከር ሶሻሊስት ሕጋዊነት እንዲከበር ማድረግ ። [10]

ሥልጣንና ተግባርን በተመለከተ ደግሞ የጠቅላይ ፍ/ቤት ከሌሎች በተጨማሪ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር አለው ፦

> የዳኝነት አሠራርን ለማሻሻል የሕጎችን አንድ ወጥ አፈጻጸም ለማረጋገጥ ለፍ/ቤቶች መመሪያ መስጠት ። [11]

ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው በሙሉ የጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት የሕጎችን በትክክልና አንድ ወጥ አፈጻጸም የማረጋገጥ ሥልጣንና ተግባራት አሉዋቸው ።

በኢትዮጵያ ውስጥ በማንኛውም ሥፍራ ማንኛውም የመንግሥት አካል ፣ በተለይም ፍ/ቤቶች ፣ ሕዝባውያን ድርጅቶች ፣ አምራች ፣ አከፋፋይና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችና እንዲሁም ሌሎች በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ተቋሞች በተለይም ለአሠራራቸው ተገቢና ተግባራቸውንም ለመወጣት የሚጠቅሟቸውን ሕጎች በትክክልና በአንድ ወጥነት ሥራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነትና ግዴታ ተጥሎባቸዋል ።

በሌላ አነጋገር አንድ ወጥ የሆነ የሕግ አጠቃቀም እንዲኖር ማናቸውም መንግሥታዊ ተቋሞች ፣ ሕዝባውያን ድርጅቶችና ሌሎችም የመንግሥት አካላት ሥልጣናቸውንና ተግባራቸውን ሕጋዊ በሆነ መንገድ ማከናወን አለባቸው ። ይህም ማለት በአንድ ዓይነት ውሳኔ ሥር የሚገዙ ሁኔታዎች ውሳኔውን የሰጠው ግለሰብ ማንም ይሁን ማን ወይም የተሰጠው ውሳኔ የሚመለከተው ወይም ሊነካው የሚችለው ግለሰብ ማንም ይሁን ማን ፣ በአንድ ዓይነት መንገድ መታየት ይኖርበታል ። የሕጉ ትክክለኛና አንድ ወጥ አጠቃቀም የተንጸባረቀባቸው ውሳኔዎች ከሌሎች በተጨማሪ የሚከተሉትን ያካተቱ መሆን አለባቸው ፦

ሀ/ ንግድ ለማካሄድ የሚያስፈልገውን ፈቃድ ለመስጠት የሚደረጉ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በግለሰቦች ሊካሄዱ የሚችሉትን የንግድ ዘርፎች ከሌሎች መለየት ፣ ለተመሳሳይ የሥራ መስኮች ሊከፈሉ የሚገባቸውን የደመወዝ መጠን መወሰንና የመሳሰሉትንና ፣ እና ፤

ለ/ በደል የደረሰባቸው ግለሰቦች የሚካሱበትን ዘዴ ለመሻት የሚደረጉ ሕጋዊ ውሳኔዎች ፣ በደል አድርሰው የተወነጀሉ ግለሰቦችን በጥፋተኛነት መያዝ ፣ በተያዙበት ወንጀል ጥፋተኛነታቸው የተረጋገጠባቸው ወንጀለኞች ላጠፉት ጥፋት ተገቢ የሆነ ቅጣት የሚያገኙበትን ሁኔታ መሻትና የመሳሰሉትን ።

ፍ/ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ችሎት ማስቻላቸው ግልጽና የታወቀ ጉዳይ ነው ። የወንጀልም ሆነ የፍትሐብሔር ችሎቶችን ለማስቻልና እነኝህም ሁኔታዎች የሚገዙበት ሕጎች መኖራቸው ደግሞ በእንጻሩ ግልጽ ሆኖ ይገኛል ። ስለዚህም ፍርድ ቤቶች የወንጀልም ሆነ የፍትሐብ

ሔር ጉዳዮችን በሚመለከቱበት ጊዜያት በሙሉ ጠቅላላው ሕጋዊ ሂደት በተገቢ ሕጎች ትክክልና አንድ ወጥ አጠቃቀም ላይ የተመረኮዘ መሆን አለበት ። ባለጉዳዮችም ቢሆኑ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት አንድ ወጥና ትክክለኛ ሕግ በሥራ ላይ ማዋላቸውንና መጠቀማቸውን ማየት የዘወትር አትኩሮታቸው ሆኖ ይገኛል ። የፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔዎች አንድ ወጥና ትክክለኛ በሆኑ ሕጎች ላይ እስከተመሠረቱ ድረስ ፣ ችሎቶች የተካሄዱት ትክክለኛና አንድ ወጥ ሕጋዊ መንገድን ተከትለው ይሁን ወይም አይሁን በአብዛኛው የባለጉዳዮች ችግር (ጭንቀት) ሆኖ አይታይም ። አንድ ወጥና ትክክለኛ የሆነ የሕግ አጠቃቀም ካለና ይህም በሥራ ላይ መዋሉ በመንግሥት አካላት የቅርብ ክትትል የሚደረግበት እስከሆነ ድረስ የወንጀልና ፍትሐብሔር ነክ ጉዳዮች በችሎት በሚታይበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች ትክክለኛና አንድ ወጥ ሕግ መጠቀም ይኖርባቸዋል መባሉ ያልተለመደ ጉዳይ ነው ሊባል አይቻልም ። ከዚህ በላይ የጠቀስነው ጉዳይ የጠቅላይ ፍ/ቤት በችሎት በተሰየመበት ጊዜ ሁሉ በግብርና ሊተረጉመው የሚገባ ጉዳይ በላይ የተቋቋመበት ስላማዊ ሆኖ ይገኛል ። በሌላ አነጋገር ፍ/ቤቶች ችሎት በሚያስችሉበት ወቅት ሕጎችን በትክክልና በአንድ ወጥነት መጠቀማቸውን ማረጋገጥ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ብቻ አለመሆኑን እንገነዘባለን ። ከጠቅላይ ፍ/ቤት ተግባራት መካከልም እንደ አንዱ ሆኖ ተቀምጧል ።

ከላይ ከተጠቀሱት የዐቃቤ ሕግ ተግባራትና ሥልጣናት እንደምንገነዘበው ሶሻሊስት ሕጋዊነት ማለት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሥልጣናት በሙሉ አንድ ወጥና ትክክለኛ የሆነ ሕግ በመላው አገሪቱ ጥቅም ላይ መዋሉን ከማረካገጥ ሌላ ምንም ነገር ሊሆን አይችልም ። ይህ ኃላፊነት ደግሞ በኅብረተሰቡ ውስጥ በተራ ባለጉዳይነትም ሆነ ውሳኔዎችን ለመስጠት ሥልጣን ያላቸውን የመንግሥት ባለ ሥልጣናትም የሕግን በደንብ በሥራ ላይ መዋል ማረጋገጥን ጭምር ሊሆን ይችላል ።

ሶሻሊስት ሕጋዊነትን ዘንድ (በግብር ይታይ ዘንድ) የሕጎችን አንድ ወጥነትና ትክክለኛነት ማረጋገጥ ከላይ የጠቀስናቸው ሁለቱ የመንግሥት አካላት ተግባራትና ሥልጣናት መሆናቸው የሆነው ሆኖ አንድ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ሥራውን ያከናውን ዘንድ አንድ ወጥና ትክክለኛ የሕግ አጠቃቀምንም ማረጋገጥ በተመለከተ የጠቅላይ ፍ/ቤት የቁጥጥር ሥልጣን በፍ/ ቤቶች አካባቢ ብቻ የተወሰነ ነው ። በሌላ ወገን ደግሞ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በማናቸውም የመንግሥት አካላት [12] ውስጥ አንድ ወጥና ትክክለኛ የሕግ አተረጓጎምና አጠቃቀም የማረጋገጥ ኃላፊነት ቢኖረውም ይህ ኃላፊነት የፍርድ ቤቶችን ሕጋዊ እንቅስቃሴዎችን አይጨምርም ። በተጨማሪ ግን የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ወይም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕጎችን አንድ ወጥና ትክክለኛ አጠቃቀም የማረጋገጥ ተግባር ያከናውናል ። ነገር ግን በሥልጣን ዝቅተኛ የሆኑ ፍርድ ቤቶች ሥራቸውን ሲያከናውኑ ሕጎችን በአንድ ወጥነትና በትክክለኛነት በሥራ ላይ መዋላቸውን መቆጣጠር የጠቅላይ ፍርድ ቤት አንዱ በሕግ አውጭው የተሰጠው ሥልጣኑ መሆኑ አይካድም ። በተሰጠው ውሳኔ አንዱ ወገን ይግባኝ ቢልም ከላይ የጠቀስነው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ተግባርና ኃላፊነት በማናቸውም ጊዜ መከናወን ይገባዋል ። ባለጉዳዮች በመሠረቱ ይግባኝ የሚያቀርቡት የመጨረሻ ውሳኔን በተመለከተ ብቻ ስለሆነ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማናቸውም ጊዜ በራሱ አነሳሽነት ከላይ የጠቀስነውን ቁጥጥር ማድረግ የሚገባው መሆኑን የበለጠ ያጠናክርልናል ። የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት አቤቱታም ሆነ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የሚሰጠው ውሳኔም ቢ

ሆን ሁለቱም ሊንቀሳቀሱ የሚችሉት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ንም ሆነ የሌሎች አነስተኛ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔን ብቻ ተመርኩዘው ነው ።

የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዮችን በሰበር በሚመለከትበት ጊዜ ፕሬዚዳንቱ ወይም ምክትል ፕሬዚዳንቶች በአባልነት እንደሚገኙ የተገለጠ መሆኑ ጉዳዩን የሚመለከተው ጉባኤ [13] ከላይም የጠቀስነውን ተግባሩን ይወጣ ዘንድም ይረዳዋል ። ይሁን እንጂ የሕጎችን አንድወጥ አጠቃቀም በበላይነት የመቆጣጠርና የመመልከት ተግባር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ተግባራት በአጭሩ ሲታዩ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት ነው ማለትም ይቻላል ። በሌላ ወገን ደግሞ “ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ” ያለባቸውን የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በዐቃቤ ህግ ወይም ፍትሐብሔር ነክ ጉዳይ ሲሆን ከተከራካሪዎቹ በአንዱ አማካይነት ሲቀርብለት በመመልከትና ሶሻሊስት ሕጋዊነትንም ማረጋገጥ ሆነው ይገኛሉ ። የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሰበር ስለሚመለከትን ስናጤን (የአንድ ውሳኔ መሻር ስሜት ሊሰጥ የሚችለው በሚደረገው መሻር ቢያንስ አንዱ ወገን የሚጠቀምበት ሆኖ ሲገኝ ነው ከሚለው እውነታ አንጻር ሲታይ) ተበደልኩ ባይ አንዱ ወገን ጥያቄውን በአቤቱታ ወይም በማመልከቻ መልክ እንዲሰማ ካላቀረበው በቀር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሰበር የመስማት ተግባር አይኖረውም ።

የሆነው ሆኖ “ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ” ያለባቸውን የመጨረሻ ውሳኔዎችን ለማሻሻል ረገድም ቢሆን ውሳኔው ይመረመርለት ዘንድ የሚፈልግ ወገን ማድረግ የሚችለው ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ የሶሻሊስት ሕጋዊነትን ስሜት በተመረኮዘ ሁኔታ አቤት ማለት ይሆናል ። ይህም ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔያቸውን በሚሰጡበት ጊዜ ሶሻሊስት ሕጋዊነትን መመሪያቸው ያደርጉ ዘንድ አንዱ አረጋጋጭ ሁኔታ ሆኖ ይገኛል ። ከላይ የጠቀስነው ሁኔታ መደበኛ ይግባኝ በተመለከተም ጭምር እውነታ አለው ። ስለዚህ ፣ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ማንም ተከራካሪ ወገን እንደሚያደርገው ሁሉ በራሱ አነሳሽነት የሶሺያሊስት ሕጋዊነትን በተግባር መተርጐምና በሥራ ላይም መዋልንም ጭምር አስገዳጅነት ሊጠይቅ አይችልም ። አይገባውም ! በሌላ በኩል ግን ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ጉባኤ እንደማናቸውም መደበኛ ፍርድ ቤት የማናቸውንም መደበኛ ፍ/ቤቶች የጠቅላይ ፍ/ቤትን ጨምሮ የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሌላ ተለዋጭ ውሳኔ መተካትና የውሳኔውንም አፈጻጸም በአስገዳጅነት የመጠየቅ መብትና ሥልጣን ተሰጥቶታል ። ይህንን ካልን ዘንድ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ጉባኤ የፍርድ ቤቶችን የመጨረሻ ውሳኔዎች በተመለከተ የወንጀል ጉዳዮችንም ቢሆን ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢቃወምም እንኳን “ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ” አለባቸው ብሎ የሚገምታቸውን የመጨረሻ ውሳኔዎች በሙሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ለመሰረዝና በሌላ ተለዋጭ ውሳኔ ለተመለከተ ተግባርና ኃላፊነት ተሰጥቶታል ማለት እንችላለን ። የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግም ሆነ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች በአንድ የመጨረሻ ውሳኔ ውስጥ “ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት” ኖረውም አልኖረውም የሚኖራቸው አቋም በክለሣ ሲታይ ለሚሰጠው ውሳኔ ምንም ፋይዳ አይኖረውም ። ነገር ግን ውሳኔውን ማሻሻል ለሚችለው ጉባኤ እንደተጨማሪ አሳማኝ ሁኔታ ሆኖ መቅረቡ አያጠራጥርም ።

የጠቅላይ ፍርድ ቤት ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር በሚያይበት ጊዜ በበታች ፍ/ቤቶች ዘንድ የሕጐችን አንድ ወጥ አሠራር የማረጋገጥ ተግባሩን እየተወጣ መሆኑ አያጠራጥርም ። ምክንያቱም ውሳኔዎችን በሰበር መመልከት ልክ እንደማንኛው ተራ ይግባኝ ከላይ የጠቀስነውን የጠቅላይ ፍርድ ቤት ተግባር በግልጽ ስለሚያመለክት ነው ። ይህንን ካልን ዘንድ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ

ጉባኤ ከተከራካሪ ወገኖች ፍላጐትና ግምት ውጭ እንኳን ቢሆን በሰበር ውሳኔዎችን በመለወጥና በማሻሻል የሕጐችን አንድ ወጥ አጠቃቀም በማረጋገጥ ረገድ የመልካም ሕግና ፍትህ አስተዳደር የሚሰፈን ኃላፊነቱን ይወጣል ። በአንጻሩ ደግሞ ወንጀል ነክም ሆነ ፍትሐብሔር ነክ የመጨረሻ ውሳኔዎችን በጠቅላይ ፍ/ቤት ጉባኤ ከሰበር መስማት ለተከራካሪ ወገኖች እንደ ተሰጠ እንደ አንድ ተጨማሪ የይግባኝ መብት መቁጠር በፍጹም ስህተት መሆኑ ሊጠቀስ ይገባል ።

ነገር ግን “ የሕጐች አንድ ወጥ አጠቃቀም ” ለማረጋገጥ ብቻ ሲባል የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሰበር ማስማት ልክ ውሳኔዎች “ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ” በማናቸውም ጊዜ የሚያስፈልገውን ያህል ሊሆን አይችልም የሚለውን መከራከሪያ ነጥብ ለማሳመን አዳጋች የሚሆን አይመስለኝም ። የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ጉባኤ “ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ” በሚኖርበት ጊዜ ውሳኔውን ከመረመረ በኋላ ሳይለውጥና ሳያሻሽል እንኳ የበታች ፍርድ ቤቶች “ የሕጐችን አንድ ወጥ አጠቃቀም ” ለማረጋገጥ ሕጐችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው በመመሪያ መልክ ሊያሳስባቸውና ሊያስገነዝባቸው ይችላል ። ስለዚህ ፡ ቢያንስ ከተከራካሪዎች ወገኖች አንዱ የተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ በጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር ይታይለት ዘንድ ፍላጐቱን የገለጠ እንደሆነ የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ጉባኤ ጉዳዩን ያመለክታል የሚለው ማከራከሪያ ሃሳብ ተአማኙ ይሆናል ።

ባለጉዳዮች የይግባኝ መብታቸውን ከጨረሱ በኋላ የጠቅላይ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሰበር ይመለከት ዘንድ አቤቱታ ሲያቀርቡ ጉባኤው “ የሕጐችን አንድ ወጥ አሠራር ” የማረጋገጥ ተግባሩን ለመወጣት ሲል ጥያቄውን መቀበል ይገባዋል ። የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ጉባኤ ሌሎች የጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶችም ሆኑ ሌሎች ዝቅተኛ ፍ/ቤቶች ለወደፊቱ “ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ” ያለበት ውሳኔ እንዳይሰጡና ውሳኔያቸውንም በአግባቡ ይመረምሩ ዘንድ ለማስተማር የመጨረሻ ውሳኔዎቻቸውን መመርመር ይገባዋል ። ታዲያ የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ጉባኤ “ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለባቸውን ” የዝቅተኛ ፍ/ቤቶች ውሳኔዎችን በተመለከተ የተሻሻለውን ፍርድ ይሰጥ ወይስ ለነዚሁ ዝቅተኛ ፍ/ቤቶች የተጠቀሰው ስህተት መገኘቱን ብቻ በመመሪያ መልክ መግለጡ ያበቃዋል ?

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ከዚህ የሚከተለውን ጥያቄ ማንሳት አስፈላጊ ይሆናል ። ከበስተኋላው ምን ምክንያት ቢኖረው ነው ፡ ሕግ አውጭው በመንግሥት አካላት ፡ ሕዝባውያን ድርጅቶች ፡ ሸቀጦችን በማምረትና በማከፋፈል ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች አገልግሎት ሰጪዎችንና ግለሰቦችንም ጭምር ጥብቅ የሆነ አንድ ወጥ የሕጐችን አጠቃቀም የማረጋገጥን ተግባር ሊሰጣቸው የቻለው ? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የሶሻሊስት ሕብረተሰብን የሶሻያሊስት እድገት ጐዳና የሚከተሉ ሕብረተሰቦች የሚመሩበትን ጽንሰ ሃሳብና የዕድገት መመሪያዎቻቸውን መመርመር አስፈላጊ ይሆናል ።

የነዚህ ሕብረተሰቦች መመሪያ ሶሻሊያዝም ነው ። ፍላጐታቸው ዕድገታቸውን በሶሺያሊዝም መርሆዎች በመምራት የተፋጠነ ሕብረተሰባዊ ዕድገት ለህዝባቸው ለማምረት ነው ። እንደዚሁም ሕብረተሰባቸው የሶሻያሊስታዊ የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ላይ የደረሰላቸው ሕዝቦች ደግሞ ወደ ኮሚኒስታዊ የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ሲሉ ዕድገታቸውን በዕቅድ በመምራት ላይ ይገኛሉ ። በአንጻሩ የሶሻሊዝምን የዕድገት ጐዳና የመረጡ በቅድመ ካፒታሊስታዊ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሕዝቦች ደግሞ የደረጁ የአውሮፓ መንግሥታት የዕድገት ታሪክ እንደሚያሳየው ካፒታሊዝምን ጨምሮ ሌሎች የዕድገት ደረጃዎችን በመዝለል ሶሻሊስት

የሆነ የዕድገት ደረጃ ላይ በመድረስ ዕድገታቸውን በፕሮግራም በመምራት ሂደት ላይ ናቸው ።

በሳይንሣዊ ሶሻሊዝም መርሆዎች መሠረት ፡ ማናቸውም አመራር በሳይንሣዊ ሶሻያሊዝም መርሆዎች እስከተመራ ድረስ ሕብረተሰቦች ከፍተኛ የሆነው የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ላይ ሊደርሱ ይችላሉ ። አንድ ጊዜ እንደዚህ ዓይነት መንግሥት ከተመሠረተ በኋላ ፡ ሕብረተሰቡ የተፈለገውን የዕድገት ደረጃ በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ይደርስ ዘንድ የያንዳንዱን የኅብረተሰብ አባል ንቃተ ህሊናና የሕብረተሰቡም የኢኮኖሚ ማኅበር በጣም አስፈላጊ ነው ። ይህንንም ግብ ለመምታት በሶሻያሊዝም መርሆ ላይ የተመረኮዘ ሕብረተሰባዊ አውቃቀርና ፡ ግንኙነትን መፍጠር አስፈላጊ ይሆናል ። በሌላ አነጋገር ፡ የኅብረተሰቡን እርስበርስ ግንኙነትና አወቃቀር ለተተለመው የዕድገት ደረጃ እውን መሆን ይረዳሉ ተብለው የሚገኙትን ሕጐችና ደንቦች ማውጣት እጅግ አስፈላጊና የሚደነቅ ነገር ነው ። የተተለመው የዕድገት ደረጃ በሥራ መታየት እውን መሆን እስካለበት ድረስ ያግሞ ፡የኅብረተሰቡን የዕድገት ሁኔታ የሚጠቁሙትን እነዚህን ሕጐች ማናቸውም የሕብረተሰቡ አባል በደንብ ይጠብቃቸውና ተፈጻሚነታቸውንም ሥራዬ ብሎ መከታተል ይገባዋል ። ይህ ደግሞ በተራው ፡ ሶሻያሊስት ሕጋዊነት መረጋገጡ ግልጽ ይሆን ዘንድ የሕብረተሰቡን ግንኙነትና አወቃቀር የሚያሳዩትን ሕጐች በአውንታም ሆነ በአሉታ በሕግ ተደንግገው ጥብቅና አንድ ወጥ አጠቃቀማቸው መረጋገጡ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል ። ካፒታሊስታዊ የዕድገት ጐዳና የሚከተሉ ኅብረተሰቦች የሕግ ሥርዓት ውስጥ ምናልባትም “ ሊያፈሩ ” (ሊሰኩ) የማይችሉትን ሕጋዊ ያልሆኑ የፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔዎች የሶሻያሊስት ዕድገት ጐዳና በሚከተሉ አገሮች ግን የመንግሥት ባለሥልጣናት ጣልቃ በመግባት ጠፍትሄ ይሰጧቸው ዘንድ የሚያስችላቸው መሣሪያዎች ማዋቀር እጅግ አስፈላጊ ይሆናል ። ሕግ በማንኛውም ሕብረተሰባዊ ዕድገት ጐዳና ለማደግ በሚፈልጉ አገሮች ውስጥ አንዳንድ ጠቃሚ መሣሪያ መቆጠሩን ሕግ በሶቪዬት ኅብረት ውስጥ ከሚጫወተው ሚና አንጻር ልንመለከተው እንችላለን ። ይህም ችግር ለማቃለል የሚረዳ የሕግ ተግባር ተብሎ የተቀመጠው ሲሆንና ፡ በዚህም ሕግ ትምህርት ሰጪነትማና ከመጫወቱም በላይ ሰዎች የኅብረተሰቡን ሕጎች እንዲማሩና የሚጠበቅባቸውንም በኅብረተሰቡ ውስጥ ሊያደርጉትና ሊከተሉት የሚገባቸውን ግንኙነት እንዲያውቁት በማድረግ ለተሰማለት [14] የሕብረተሰብ ዕድገት ደረጃ የሚደነቅ አስተዋጽኦ ድርሻውን ይከፍላል ። ሕግ ከዚህ በላይ የጠቀስነውን በተግባር እንዲፈጸም አስፈላጊ ከሆነ ጥብቅና አንድ ወጥ አጠቃቀሙን የሚያረጋግጡ መሣሪያዎች ደግሞ በአንጻሩ መዋቀር አለባቸው ።

ከላይ ለማስገንዘብ እንደሞከርነው ፡ የነዚህ መሣሪያዎች በተግባር ላይ መዋል ለግለሰቦች የተተወ እንደሆነ ደግሞ የሕጐችን ጥብቅ አሠራር ማረጋገጥ ስለማይችሉ የሕጐች ጥብቅና አንድ ወጥ አጠቃቀም ሊኖር አይችልም ። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን ወንጀሎችን በክስ አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ የሚያስቀጣ ወንጀል ቀላልና (የግል አቤቱታ) ከባድ ወንጀሎች በማለት መከፈል ነው ። ቀላል ወንጀሎች የግለሰቦችን ግላዊ ጥቅም ብቻ ሊነኩ የሚችሉ ወንጀሎች ናቸው ። ይህ ከሆነ ዘንዳ በክስ አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጣ ወንጀል ወደ ህግ ፊት ማቅረብና ተገቢውን ቅጣት ማስወሰን ጉዳቱ በደረሰበት ግለሰብ ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሠረተ ይሆናል ። በሌላ ወገን ደግሞ ከባድ ወንጀሎች የሚመለከቱት የጉዳቱ ቀጥተኛና ቀዳሚ ተጐጂውን ግለሰብ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ህብረተሰቡን በመሆኑ ወደ ህግ ፊት ማቅረቡና ተገቢውን ቅጣት የማስቀጣቱ ኃላፊነት ለመንግሥት አካል ይሰጣል ።

ይህም የመንግሥት አካል የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መሥሪያ ቤት ነው ። ይህም ለአንድ ማህበረሰብ እድገት እጅግ አስፈላጊና ያለሱም ዕውን ሊሆን የማይችለውን የሕግንና ሥርዓትን መከበርና መጠበቅ ለማረጋገጥ ህብረተሰቡ የወንጀሎችን መፈጸም መከላከል ስለሚገባው ነው ። ነገር ግን ህብረተሰቡ ወንጀሎችን ለመከላከል ብርቱ ጥረት እያደረገ እያለ ወንጀሎች ተፈጽመው ሲገኙ ከባድ ወንጀል ፈጽመው የተገኙ ግለሰቦች በሙሉ ህብረተሰቡ ተገቢውን ቅጣታቸውን በመስጠት ደግመው ጥፋት ላይ እንዳይገኙ ማድረግ ይኖርበታል ። ከባድ ወንጀል የፈጸሙ ግለሰቦችን የመቅጣት ኃላፊነት የተፈጸመው ወንጀል በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳት ለደረሰባቸው ግለሰቦች መተው ህብረተሰቡ ለወደፊት ወንጀል ሊፈጽሙ ይችላሉ ተብለው የሚጠረጠሩትን ግለሰቦች በሙሉ ከዚህ አድራጎት ይገቱ ዘንድና ወንጀልንም ሳይፈጽም አስቀድሞ ሊደረግ የሚገባውን ዋና የህብረተሰቡን ፍላጐትና መልካም አስተሳሰብ ፋይዳ ቢስ ማድረግ ይሆናል ። ይህ ደግሞ ጉዳት የደረሰባቸውን ግለሰቦች ወንጀለኞችን ለተለያየ ምክንያቶች ለምሳሌም እንደ ካሳ የመሳሰሉትን ካገኙ በኋላ ወንጀለኞቹ ተገቢውን ቅጣት ሲያገኙ ነጻ እንዲለቀቁ የተመቻቸ ሁኔታዎችን እንዲፈጥሩ ያበረታታቸዋል ።

የአንድ አገር የሕግ ሥርዓት ለአገሪቱ ማህበራዊ ዕድገት አስፈላጊ መሆኑን ከተገነዘብን ዘንዳ በተለይም የሶሻያሌስት የዕድገት ጉዳናን የሚከተሉ ህዝቦች ለሚያስሙት የዕድገት ደረጃ የሚከተሉት የሕግ ሥርዓት ከፍተኛ አስተያየት ያደርግ ዘንድ የመጨረሻው ውሳኔዎችን በሰበር መስማት የመሳሰሉትን መዣሪያዎች በመንግሥት ባለሥልጣኖች ኃላፊነት ሥር ማዋቀር ይገባቸዋል ። በሰበር ሰሚነት መሠረታዊ የሆኑ የሕግ ስህተቶች ሊታረሙ እስከቻሉ ድረስ የሕጐች ጥብቅና አንድ ወጥ አጠቃቀም መረጋገጡ አከራካሪ አይሆንም ።

የሆነው ሆኖ ግን በተመሳሳይ ምክንያት እንደሚታወቀው ሁሉ " መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት የመጨረሻ ውሳኔ በስውር ቢሻሻልም ጥቅም ሊያገኝ የሚችለው ወገን የአፈጻጸሙን ሁኔታ ተከታትሎ የመጨረሻ ውጤት ለማግኘት ጥረት እስካላሳየ ድረስ የመጨረሻ ውሳኔ ተሻሻለ ወይም ተለወጠ ለማለት አያስደፍርም ። ነገር ግን ፍርዶች ሳይፈጸሙ መቅረታቸው ሊሻሻሉ ወይም ሊቀየሩ አይገባቸውም ማለት አይደለም ። ምክንያቱም " መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት" የመጨረሻ ውሳኔዎች መርምሮ ፍርዱን መቀየር ወይም ማሻሻል ከላይ የጠቀስነውን " የሕግን መልካም አስተዳደር ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ አንድ ወጥ የሕግ አጠቃቀም " ለፍርድ ቤቶች ፍትህ የተመላበት አሠራር አስፈላጊ መሆኑን ማረጋገጥ ከመሆኑም በላይ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ አብይ ተግባር ሆኖ ይገኛል ።

የሆነውሆኖ ግን የሕጐችን አንድ ወጥ አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔዎች መመርመር ያስፈልጋል የሚለው የመከራከሪያ ነጥብ ውሳኔዎቹ " መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት " እንዳለባቸው ተቆጥሮ ሊመረምሩ ያስፈልጋል የሚለውን አቋም ሊያሰ.ይዘን አይገባም ።

ከላይ እንደጠቀስነው የጠቅላይ ፍ/ቤት ጉባኤ የበታች ፍርድ ቤቶች እንዴት አድርገው ሕጐችን በሥራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው መመሪያዎችን መስጠት ይችላል ወይ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል ። በዚህም አንድ ባለጉዳይ በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታውን ማሰማትና ውሳኔውም ይመረመርለት ዘንድ ጥያቄ የሚያቀርብ ከሆነ በመጨረሻ ላይ የተለወጠለትን ወይም የተሻሻለበትን ውሳኔ ለማስፈጸም የሚጠይቅ መሆኑን መቀበል እጅግ አስፈላጊ ይሆናል ። ይህም ሊሆን የሚችለው ሙቼውንም ቢሆን ውሳኔው እንዲሻሻልለት ጥያቄ

ውን ያቀረበው ሰው በሰበረ ሰሚው ጉባኤ የተሰጠው ወይም የተሻሻለበት ውሳኔ የበለጠ የሚጠቀመው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ አያጠራጥርም የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ጉባኤም ቢሆን ከአንድ ከዝቅተኛ ፍ/ቤት በተለይ ውሳኔ ላይ ተበደልኩ ባይ ባለጉዳይ የሚጠብቀው ይኸንኑ ከላይ የጠቀስነውን ቅድመ ሁኔታ ብቻ ነው ። ይህ ደግሞ እንደገና አንድ ተበደልኩ ባይ ባለጉዳይ ጥያቄ ቢያ ቀርብም ባያቀርብም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ከተግባሮቹ አንዱ የሆነውን ማለትም :—

የዳኝነት አሠራርን ለማሻሻልና የሕጎችን አንድ ወጥ አፈጻጸም በማረጋገጥ ለፍርድ ቤቶች መመሪያዎችን መስጠት [15]

ለመወጣት ሲል ብቻ የዝቅተኛ ፍ/ቤቶችን የመጨረሻ ውሳኔዎች መመርመሩ ተቀባይነት ያለው አሠራር ነው ።

ፍርድ ቤቶች ፍትህ ነክ ተግባራቸውን ለመወጣት አንድ ወጥ የሕጎችን አጠቃቀም ይከተሉ ዘንድ ማረጋገጥ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ኃላፊነት ሆኖ ሳለ ከዚህ ቀጥሎ ለተመለከተው አንዱ የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ተግባር ምን ትርጉም መስጠት ይገባናል የሚለውን ጥያቄ ማንሳት እጅግ አስፈላጊ ይሆናል ። ይኸውም :—

የፍርድ ቤቶችን ውሳኔዎችና ትዕዛዛት ሕጋዊነት መከታተል ። [16]

ለዚህ ጥያቄ መልስ ከመስጠታችን በፊት የሚከተሉትን ነጥቦች ከሃሳባችን ውስጥ ማስቀመጥ ይኖርብናል ። ከላይ እንደጠቀስነው ፡ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የሕጎችን ትክክለኛና አንድ ወጥ አጠቃቀም የሚያረጋግጥበት መሳሪያ ከነጥቦቹ መካከል አንዱ ነው ። ይህም ከሕግ ውጭ የተሰጡ የዝቅተኛ ፍርድ ቤቶችን ውሳኔዎች በሥልጣን የሆኑ ፍርድ ቤቶች እንዲሠርዙዋቸው ለማሳሰብና ለማመልከት ጭምር ነው ። ስለሆነም ጠቅላላው በሥልጣን ከፍተኛ የሆኑ ፍርድ ቤቶች በተለይም የጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ጉባኤ ከሕጉ ውጭ የሆኑ የአነስተኛ (ዝቅተኛ) ፍርድ ቤቶችን ውሳኔዎች በመሻርና በመለወጥ ሶሻያሊስት ሕጋዊነትን ማረጋገጣቸው ግልጽ ይሆናል ።

ከላይ እንደተጠቀሰው በአዕምሮአችን ልናስታውሰው የሚገባን ሁለተኛ ነጥብ ቢኖር በሶሻሊስት ፍልስፍና የሚመሩና የሶሺያሊስት የዕድገት ጐዳና የሚከተሉ ሕብረት ሰቦች የሕግ ሥርዓት ፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ " ቀሲቃሽ " ለአሠራሩም ከተከራካሪ ወገኖች በአንዱ አማካይነት " ጉትጉታና ቅስቀሳ የሚያስፈልገው " ከሆነ ይህንኑ ሥርዓት በሥራ ለመተርጐም ሕግ በሶሺያሊስት ሥርዓት ማህበር ውስጥ ሊጫወተው የሚገባውን ሚና የበለጠ ማጉልበት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ የሶሻያሊስት ህጋዊነትን የማረጋገጥ ድርሻውን መወጣት መቻሉን ይጠይቃል ። ታዲያ ይህ መሆን ካለበት ደግሞ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ በፍ/ቤቶች ውሳኔዎች ላይ ከተከራካሪ ወገኖች ምንም ዓይነት አቤቱታ ባይሰነዘርም እንኳን ፡ ተገቢውን መመሪያ ለዝቅተኛ ፍርድ ቤቶች መስጠት ይቻለው ዘንድ የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔዎች ሊመረምር ይገባዋል ።

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተገቢ የሆኑ መመሪያዎች መስጠት ይችል ዘንድ በአንድ ወጥ የህግ አጠቃቀም ላይ ያልተመረኮዙ ውሳኔዎች በሚኖሩበት ጊዜ ይህንኑ ሁኔታ ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የማሳወቅ ኃላፊነት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ላይ የተጣለ መሆኑ ግልጽ ነው ። ይህ ተግባር የፍ/ቤቶችን የመጨረሻ ውሳኔዎችንም መጨመሩ ደግሞ በአኳያው ግልጽ ነው ። በወንጀል ነክ ጉዳዮች ላይ ብቻ አግባብ ካለው ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ጋር ሲነጻጸር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚ

ዳንት ” መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሁተት ” ያለባቸውንና ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ውሳኔዎች ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ ማቅረብ የሚችል ዓይነተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን ነው ። ይህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ተግባር የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ አንድ ወጥ የሕግ አጠቃቀም የማረጋገጥ ተግባሩን እንዲወጣ የሚያደርገው ቅድመ ሁኔታ መፍጠሩን ስንመለከት ከላይ የጠቀስነው ሁኔታ እውነታነቱ የበለጠ ግልጽ ይሆናል ።

በሌላ ወገን ደግሞ ፡ የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መሥሪያ ቤት ፍርድ ቤቶች ፍትሐብሔር ጉዳዮችን በተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ይቻላቸው ዘንድ በፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎችንና ትዕዛዛትን ይጠቀሙ አይጠቀሙ የሚያውቅበት ምንም መንገድ የለውም ። በተጨማሪ ፡ ከላይ ለማስቀመጥ እንደተሞከረው የጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ስሚ ጉባኤ ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ጨምሮ በበታች ፍርድ ቤቶች ተግባራቸውን ሲያከናውኑ የሚሰጡትን ትዕዛዛትንና ውሳኔዎችን በመመርመር አንድ ወጥ የሕግ አጠቃቀም መኖሩን ማረጋገጥ ፡ አለበት ። የውሳኔዎችንና የትዕዛዛትን ሕጋዊነት የመከታተል ተግባርና “ ኃላፊነት ” የሕግን መልካም አስተዳደር ማሻሻልና የሕጐችን አንድ ወጥ አጠቃቀም “ ማረጋገጥ ” በሚለው ጽንሰ ሀሳብ ውስጥ የሚያጠቃልል መሆኑን ስናስተውል ይኸው ተግባር ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊተው ይገባል ። የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መሥሪያ ቤት ሊያደርግ የሚችለው ነገር ቢኖር ለሌሎች የበላይ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ይግባኝ ማሰማት ብቻ መሆኑን ስንመለከት ከዚህ በላይ የገለጽነው ጉዳይ ከምንጊዜም ውም የበለጠ ምክንያታዊ ይሆናል ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

* የኢ. ሀ. ድ. ሪ. ምክትል ዐቃቤ ህግ ኤል አል ቢ ፣ የሕግ ፋኩልቲ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ / ቀ.ኃ.ሥ.ዮ./ ፤ የፒ. ኤች. ዲ. እጩ ፣ ኤድንበርድ ካርድልጅ ዩኒቨርሲቲ/ዩጐስላቪያ/ በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ የሕግ ፋኩልቲ ፣ የትርፍ ጊዜ መምህር ።

1. የጠቅላይ ፍርድ ቤት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 9 ፣ አንቀጽ 4/4 በግልጽ ተለይቶ እስካልተሰጠ ድረስ በዚህ ቁጥር የተመለከቱ አዋጆች በሙሉ እ. ኢ. በ1987 የታወጁ ናቸው ።/
2. በፍርድ ቤቶች አደረጃጀት ውስጥ በማንኛውም ከፍታ የሚገኝ ፍርድ ቤት ክፍል የሚያመለክት የአማርኛ ቃል ። ነገር ግን እዚህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ ለማለት ተጠቅመንበታል ።
3. የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 20
4. የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 5/ 1/
5. የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ይመልከቱ ።
6. የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 10
7. ከላይ በቁጥር 1 የተመለከተውን አዋጅ አንቀጽ 5/ 2/
8. ከላይ በቁጥር 5 የተመለከተውን አዋጅ አንቀጽ 4
9. —''— —''— —''— —''— —''— አንቀጽ 10//1/
10. ከላይ በቁጥር 1 የተመለከተውን አዋጅ አንቀጽ 3
11. —''— —''— —''— —''— —''— አንቀጽ 22/2/
12. ሶሻያሊስት ሕጋዊነትን የማረጋገጥ ተግባራቸውን የመቆጣጠሩ ሥልጣን ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባር ውጭ የሆኑ መንግሥታዊ አካላት መኖራቸው የታወቀ ነው መንግሥት ምክር ቤት አንዱ ነው ።
13. ከላይ በቁጥር 3 ላይ ይመልከቱ
14. በመፍትሔ ሰጭነት የሕግ ተግባራት ላይ ለተደረገው ውይይት ፣ ጀምስ ፣ ኤል ሄልደብራንድ ፣ ዘ. ሶሲዮሎጂ ኦፍ ሶቪየት ሎው /ኒው ዮርክ ፣ 1972/ ፣ 111 ይመልከቱ ።
15. ስለ ሶቪዬት ኅብረት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዚሁ ዓይነት ተግባር ፣ ገጽ ‡ ኢ ፣ ትሩብኒኮቭ ፣ " ሪቪው ኦፍ ዲስገርንስ ስሩ ጁዲሺያል ሱፐርቢዢን" ፣ ሶቪዬት ሎው ኤንድ ገቨርንሜንት /ቅጽ 9 ፣ ቁጥር 2/፣ገጽ 188—204ና ቢ. ኩሊኖብ ፣ " ዘ ሱፐሪም ኮርት ኦፍ ዩ ኤስ ኤስ አር—ዘ ሃያስት ሊንክ ኢን ዘ ሶቪዬት ጁዲሺያል ሲስተም " ሶቪዬት ሎው ኤንድ ገቨርንሜንት /ቅጽ 17 ፣ ቁጥር 2/ ገጽ 57—74
16. ከላይ በቁጥር 3 የተጠቀሰውን አዋጅ አንቀጽ 13 ይመልከቱ ።

JOURNAL
of
ETHIOPIAN LAW

Published by the Faculty of Law,
Addis Ababa University in Co-operation
with the Ministry of Law and Justice

EDITORIAL BOARD

Wondayen Mehretu, Chairman
Minister of Justice

Bilillign Mandefro
Procurator General

Girma Selassie Araya
President of the High Court

Daniel Haile
Dean of Faculty of Law

Assefa Liben
President of the Supreme Court

Tadesse Beyene
Director of Institute of Ethiopian Studies

Selamu Bekele, Secretary
Editor-in-Chief

EDITORIAL TEAM

Selamu Bekele
Editor - in - Chief

Z. Galicki, Article's Editor
Menberetsehi Tadesse, Cases, Commentary and Current Issues Editor

Ibrahim Idris, Managing Editor
Mihret Adereye, Secretary

For correspondnce use the following address: Journal of Ethiopian Law, P.O. Box 1176, Addis Ababa University, Addis Ababa, Ethiopia Telephone 11-17 33/110844 Ext. 108, Cable Address, AAUNIV, Telex 21206

Assistant Editors

Muluken Teshome
Seifeselassie Lema
Takele Tezera
Yossias Tadesse

Belachew Antoine
Dessalegn Mesfin
Haileleul Mulugeta
Mahari Radae

Table of Contents

ARTICLES :-

Tewodross II and the regime of

extra - territoriality under the
Anglo - Abyssinian treaty of 1849.
Tamiru Wondimagegnehu 91

The Amharic Letters of Emperor
Theodore of Ethiopia to Queen
Victoria and her Special Envoy 114

Treaty of Amity and Commerce between
Great Britain and Abyssinia 118

The Law Making Process in Ethiopia:
Post - 1974, part one.
Shiferaw Wolde Michael 122

The Law Making Process in Ethiopia:
Post - 1974, part Two
Shiferaw Wolde Michael.. 128

Cases :-

Tutor of Ayeletch Wolde Gebrael V.
Trunesh Tessema
(Civil Appeal No. 394/72 E.C.) 138

Tadesse Gurmu V. Truworq Eyassu
(Civil Appeal No. 1111/74 E.C.) 147

Commentary :-

Acknowledging the illigitimate child.
Mesfin Gebre Hiwot 153

Current Issue :-

The hearing of final judgment by the Supreme court
by way of cassation : Another right of appeal
granted to any one of the parties ?
Yoseph Gebre Egziaber 161

Tewodros II and the Regime of Exra-Territoriality under the Anglo-Abyssinian Treaty of 1849

Tamiru Wondimagegnehu

Introduction

Tewodros II of Ethiopia is probably among those leaders whose names are associated with as much curses as praises. One of thoseacts for which he definitely deserves praise is his refusal to give in to British extra territorial right which was bequeathed to him through his victory over Ras Ali.* In its simplest sense the regime of extra-territoriality was meant to serve as a vehicle of guaranting aliens to live under the protection of their national laws even when they are in a territory other than their own.

The pretext for such an arrangement has varied through the ages. It was religious difference at first and as the years went by the protection of other interests such as commerce and trade crept into the list. Such a special protection was needed, so it was alleged by the lackeys of the regime, because the host countries with their inferior and retarded civilization lacked legal institutions for the protection of foreigners in a manner consistent with the requirements of civilization.[1]

The regime of extra- territoriality, therefore, generally involved a so-called civilized state on the one hand and a backward one on the other. In such a deal, however, it was the so-called backward state, that was invariably the loser as it was expected to make concessions on its sovereign right in return for nothing.

The striking of such a derogative deal with one power was enough to extend the scope of the treaty to include other states not party to it. This was generally achieved through the application of the most favoured nation treatment clause contained either in previous treaties or in newly concluded ones.[2] Such an arrangement was, obviously, a limitation of the sovereignty of the conceding state in more than one way. It meant, in many respects, the exclusion, of the alien community from the jurisdiction of the state in which they reside or work . It also enabled the consul or diplomatic staff of a foreign power not only to usurp the judicial power of the host state , but also to apply his own legal system in a country which at least in theory, is sovereign and independent.

Since a good part of the trade and commercial activities were conducted by foreigners, such a treaty had also the additional effect of legislating such sectors out of the control of the host state. It was, in short, a prelude to a bigger loss which in many instances had resulted in the relagation of the host stat into a status of a colony or a protectorate.[3]

---

* See letters of Tewodros and the treaty of 1849 which are reprinted following the article as relevant background documents (Editor)

Not all leaders of the victim states were unaware of the heinous nature of such an arrangement. Emperor Tewodros II of Ethiopia who reigned from 1855-1868 was one of those leaders who foresaw the evil consequences of such a deal and stood squarely to oppose it. It was the first and the earliest attempt to impose such an affront on the independence of Ethiopia. His consistency was so remarkable in that he preferred death in his own hand, rather than capitulate to British dictation.

Background to the Treaty of 1849

An outline of the history of the treaty, or that of Emperor Tewodros is beyond the scope of this short paper. What is intended here is to discuss and point out some of the salient elements in the Anglo-Abyssinian Treaty of 1849 regarding extra-territoriality and to touch on some of the objections which were raised by the Emperor. But to do that a sketchy presentation of the background of the treaty as well as the personalities that were closely involved with it would first be in order.

The history of the Anglo-Abyssinian Treaty of 1849 is in a way a history of Walter Chichele Plowden. Walter Plowden was born on August 9,1820.He went to India at the age of 19 and joined the firm of Carr, Tagore & Co., of Calcutta which job he gave up 4 years later with a view to return to England. On *his* arrival at Suez, sometime in 1843, he met Mr. John Bell, an ex-naval officer in the British army, and on the spur of the moment decided to join Mr. Bell in an expedition into Abyssinia with the aim of discovering the source of the White Nile. He remained in Abyssinia till 1846 when he decided to go back to England via Massawa, and reached London in August 1847. His nearly five years travel in Ethiopia had gained him the acquaintance and, indeed, the confidence of some of the prominent chieftains of the time. Ras Ali and Dejach Wube were among them. These two powerful chieftains were competing for the position of king-maker-a position that not only gave the powerful Ras to decide on who should be the king but also to act in the name of the king without even caring to consult him. Circumstances were in favour of Ali in the struggle, and upon his departure in 1846 Plowden undertook to act as Ali's emissary to Britain. He was accompanied by Aleka Desta as an envoy who, it is said, refused to proceed to London from Cairo after his bitter experience of shipwreck in the Red Sea.[4]

Ras Ali's message was not serious in content, so much so that he did not see the need even to put it on paper. With the envoy unwilling to go to England and with the small presents intended for the Queen laying in the bottom of the Red Sea, the task of conveying the oral message to great Britain was entirely left to Plowden. The purpose of the mission, as far as Ras Ali was concerned, did not pass from a mere expression of courtesy. This is evident from Plowden's own memorandum, which states in part,[5]

> It is not to be supposed that the Ras could have in view any more definite result than a certain interchange of courtesy, the consequent facilities and protection that would be afforded by him to English travellers.

But from the point of view of Plowden the mission had definite intent and result. In the first place it had enabled him to travel to England and back at the expense of the British government. In the second place it had augmented his chance of having audience with the high ranking officials of the Foreign Office providing him thereby with the residual opportunity to advance his own views on what Britain should do about Ethiopia and possibly to press for it. In the end it was Plowden the British and not Plowden Ali's envoy that emerged. Great Britain was quick to act. Sometime in 1847 Palmarstone had decided to appoint Mr. Plowden British Consul in Abyssinia with his residence at Massawa.

After further consultation Plowden was given his directives and assignments and was dispatched in January 1848 to Abyssinia, via Massawa, with a letter for Ras Ali and draft of the treaty to be concluded "without any material alterations". Plowden was thus expected to accomplish mainly two tasks. The first was to establish British consulate in Massawa and to serve as the first British consul in Ethiopia from there; and the second was to get Ras Ali to agree to the terms of the treaty "drawn up in the name of the Emperor or in the joint name of the Emperor and the Ras" and to have it "signed by both".[6] Plowden had equally succeeded and failed in both. His task was a success vis-a-vis Ras Ali, but it was a complete failure vis-a-vis Emperor Tewodros.

In as much as the establishment of the Consulate as well as the designation of a Counsul did not arise from any bilateral accord between the two countries, it was a unilateral act of Great Britain. The effect was, however, greatly mitigated by the fact that the Consulate was to operate from Massawa, a territory then under Turkish jurisdiction.

Although Plowden was appointed the first Consul he was by no means the first to advance the idea of Consulate in Abyssiina. Charles Beke claims the credit for having put forward the idea as far back as 1846. According to him the "idea did not originate in any political object but in consequence of a suggestion made by me in 1846 as to the obtaining of agricultural labourers from Abyssinia".[7] Palmerston hinges the reason on trade, and when Plowden insisted that the Consulate be established on Ethiopian soil, he is said to have rejected the proposal in these words: "All we want is trade and land is not necessary for trade."[8]

But, the purpose for establishing the Consulate, or the tasks assigned to the Consul, seem to be far from non political or simplistic as claimed by Beke and Palmerston. Past and subsequent events provide ample evidence to suggest otherwise. The inter European rivalry, specially between Britain and France,

which was evident from the intense diplomatic as well as religious activities in the courts of several chieftains from Shewa to Tegrai had no doubt their share to play. This was how Viscount Valentia, formerly Sir George Annesly, raised the alarm as early as 1804 for Great Britain against the impending French expansion in the region.

> The crescent of Mohammed no longer indeed, forebodes danger to christanity but the equally terrible eagles of regenerated France threaten universal destruction to ancient establishments, and it is apparent that their formidable master has more particularly formed his plans against the eastern Empire of England. It was for the furtherance of this object that Egypt was conquered - and it is a continuation... to cultivate the friendship of the Arab powers. Abyssinia is of infinitely more importance than these, but fortunately, France knew not that Abyssinia was accessible.[9]

The Viscount urged Great Britain to take advantage as the first comer by establishing relation with Abyssinia which in his words "will forever shut out the French, but if we should neglect the opportunity, they will profit by our folly..."The taking of Aden by the British in 1839, and the entrenchment of the Catholic Mission in northern Abyssinia as well as the intense activity of the French around Zeyla and Tajura were not signs that could help to mitigate the feud either.

This is also what one learns from the indignant reply of Plowden's brother against charges of breach of duty levelled at Plowden posthumously by officials of the Foreign Offce. According to him,

> "The duties of the Consul were to watch and counteract foreign intrigue-that of France especially, to keep peace between Abyssinia and Egypt; to obtain the abolition of slavery and to establish and promote commercial intercourse between Great Britain and Abyssinia."[10]

At any rate, whatever may be the motive, Plowden was back at Gondar early in 1848 not as a traveller as theretofore he was, but as Consul of the British Government, and of course with a definite assignment.

Plowden's report to the Foreign Office indicates that he did not meet any difficulty in presenting the gifts he was carrying for the Ras or in having himself accepted as British Consul in Abyssinia. Nor was he challenged on the content of the treaty which was unilaterelly drafted by the Foreign Office.

One problem in connection with it was to track down Ras Ali to enlighten him on the purpose and content of the treaty. Plowden states that he was greatly assisted by his fellow countrymen John Bell who, having earlier enrolled himself in the service of the Ras, was holding a position of some prominence.

Finally, after 8 months of wandering with the Ras accompanying him on his various campaigns, Plowden was able to have the treaty signed by the Ras and not by the King as directed by the Foreign Office on November 2, 1849, at a place called Ennawga, in the province of Gojam. This led Plowden to suggest to the Foreign Office that a ratification of the treaty be addressed to Ras Ali " to impress him with the reality of the transac'ion" and as a result the letter of ratification was received by Ali on 1 March 1852 [11].

The occassion of the signing of the treaty is vividly portrayed by Plowden as follows:

> ... one morning, I went into his inner tent and has the treaty read to him by my scribe.
>
> ... He kept talking to his favourite shoomeree about a horse that was tied in the tent and that was nearly treading me under foot half a dozen times' (we all sat on the ground, the Ras inclusive). On asking me some trifling question in answer, I begged his attention to what was being read, to which he assented, and yawned exceedingly - however, it was got through some points having been explained and dwelt upon by me. Where upon, the Ras said that he saw no harm whatever in the document: on the contrary, that it was excellent, but appeared to him exceedingly useless, in as much as he did not suppose as Abyssinia was then constituted, that one English merchant would or could enter it in ten years. He then sealed the two copies, and gave his own to a favourite debtara, with orders to take it to Debre Tabor, and lock it up there." [12]

But Ali was not there to stay for long. He did not stay long enough even "to publicly proclaim the Consulate and the principal points of the Treaty" much less witness its implementation. His demise came swiftly when his soldiers were beaten successively by the forces of Kassa, his son-in-law, who was soon to become Emperor Tewodros II King of Kings of Abyssinia. The succession of events and the incredible decline of the Ras, who had signed the Treaty with the assumed title of 'Ali Neguse Abesha' only four years ago was so fast as to lead Plowden to inform the [13] Foreign Office that the Treaty with Ras Ali was " likely to become a nullity ". Ali knocked out of the scene soon after, Kassa and Wube emerged as the principal contenders to fill the place vacated by him. That too was not a duel which lasted long.

The battle of Deresge between the forces of Kassa and Wube of February 1855 sealed off the fate of Wube and that of the Zemene mesafint (alias the Era of the Princess, the period between 1769 - 1855 in Ethiopian history). Kassa, who emerged victoricus in successive battles, was not content with the assumption of the fictiticus title of King-Maker, so much vaunted and fought for by his predecessors. He was intent to deal with it decisively and to do that he had to pierce the veil that separated the puppet king from the strong chieftain and unite them in the personality of one leader. And that was precisely what he did when he was crowned and declared himself Tewodros II king of kings of Abyssinia on or around II February 1855 at the church of Deresge. It was the beginning of the end of an old era and the commencement of new one.

With kassa installed as Tewodros at the helm of state power and with the consequent confusion resulting from the war plowden saw it fit to remind Tewodros of the Treaty he had signed with Ras Ali and of his postion as British counsul in abyssinia.

He was at the court of Tewodros in June 1855 at the behest of John Bel who having changed side was even better off under his new master.

The Treaty of 1849

But before proceeding into that, a quick survey of the relevant part of the treaty would first be in order.

The Anglo - Abyssinian Treaty of 1849 was concluded between the two countries as a Treaty of Commerce and Friendship. [14]

It consisted of 19 Articles of which the first 16 and the last Articles were substantially identical with the 16 Articles that constituted the Anglo-Shewan Treaty signed on November 16, 1841 [15] between Sahle silassie king of Shewa and Captain W.C. Harris at the Shewan Capital of Angolella.

